ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

መቅድም 1

መግቢያ 2

1. የአውራ አምባ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ሁኔታ 5

2. የአውራ አምባ ማህበረሰብ አመሰራረት (በዙምራ ሲገለጽ) 6

3. የአውራ አምባ ማህበረሰብ የአባልነት ደረጃዎች 11

3.1 የማህበረሰብ አባል 11

3.2 የኅብረት ስራ ማህበር አባል 11

4. አምስቱ የዙምራ መሰረታዊ ሀሳቦች 13

4.1 የሴቶችን እኩልነት ማክበር 13

4.2 የህፃናት መብትን ማክበር 15

4.3 በእርጅና ሆነ በጤና እጦት ለስራ ብቁ ያልሆኑ ደካሞችን መንከባከብ 15

4.4 መጥፎ አነጋገርና መጥፎ አሰራርን ማስወገድ 16

4.5 የተበጣጠሰ ወገንተኝነትን ማስወገድ 17

5. የአውራ አምባ ማህበረሰብ አኗኗር 18

5.1 መዋቅራዊ አደረጃጀት 18

5.2 የቤት አሰራርና አያያዝ 20

5.3 የስራ ባህል 24

5.4 የሴቶች እኩልነት 29

5.5 ቱሪዝም 30

5.6 ለወገን ደራሽ 32

5.7 የህጻናት አስተዳደግ 35

5.8 የቤተሰብ ውይይት (ሰላምን ፍለጋ) 38

5.9 ትምህርትና የመማማር ሂደት 40

5.10 ኪነ-ጥበብ 46

5.11 የጋብቻ ስነ ስርዓት 47

5.12 እምነት 48

5.13 የሀዘን ስነ-ስርዓት 51

6. ከጎብኚዎች አስተያየት 53

7. ከክብር ዶ/ር ዙምራ ኑሩ አባባሎች ጥቂቶቹ 67

መቅድም

የአውራ አምባ ማህበረሰብን ለመጎብኘት ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚመጡ ጎብኚዎች የክቡር ዶክተር ዙምራን ፍልስፍና በጽሁፍ እንዲሰፍር የሚጠይቁ ብዙዎች ናቸው፡፡ ዙምራ ግን ይህ ሃሳብ በመጽሀፍ እሚሰፍር ከሆነ ቴክኖሎጅ እያደገ በሚሄድበት ጊዜ የተጻፈው በዚህ ልክ ነውና ከዚህ በላይ ለማለፍ አይቻልም በማለት የኋላ ልጅን ገድቦ ስልጣኔን ሊያስቀር ስለሚችል በመጽሀፍ መስፈር የለበትም እያለ መልስ ይሰጣቸው ነበር፡፡ ጎብኚዎችም ይህ የምትመልሰው መልስ የአንተን አርቆ አሳቢነት በበለጠ አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ በአንተ አንደበት የሚፈልቁ ሀሳቦች ሁሉ ለሰው ልጆች ጠቃሚ የሆኑና ከዚህ በፊት ያልተገኙ በቀጣይም ሊመጡ ይችላሉ ተብለው የማይታሰቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የምታፈልቃቸው ሀሳቦች በሙሉ መሆን የሚገባቸውና ለሰው ልጆች በሙሉ አስተማሪ ስለሆኑ ሁሉም በመጽሀፍ ሰፍረው ለሁሉም የሰው ልጆች የሚዳረሱበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል ይላሉ፡፡ በኋላም ክቡር ዶክተር ዙምራ በዚህ ሀሳብ ተስማምቶ ሀሳቡ በጽሁፍ እንዲሰፍር ፈቅዷል፡፡

ስለማህበረሰቡ በርካታ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ የ2ኛ ዲግሪና የ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፋቸውንና እንዲሁም የውጭ አገር ጥናትና ምርምር አቅራቢ ተመራማሪዎች የተለያዩ ጉዳዮችን እየመረጡ ጽፈዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ ጸሃፍት የማህበረሰቡን ነባራዊ ሐቅ ከራሳቸው የህይወት ተሞክሮ ጋር ስለሚያያይዙት ሀሳቦቹ ተዛብተው የሚገኙበት አጋጣሚዎች ብዙዎች ናቸው፡፡ ጎብኚዎች ይህንንም ችግር ለመቅረፍ መጻህፍት በማህበረሰቡ ልጆች መጻፍ እንዳለባቸው አስተያየታቸውን ይጠቁማሉ፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ልጆችም ዙምራ ያሳደገንና ከጧት ከማታ ሀሳቡን እያዳመጥን ያለን ብንሆንም ዙምራ የሚያፈልቃቸው ሀሳቦች የተለዩና አዳዲስም በመሆናቸው ሀሳቦቹን ያለምንም እንከን ለማቅረብ አዳጋች መሆኑ አይቀርም፡፡ በተቻለ መጠን ግን ሀሳቡን ሳናዛባ ለማቅረብ ከሀሳቡ አፍላቂ ጋር በተደጋጋሚ እየተገናኘን ለማጥራት የሞከርን ቢሆንም አልፎ አልፎ ግድፈቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

ይህንን ጽሁፍ ያዘጋጀነው አካላት የተለያዩ መጻህፍትን በማንበብ የአጻጻፍ ስልታችንን ያዳበርን ባለመሆናችን የቋንቋ አጠቃቀማችና አጠቃላይ የአጻጻፋችን ሁኔታ በርካታ ግድፈቶች ሊኖሩበት እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም አንባቢያን ለግድፈቶቻችን አስተያየታችሁን እንድትሰጡን እየጠየቅን በቀጣይ የተማሩና በሙያው የተካኑ የማህበረሰባችን አባላት እተበራከቱ ሲሄዱ ግድፈቶቻችን ይሞላሉ ብለን እናስባለን፡፡

መግቢያ

የአውራ አምባ ማህበረሰብ በኢትዮጵያና እንዲሁም በሌሎች የአላማችን ክፍሎች የተለመዱና ጎታች የሆኑ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ቆም ብሎ በማሰብና ከስራቸው ተነቅለው እንዲጠፉ በማድረግ ትክክለኛና አዲስ ጎዳና በመዘርጋት እየተገበረ ያለና የሌላው የዓለም ክፍል ህዝቦች ትምህርት ወስደው በመተሳሰብና በመረዳዳት እየሰሩ፣ በመካከላቸው የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ስሜት ዳብሮ በፍቅር፣ በሰላምና በደስታ እንዲኖር የሚያደርግ ስልት ቀይሶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ይህ ማህበረሰብ የተመሰረተው በክቡር ዶክተር ዙምራ ኑሩ ሲሆን ዙምራ በ2 ዓመት ዕድሜው ግልጽ ያልሆኑለትን ጉዳዮች በማንሳት ጥያቄዎቹን ሊመልሱልኝ ይችላሉ ብሎ ለሚያስባቸው ሰዎች ማቅረብ ጀምሯል፡፡ ከ4 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ደግሞ በሴቶች እኩልነት፣ በህጻናት መብት፣ ደካማ ወገንን በመደገፍ፣ መጥፎ አሰራርና አነጋገርን ከነአካቴው ማጥፋት በሚሉት መሰረታዊ ሀሳቦቹ ከአካባቢው ህብረተሰብ ባይተዋር ሆኖ የሚያደርገው አጥቶ የህጻንነት ጊዜውን አሳልፏል፡፡

ክቡር ዶክተር ዙምራ ከ13 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ እነዚህ መሰረታዊ ሀሳቦቹ በአካባቢው ህብረተሰብ ተቀባይነትን ስላላገኙለት ሀሳቡን የሚጋራው ህብረተሰብ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ውሎ እሚነጋገረው መሽቶ እሚያድርበት እያጣ በባዶ አንጀቱ በየዱሩ ከአውሬዎቹ ጋር እያደረ በመከራና በስቃይ እየተንከራተተ 5 ዓመታትን ያህል በሰቀቃ ቢያሳልፍም ውጤታማ ሊሆን አልቻለም፡፡

በመሆኑም ትንሽ የህሊና ረፍት ቢሆነኝ ብሎ ወደቤተሰቦቹ ተመልሶ የእርሻ ስራውን እያካሄደ የሚያገኘውን ምርት ደካሞችን ለማከፋፈል አሰበ፡፡ ከዚያም በእርሻ ስራው ተሰማርቶ የሚያገኘውን ምርት ለደካሞች እያከፋፈለ መኖሩን ተያያዘው፡፡ በክረምት ወራት የእርሻ ስራውን እያካሄደ የሚያገኘውን ምርት ለደካማ ከማከፋፈሉ ተግባር ጎን ለጎን በበጋ ወራት ተስፋ ባለመቁረጥ የሀሳቡ ተጋሪ ህብረተሰብ ፍለጋውን አጠናክሮ ገፋበት፡፡

ይህን ደካሞችን የመርዳቱንና የሀሳቡ ተጋሪ ህብረተሰብ ፍለጋውን ለበርካታ ዓመታት ሲያካሂድ ከቆዬ በኋላ ፎገራ ወረዳ ላይ በጎረቤታማ ቀበሌዎች ሀሳቡን የሚያደምጡ አጋሮችን ማግኘት ቻለ፡፡ እነዚህን የሀሳቡ አጋር ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎች ሲያገኝ የሚኖርበትን ቦታ ለቆ ወደሰዎቹ በመሄድ ሁሉንም መሰረታዊ ሀሳቦቹን ሲያስረዳቸው ሰዎቹም በሀሳቡ ስለተስማሙ በ1964 ዓ.ም የአውራ አምባን ማህበረሰብ መሰረተ፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ሁለት ዓይነት የአባልነት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነሱም የአውራ አምባ ማህበረሰብ አዲስ ምዕራፍ ባህሪና ልማት ግንባታ ሁለገብ ማህበር (**የማህበረሰብ**) አባልና የአውራ አምባ ማህበረሰብ የገበሬዎችና እደ-ጥበባት ሁለገብ ኅብረት ስራ ማህበር (**የኅብረት ስራ ማህበር**) አባል ናቸው፡፡ የማህበረሰብ አባል ማህበረሰቡ የሚመራባቸውን እሴቶችና መርሆዎች በማወቅ፣ በመተግበርና እሴቶቹንም ወደ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል እንዲስፋፉ በማድረግ የሚኖር የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ የማህበር አባል ደግሞ የማህበረሰብ አባል ከሆኑት ግለሰቦች መካከል ደካማ ከጠንካራ በመሆን እየተደጋገፉ በመስራት ሁሉን አቀፋዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ያመች ዘንድ ጉልበቱንና ዕውቀቱን በማስተባበር በጋራ ሰርቶ በማምረት ጥቅምና ጉዳቱን በጋራ ተካፋይ በመሆን የሚኖር ነው፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ዙምራ የተነሳባቸውን መሰረታዊ ሀሳቦች ማለትም የሴቶችን እኩልነት አረጋግጦ፣ የህጻናትን መብት አስከብሮ፣ ለስራ ብቁ ያልሆኑ አቅመደካሞችን ተንከባክቦ፣ መጥፎ አነጋገርንና አሰራርን አስወግዶ፣ በራስ ላይ እንዲሆኑ የሚፈለጉትን ነገሮች በሰዎች ላይ እንዲሆኑና በራስ ላይ እንዳይደርሱ የሚፈለጉ ነገሮችን በሰዎች ላይ እንዳይደርሱ አርቆ አስወግዶ፣ ነጭ ጥቁር ማድረግ የአንድ ፈጣሪ ስራ ሆኖ ሁሉም የሰው ልጆች የዘር ሀረጋችን የአንድ አዳምና ሄዋን ልጆች ነን ብሎ በማመን ሁሉንም ወንድም እህት በማድረግ ለሁሉም እኩል ክብር ሰጥቶ የሚኖር ማህበረሰብ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ለስራ ያመቸው ዘንድ እሚመራው 13 ኮሚቴዎችን አዋቅሮና አደራጅቶ ነው፡፡ እያንዳንዱ ኮሚቴ የራሱ አባላትና የስራ ድርሻ አለው፡፡ ከ13 ኮሚቴዎች የልማት ኮሚቴው አብይ ኮሚቴ ሲሆን በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎችና የሌሎቹን /የ12ቱን ንዑሳን ኮሚቴዎች/ የስራ እንቅስቃሴዎቻቸውን ይከታተላል፤ ያስተባብራልም፡፡

ማህበረሰቡ በሳምንት አንድ ቀን በነቂስ በመውጣት እንደችሎታው በገቢ ማስገኛ የስራ እንቅስቃሴ ተሰማርቶ ሲንቀሳቀስ ይውላል፡፡ በዚህ የስራ እንቅስቃሴ የሚገኘው ገቢና የማህበረሰቡን ልምዶች ለመካፈል ከሚመጡት ጎብኝዎች የሚገኘው ክፍያ ለወገን ደራሽ ይባላል፡፡ ይህ የወገን ደራሽ ገንዘብ የሚውለው ለአቅመ ደካሞች፣ ታመው መታከሚያ ላጡ ግለሰቦች፣ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ለማሟላትና እንዲሁም ከማህበረሰቡ ውጭ ላሉ የባሰ ችግር ውስጥ ወድቀው ለሚገኙ ሰዎችና ተዛማጅነት ላላቸው ጉዳዮች ነው፡፡ የወገን ደራሽ ገንዘብ አቅሙ እየተጠናከረ ሲሄድ በዓለማችን ለሚገኙ በችግር ላይ ወድቀው ለሚገኙ ሁሉ ይደርሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

የማህበረሰቡ አባላት በሙሉ በየ15 ቀኑ አንድ ጊዜ ሰላምን ፍለጋ የቤተሰብ ውይይት ያካሂዳሉ፡፡ ለዚህ ውይይት የመወያያ አጀንዳ የሚሆኑት የስራ እቅድ ክንውንን በተመለከተና በጥቅሉ መጥፎ አሰራርና አነጋገርን መዋጋትን በተመለከተ ናቸው፡፡ የዚህ የቤተሰብ ውይይት ዋና ዓላማ የሰው ልጆች በሙሉ በየቤታቸው እየተወያዩ ችግሮቻቸውን ሁሉ እየፈቱ ዕድገትና ሰላምን ለማምጣት ቁልፍ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሁሉም የአለም ህዝብ በየቤቱ ስለበጎ ስራ ተወያይቶ ቢወጣ በአለም ላይ ሰላም ይሰፍናል ብሎ ያምናል፡፡

በማህበረሰቡ ጋብቻ የሚፈጸመው በሁለቱ ፆታዎች ሙሉ ፈቃደኝነትና ዕድሜያቸው ወንዱ 20 ዓመትና በላይ፣ ሴቷ 19 ዓመትና በላይ ሲሆናቸው ነው፡፡ ጋብቻ ከተፈጸመ በኋላ ሁለቱም ተጋቢዎች በተለመደው የስራ እንቅስቃሴያቸው ተሰማርተው ይውላሉ፡፡ በጋብቻ ጊዜ የሚባክን ቅንጣት ታክል ጊዜም ሆነ ለሰርግ ተብሎ የሚወጣ ወጭ የለም፡፡ ከጋብቻ በፊት ወንዱም ሴት፣ ሴቷም ወንድ አያውቁም፡፡ ከትዳር በኋላም ከትዳር ጓዶቻቸው ውጭ ፈጽሞ አይሔዱም፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ሰማይና መሬትን፣ ሌትና ቀንን፣ ሴትና ወንድን አየርን፣ ፀሀይንና ሁሉንም በመሬት ላይ ያሉ ነገሮችን የፈጠረ አንድ ፈጣሪ እንዳለና እምነትም የሚገለፀው በበጎ ስራ እንደሆነ ያምናል፡፡ በመሆኑም በራስ ላይ እንዲደረጉ የሚፈለጉትን መልካም ነገሮች በሰዎች ላይ እንዲደረጉ በማድረግና በራስ ላይ እንዳይደርሱ የሚፈለጉትን መጥፎ ድርጊቶች በሰዎች ላይ እንዳይፈጸሙ አርቆ አስወግዶ ነው እሚኖረው፡፡

በአውራ አምባ ማህበረሰብ ሀዘን ማለት ሰዎች በህይወት እያሉ በሰዎች መካከል ሆነው ለሚገጥማቸው ችግር ዋስትና በመሆን ደስታቸውንም ሆነ ችግራቸውን በጋራ በመካፈል ሰዎቹ ከገጠማቸው ችግር መታደግ መቻል ማለት ነው፡፡ ከአቅም በላይ ሆኖ በማህበረሰቡ አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ከውስጥ የመነጨ ስሜት ነውና እንባ ማፍሰስ አይቀርም፡፡ ነገር ግን ወዮ እያሉ፣ ደረትን እየደቁ፣ ፊትን እየነጩ ሙሾ በመደርደር ማልቀሱ ያን የሞተን ወገን አይተካም፡፡ እንዲያውም ተጨማሪ ጉዳት ነው እሚያስከትለው፡፡ የቀብሩ ስነ-ስርዓትም የሚፈፀመው ስነስርዓቱን ለመፈጸም ይበቃሉ በተባሉ ሰዎች ነው፡፡ የቀብር ስነስርዓቱን ለመፈጸም ከሚሄዱት ሰዎች የተረፉት የሟቹን ቤተሰብ ሲያፅናኑ ይቆያሉ፡፡ የቀብር ስነስርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የማህበረሰቡ አባላት ወደየስራ ዘርፋቸው የሟቹን ቤተሰብ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ይህን የሚደረገው የሟቹ ቤተሰቦች ሀዘኑን እንዲረሱት በማሰብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሀዘኑ ያበቃል ማለት ነው፡፡

1. የአውራ አምባ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ሁኔታ

የአውራ አምባ ማህበረሰብ የሚገኘው በአማራ ክልል፣ በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን፣ በፎገራ ወረዳ፣ በወጅ አውራ አምባ ቀበሌ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሰፍሮ የሚገኝበት ቦታ ከወረዳው ዋና ከተማ ወረታ ወደ ደብረታቦር በሚወስደው አውራ መንገድ 12 ኪ.ሜ ከተጓዙ በኋላ 2 ኪ.ሜ በስተቀኝ በኩል ገባ ብሎ ይገኛል፡፡



የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ካርታ

የወጅ አውራ አምባ ቀበሌ መልከዓ ምድር 30% ሜዳማ፣ 40% ተራራማ፣ 30% ወጣገባ ነው፡፡ ቀበሌው 2000ሜ ከባህር ጠለል በላይ ከፍታ ያለው ሲሆን የአፈር ዓይነቱ በአብዛኛው ቡናማ (ሸክላ) አፈር ነው፡፡ የቀበሌው የአየር ንብረት በአብዛኛው ወይናደጋ ሲሆን አማካይ የሙቀት መጠኑ 25^{0}ሴና አማካይ የዝናብ መጠኑ 4500ሚ.ሜ ነው፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ መኖሪያ መንደር (2003ዓ.ም)

2. የአውራ አምባ ማህበረሰብ አመሰራረት (በዙምራ ሲገለጽ)

በ6 ወር እድሜዬ ቆሜ እንደሄድኩ፣ በ2 ዓመቴ እንደትልቅ ሰው የመናገርና የመጠየቅ ብቃት እንደነበረኝ እና በ4 ዓመት እድሜዬ ደግሞ በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮችን ሳነሳ እንደነበር እናቴ አጫውታኛለች፡፡ ከአራት ዓመት ዕድሜዬ ጀምሮ በሴቶች እኩልነት፣ በህጻናት መብት፣ ደካማ ወገኖችን በመደገፍ፣ በአጠቃላይ መጥፎ አሰራርንና አነጋገርን በማስወገድ ሰላም መፍጠር በሚሉት መሰረታዊ ሀሳቦቼ በአካባቢው ካለው ማህበረሰብ ተለይቼና ባይተዋር ሆኜ እማደርገው አጥቼ የህጻንነት ጊዜዬን አሳልፊያለሁ፡፡

በ13 ዓመቴ የሰው ልጆችን እንደ እህል እንደ ውሃ ተርቤ፣ ሰው እያለ ሰው ያጣሁ ሆኜና በአካባቢው ያን የሚፈልግ አጥቼ ሀሳቤን የሚጋራኝ ሰው ፍለጋ ከቦታ ቦታ ስባዝን ቆይቻለሁ፡፡ ይህን ሁኔታዬን ያዩ ሰዎች ከሁሉም በላይ ምንድነው እምትፈልገው ብለው ቢሉኝ የሰው ልጅ እንደ እንጀራ፣ እንደ እህል፣ እንደ ውሃ ነው እሚርበኝ፣ እሚጠማኝ ብዬ ነው እምላቸው፡፡ ናፍቆቱ ሲብስብኝ የዓለም የሰው ልጆች የኔ ሆነው ባገኛቸውም እንኳ ረሀቤ የሚወጣልኝ አይመስለኝም፡፡ እናም ያንን አጥቼ ጎጃም፣ ጎንደር ወሎ እያልኩ ስባዝን አሁንም እንዳሰብኩት አልሆነም፡፡ ውዬም እምነጋገረው፣ መሽቶም እማድርበት አላገኘሁም፡፡ ማታ ማታ ዛፍ ላይ እሰቀላለሁ፤ ሲጎረብጠኝ ተስፋ በመቁረጥ ወደ መሬት እወርዳለሁ፡፡ አውሬዎች እየተፈራረቁ ከበውኝ ያድራሉ፡፡ ሲነጋጋ አውሬዎቹ ጥለውኝ ይሄዳሉ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን የሚበላውንና የሚጠጣውን ነገር እናቱ ትቁጠረው፡፡

ከህጻንነቴ ጊዜ ጀምሮ በምጠይቃቸው ጥያቄዎችና በማነሳቸው ከሰዎች ለየት ያሉ ሀሳቦች በአካባቢው ያሉ ሰዎችና እንዲሁም የስጋ ዘመዶቼ **ይኽ ልጅ ታሟል** እያሉ ሀሳቤን አልተቀበሉኝም፡፡ እድሜዬ እያደገ ሲሄድ በዓይኔ እማየውና በጆሮዬ እምሰማው አእምሮዬን እረፍት እየነሳው ሲመጣና መፈጠሬን የጠላሁበት ጊዜ እየመጣ ሲሄድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየተዘዋወርኩ ሀሳቤን የሚጋራኝ ባገኝ ብዬ አሰብኩ፡፡ ከቦታ ቦታ

እየተዘዋወርኩ በመንቀሳቀስ ሰዎች በሀዘኑ፣ በደስታውና በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚሰባሰቡበት ጊዜ አራቱን መሰረታዊ ሀሳቦቼን የማካፈል እንቅስቃሴዬን ሳደርግ ቆየሁ፡፡

ይህን በማደርግበት ጊዜ እንደ ወላጆቼ ታሟል ባይሉኝም "ይቺ ልጅ ምን ማለቷ ነው? እምትናገረው ሀሳብ መልዕክት ያለው ነው ግን ማን ይወስደዋል ብላ ነው?" እያሉ በግርምት ከማየት በቀር ሀሳቤን እሚረዳልኝ አላገኘሁም፡፡ ሀሳቤን ስነግራች ግር ሲላቸው ሀሳቤ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ብዬ ስጠይቃቸው ትክክልማ ትክክል ነው፡፡ ግን ሰው አይሄድበትም (አይችለውም)፡፡ ብቸኛ ነህ ይላሉ፡፡ እኔም አይ ሰው መውሰድ አለመውሰዱን ተውት፡፡ ሰው ወሰደው አልወሰደው አይደለም፡፡ ብቻ ትክክል መሆኑን ያዙልኝ፡፡ እስከመሸብኝ ድረስ ሄጄ አድራለሁ እላቸዋለሁ፡፡

ወይ እሚሰማኝ፣ ወይ እሚጠይቀኝ ባገኝሁ ብየ የተንከራተትኩበትን ሁሉንም አላገኘሁ፡፡ ተስፋ ስቆርጥ እንግዲህ ወደ አገር ቤት ልመለስና ወላጆቼ እንደሚሰሩት እየሰራሁ ባይሆን በአካባቢው ያሉ ደካሞችን እየረዳሁ ብሄድ የህሊና ረፍት አገኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ፡፡

የማህበረሰቡ መስራች ክቡር ዶክተር ዙምራ ኑሩ (1985)

ከዚያ ተመልሼ ከወላጆቼ ጋር ተደባልቄ ትዳር ልይዝ ነው ሴት ፈልጉልኝ ስላቸው ደስታ ተሰማቸው፡፡ አብዶ፣ ታሞ፣ ከቦታ ቦታ እየዞረ ሲሉ የነበሩት ትዳር ልይዝ ነው ብዬ ስላቸው ትዳር ካሰበ በሽታው ለቆት ነው፡፡ በሽታው ባይለቀው ኖሮ ትዳር አያስብም ነበር የሚለውን ያስቡና ደስ ብሏቸው ወዲያው ሴቷን ፈለጉልኝ፡፡ እኔም ትዳሬን መስርቼ እንደ ወላጆቼ እርሻ እያረስኩ በዓመቱ ያገኘኋትን ምርት በአካባቢው ለሚገኙ ደካሞች ማከፋፈል ጀመርኩ፡፡ ይህን በማከፋፍል ጊዜ አይ አይድንም የሚድን በሽታ አይደለም፡፡

እሱ አይበላም፣ አይለብስም፣ አይጠጣም፣ አልታደለም፡፡ የሱን ገንዘቡን ዘመድ አያገኘውም፡፡ ለባዕድ ነው እሚሰጠው ይላሉ፡፡ ባዕድ ዘመድ የሚባለው ልዩነት ሲመጣብኝ በሀሳብ ብቸኛ አደረገኝ፡፡ ብቻዬን መኖር አልችልም፡፡

በበጋው ወቅት ምናልባት እያልኩ ተስፋ አልቆርጥም፡፡ አንድ ቀን ሀሳቤን እሚጋራኝ አገኛለሁ እላለሁ፡፡ በጋ ላይ በአንዱ ቦታ ሂጄ እቆያለሁ፡፡ የእርሻ ወቅት ሲሆን እመለሳለሁ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልኩ ያለማቋረጥ ለበርካታ ዓመታት ያክል ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርኩ የሃሳቤ ተጋሪ ማህበረሰብ ለማግኘት እልህ አስጨራሽ ጥረት ካደረኩ በኋላ በአንደኛው ዓመት ከመኖሪያ ቦታዬ ከእስቴ ወረዳ ተነስቼ ወደ ጎንደር ስሄድ ፎገራ ወረዳ ላይ በገበሬዎች ዙሪያ ሃሳቤን የሚያዳምጡ ሰዎችን አገኘሁ፡፡ ሀሳቤን ሲያደምጡኝ በየዓመቱ እየተመላለስኩ ከሰዎቹ ጋር በርካታ ውይይቶችን ካደረኩ በኋላ እንግዲህ እዚያው ሂጄ ብቀመጥ እቅዴ ይሳካል ስል ስኖርበት የነበረውን የእስቴ ወረዳ ለቅቄ ሰዎቹ ወደ እሚገኙበት ፎገራ ወረዳ በ1964 ዓ.ም መጥቼ ተቀመጥኩ፡፡

እዚህ ተቀምጬ የአውራ አምባን ማህበረሰብ መሰረትኩ፡፡ ለማህበረሰቡ አባለት ለማቅረብ የመጀመሪያው መነሻ መሰረታዊ ሀሳቤ የሆነው የሴቶች እኩልነት ነው፡፡ *ሴት በሴትነቷ እናት ናት፡፡ ወንድ በወንድነቱ አባት ነው፡፡* አባትና እናት ሆነው ሴቷ እንደሞግዚት ወንዱ እነደአዛዥ የሆነበት ምክንያት በጉልበት ነው? በጉልበት ከሆነ ትርፍ ጉልበታችን ለስራ እናውለው፡፡ እናት እናት ናት፡፡ አባት አባት ነው፡፡ እናት በሌለችበት አባት የለም፡፡ አባት በሌለበት እናት የለችም፡፡ እኩል ሊያደርጋቸው ይገባቸዋል፡፡ ሚስቶቻችን ስንል ባዕድ መስለውን እንደሆነ እናቶቻችን እንበላቸው፡፡ እያልኩ ሀሳቤን ለሚያደምጡኝ ሰዎች አካፈልኳቸው፡፡

ማህበረሰቡ ሲመሰረት ከነበሩ አባላት መካከል ጥቂቶቹ

በመቀጠል ያነሳሁት ጉዳይ ጠብ *እስከናካቴው ከምድረ-ገጽ መወገድ አለበት* የሚል ነው፡፡ ሰላምን፣ ገነትን ፈጥረን መሄድ አለብን፡፡ እዚህ ላይ የነሱ ጥያቄ ምንድነው? ጠብ እንዴት ይቀራል ትላልህ? የሚል ነው፡፡ እኔም እንዲህ በማለት ነው መልሱን የሰጠኋቸው፡፡ ጠብ ስር የለውም፡፡ ጠብን እኛ ካወቅንበት ማስወገድ የኛ ነው፡፡ ጠብን ከመሳል ይልቅ ፍቅርን እየሳልን ብንሄድ የኛ ነው፡፡ ፍቅርንም ጠብንም እምንስለው እኛ ነን፡፡ ምርጫችን ሰላምና ፍቅር ከሆነ ጠብ የለም፡፡ ጠብን የሚያነሳሱ ሁለት ዐ/ነገሮች ናቸው፡፡ እነሱም መጥፎ አሰራርና መጥፎ አነጋገር ናቸው፡፡ መጥፎ ቢናገሩን እንደማንወድ፣ መጥፎ ቢሰሩብን እንደማንወድ፣ በራሳችን ላይ እንዲደረግብን የማይገባንን ነገር በሰው ልጆች ላይ ማስወገድ ነው፡፡ ያን ጊዜ ጠብ የለም፡፡ እላቸዋለሁ፡፡

ሌላው የጠየቁኝ ነገር *ሰላም እንዴት ይመጣል ትላለህ?* ብለው ነው፡፡ ሰላም የሚመጣው ሁሉም የሰው ልጆች ነጩም ጥቁሩም ሁሉም እህት፣ ሁሉም ወንድም ሆነን ከመካከላችን ችግር የደረሰበት ሰው ቢኖር ሁላችንም እጃችንን አንስተን የዚያን ሰው ችግር በማስወገድ ነው፡፡ ችግሩን ስናስወግድለት ደስታ ይሰማዋል፡፡ ገንዘባችን ደስታው ነው፡፡ ደስታውን መካፈል ያስፈልጋል፡፡ ከዚያ ተሳስበን ተዛዝነን ከሄድን እውስጥ ያለው ደስታ ነው፡፡ ደስታን ፈጠርን ማለት ሰላምን ፈጠርን ማለት ነው፡፡ ሰላምን ፈጠርን ማለት ደግሞ እምንፈልገውን ገነት ፈጠርን ማለት ነው፡፡ ይህን እራሳችን እምንሰራው ነው፡፡ ገነት እሚገኘው እዚህ ሳለን በሰራነው ስራ ነው፡፡ እዚያ ከሄድን በኋላ አይበስልም፡፡ ጠብን ማስወገድ ሰላምን መፍጠር ከሰማይ እንዲወርድልን አንጠብቅ፡፡ እዚሁ እኛ እምንፈጥረው ነው፡፡

ይህን ተማምነንበት ስንቀጥል በአካባቢው ያሉ ሰዎች አካሄዳችን አልዋጥላቸው ብሎ መኖሪያ ቢያሳጡንም የተማሩ ሰዎች እስከሚያገኙት ድረስ ህይወታችን መስዋት አድርገን ስንታገል ቆይተናል፡፡ የተማሩ ሰዎች እነማን ናቸው? የሀይማኖት አባቶችና የቀለም ምሁሮች ናቸው፡፡ የሀይማኖት አባቶችም ይሁኑ የቀለም ምሁሮች ያግኙት ነው ይበሉ ያንሱት፤ አይደለም ካሉ ይተውት፡፡ እስከሚያገኙት ድረስ ግን ህይወታችን መስዋዕት አድርገን ለተማሩ ሰዎች ማድረስ አለብን ብለን ሀሳባችን መስርተን ትግላችንን ቀጠልን፡፡ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ይህ አልዋጥላቸው ብሎ መኖሪያ ቢያሳጡንም ትግላችን በዚያው በመቀጠል ስንሄድ እነሱ ሲያቅታቸው በደርግ ጊዜ በ1980 ዓ.ም ወደ ፖለቲካው እያጋጩ ወያኔ የሚባል ስያሜ እያስጠጉ ሲሉ ደርግ ደግሞ እኛን ሊያጠፉ ሲመጣ እግሬ አውጭኝ ብለን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ተፈናቅለን ተሰደድን፡፡

ስደት ባለበት ስራ የለም፡፡ ስራ በሌለበት ገንዘብ የለም፡፡ እሚበላ እሚጠጣ የለንም፡፡ ብንታመም እምንታከምበት የለንም፡፡ በዚህም ሳቢያ የሞቱ ወገኖቻችንን በየቁጥቋጦው ስር አፈር እያለበስን ዓላማችንን ለተማሩ ሰዎች ለማድረስ ትግላችንን ቀጠልን፡፡

በ1985 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ከስደት ስንመለስ መሬታችን በአካባቢው አርሶ አደሮች ተይዞ አገኘነው፡፡ መሬታችንን ለማስመለስ ለወረዳ፣ ለዞንና ለክልል ብናመለክትም ምላሽ አላገኘንም፡፡ ያገኘነው ምላሽ ቢኖር የመሬት ስሪቱ ሲመጣ ታገኛላችሁ የሚል ነበር፡፡ የመሬት ስሪቱ እስኪደርስ ድረስ ለቤት-ቦታ የሚሆን ብሎ ወረዳው 17.5 ሄክታር ብቻ ሰጠን፡፡ የመሬት ስሪቱን መንግስት ለሁሉም እኩል እንዲደርስ ቢያወርድም ፊልድ የወጣው ቡድን ግን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመደራደር መሬቱን ሊሰጠን አልቻለም፡፡ በመሆኑም ለስራ እጦት፣ ለእንግልት፣ ለረሀብ፣ ለበሽታ ተዳርገናል፡፡ ከዚህም በከፋ ሁኔታ በርካታ የሀሳብና የስራ አጋሮቼ ለህልፈተ-ህይወት ተዳርገዋል፡፡ በኋላም ህይወት የተንጠለጠለው በመሬት ብቻ ሳይሆን በኢንዱስትሪም ማደግ ይቻላል ብለን በማሰብ በማህበር ተደራጅተን ወደ ስራ ገባን፡፡

በዚህ ሁኔታ ከ1964-1993 ዓ.ም ድረስ ሀሳቤን ለተማሩ ሰዎች ለማድረስ ይህን እልህ አስጨራሽ ትግል ካለፍን በኋላ ሀሳቤን ጋዜጠኞች በተለያዩ ሚዲያዎች ማለትም በጋዜጦች፣ በመጽሄቶች፣ በአማራ ሬዲዮ ጣቢያና በሌሎችም ሚዲያዎች ለህዝብ ለማድረስ በመጠኑ የዘገቡ ቢሆንም እንኳ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለሌላውም የዓለም ክፍል እንዲደርስ ፋና ወጊ የሆነው በ1993 ዓ.ም በጋዜጠኛ መቅጫ እንግዳየሁ፣ በዋና ካሜራ ማን ጌታቸው መሀሪና በረዳት ካሜራ ማን አስማማው ተዘጋጅቶ በአማራ ቴሌቪዥን ፕሮግራም በ2 ክፍል እንዲቀርብ የተደረገው ዝግጅት ነው፡፡

የሀሳቤ ሚዲያ ላይ መዋል ወይ እሚሰማኝ ባገኘሁ ወይ እሚጠይቀኝ ባገኘሁ ብዬ ያጣሁትን አሁን ላይ ክብር ምስጋና ይግባውና የሚሰማኝ እነኳ አገኘሁ /ያሰብኩትና ከልጅነቴ ጀምሬ ይዤው የመጣሁት ራዕዬ እውን ሆኗል/ ባልልም ሀሳቤን እሚረዳልኝ በማግኘቴ አንድ እርምጃ ብዬ እገኛለሁ፡፡ በአሁኑ ደረጃ ላይ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያሉ ሰዎች ሀሳቤን በመጽሄት፣ በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት እያገኙና እዚህም እየመጡ እየተረዱልኝ ይገኛሉ፡፡ አሁን ላይ አንድ እርምጃ ብዬ እገኛለሁና መነሻዬ ይኸ ነው፡፡ ለሰው ልጆች ነው፡፡ ይህ የገለጽኩት ደግሞ እየሰራነው፣ እያደረግነው፣ እየሆንነው፣ ያለነውን ነው፡፡

3. የአውራ አምባ ማህበረሰብ የአባልነት ደረጃዎች

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ሁለት ዓይነት የአባልነት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነሱም የአውራ አምባ ማህበረሰብ አዲስ ምዕራፍ ባህሪና ልማት ግንባታ ሁለገብ ማህበር (**የማህበረሰብ**) አባልና የአውራ አምባ ማህበረሰብ የገበሬዎችና እደ-ጥበባት ሁለገብ ኅብረት ስራ ማህበር (**የኅብረት ስራ ማህበር**) አባል ናቸው፡፡

3.1 የማህበረሰብ አባል

ይህ የአባልነት ደረጃ በአውራ አምባ ማህበረሰብ አዲስ ምዕራፍ ባህሪና ልማት ግንባታ ሁለገብ ማህበር በመታቀፍ፣ ማህበረሰቡ የሚመራባቸውን እሴቶችና መርሆዎች በማወቅ፣ በመተግበርና እሴቶቹንም ወደ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል እንዲስፋፉ በማድረግ የሚኖር የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ የማህበረሰብ አባል በየትኛውም የዓለም ክፍል ስራውን በተናጠል በመስራት በግሉ እየኖረ ከማህበረሰቡ መስራቾች ጋር በመወያየት በየአለበት ቦታ ሆኖ የማህበረሰቡን ራዕይና ተልእኮ እውን ለማድረግ በርትቶ የሚሰራ ነው፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ አዲስ ምዕራፍ ባህሪና ልማት ግንባታ ሁለገብ ማህበር በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ጥቅምት 8 1999 ዓ.ም ህጋዊ እውቅና አግኝቷል፡፡

3.1.1 የአውራ አምባ ማህበረሰብ ራዕይ፡- ሁሉም የሰው ልጆች እርስ በርሳቸው ተከባብረው፣ ተፈቃቅረውና ተረዳድተው የሚኖሩበት ዓለም ተፈጥሮ፣ ድህነት ከዓለማችን ጠፍቶ፣ ሁሉም የሰው ልጆች ስለሰላም ሲያስቡና ሰላም በሁሉም የዓለም ክፍሎች ላይ ተዘርግቶ ማየት ነው፡፡

3.1.2 የአውራ አምባ ማህበረሰብ ተልዕኮ፡- የአውራ አምባ ማህበረሰብ መልካም ተሞክሮዎችና እሴቶች ለሁሉም የሰው ልጆች በስፋትና በጥራት እንዲዳረሱ በማድረግ መጥፎ አነጋገሮችና አሰራሮች ተወግደው መልካም አስተሳሰብ፣ አነጋገርና አሰራር ጎልብተው ሰላም በሁሉም የዓለም ክፍል የሚሰፍንበት ዘዴ ማሳየትና በስራ ላይ ማዋል ነው፡፡

3.2 የኅብረት ስራ ማህበር አባል

ይህ የአባልነት ደረጃ ደግሞ በአውራ አምባ ማህበረሰብ አዲስ ምዕራፍ ባህሪና ልማት ግንባታ ሁለገብ ማህበር (የማህበረሰብ) አባል ከሆኑት ግለሰቦች መካከል ደካማ ከጠንካራ

በመሆን እየተደጋገፉ በመስራት ሁሉን አቀፋዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ያመች ዘንድ ጉልበቱንና ዕውቀቱን በማስተባበር የአውራ አምባ ማህበረሰብ የገበሬዎችና የእደ-ጥበባት ሁለገብ ኅብረት ስራ ማህበርን መስርቶ በጋራ ሰርቶ በማምረት ጥቅምና ጉዳቱን በጋራ ተካፋይ በመሆን የሚኖር ነው፡፡ የኅብረት ስራ ማህበሩ አባላት የቡድን መሪው እንደችሎታቸው በሚመድባቸው የስራ ምድብ በመሰማራት እምቅ አቅማቸውን ተጠቅመው በቅንነት በመስራት ወደላቀ የኢኮኖሚ እድገት ለማምራትና ድህነትን ለማጥፋት ቆርጠው የተነሱ ናቸው፡፡

የዚህ ማህበር አባላት በሙሉ የማህበረሰቡን እሴቶችና መርሆች (ደንቦች) ተቀብለው ከመስራትና ከማስፋፋት በተጨማሪ የኅብረት ስራ ማህበሩን የውስጥ ደንብ በማውጣትና ደንቡንም በማክበር በጋራ፣ በመተሳሰብ፣ በታማኝነትና በቅንነት ስራቸውን እየተደጋገፉና እየተረዳዱ እየሰሩ የሚኖሩ የማህበረሰቡ ክፍል ናቸው፡፡ የኅብረት ስራ ማህበሩ አባላት ስራዎቻቸውን በጋራ በየተመደቡበት በመስራት ደካማ ከጠንካራ ተጋግዘውና ተረዳድተው የሚሄዱበትና በኋላ የትርፍ ክፍፍል ላይም ደካማ ከጠንካራ ሳይባል እኩል ተከፋፍለውና ሁሉም እኩል ተደስተው የሚኖሩበት ሂደት ነው፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ የገበሬዎችና እደ-ጥበባት ሁለገብ ኅብረት ስራ ማህበር በአማራ ክልላዊ ብሄራዊ መንግስት የማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ የካቲት 6 2000 ዓ.ም ላይ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

3.2.1 የኅብረት ስራ ማህበሩ ራዕይ፡- የአባላትን እውቀትና ጉልበት በማስተባበር፣ ደካማ ከጠንካራ በመደጋገፍ፣ በተለያዩ የስራ ዘርፎች በመሳተፍና አዳዲስ የስራ ዘርፎችን በመፍጠር ድህነትን አጥፍቶ የማህበሩን የኢኮኖሚ አቅም በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ነው፡፡

3.2.2 የኅብረት ስራ ማህበሩ ተልእኮ፡- የማህበሩን አባላት ጠንካራ ከደካማ በማቀናጀት፣ በመረዳዳትና በመተሳሰብ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተሰማርቶና ያለውን ሁሉ እምቅ አቅም አሟጦ በመጠቀም የማህበሩን የኢኮኖሚ እድገት ወደላቀ ደረጃ በማድረስ፣ እድገቱ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ምሳሌ እንዲሆንና ምሳሌነቱም በጥራትና በስፋት ለሁሉም የሰው ልጆች ተዳርሶ ድህነት እንዲጠፋ ለማድረግ የሚያስችለውን ስልት በተግባር እየሰሩ ማሳየት ነው፡፡

4. አምስቱ የዙምራ መሰረታዊ ሀሳቦች

ዙምራ አራት መሰረታዊ ሃሳቦችን በአራት ዓመት ዕድሜው ገደማ አንስቷል፡፡ አምስተኛውን መሰረታዊ ሃሳብ ድግሞ እንዲሁ ከ18 ዓመት ዕድሜው በኋላ አግኝቷል፡፡ ዙምራ እነዚህን መሰረታዊ ሀሳቦች እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ በብቸኝነት ተሸክሚቸው ቆይቷል፡፡ በ1964 ዓ.ም ሀሳቡን የሚያደምጡ አጋሮችን ሲያገኝ መሰረታዊ ሀሳቦቹን እንዴት በማህበረሰቡ ሊተገበሩ እንደሚችሉና ሲተገበሩ ደግሞ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ በዝርዝር ሀሳቡን ለመቀበል ለተዘጋጁት ሰዎች ከራሱ የህይወት ተሞክሮ ጋር በማቀናጀት አቅርቦላቸዋል፡፡

እነዚህም መሰረታዊ ሀሳቦች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

1. የሴቶችን እኩልነት ማክበር
2. የህፃናትን መብት ማክበር
3. በጤናም ሆነ በእርጅና ምክንያት ተዳክመው ለስራ ብቁ ያልሆኑ ሰዎችንና ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችን መንከባከብ
4. መጥፎ አነጋገርና መጥፎ አሰራርን ማስወገድ (ስርቆትን፣ ሌብነትን፣ ስድብን እርግመትን፣ ድብደባን፣ ነገረኝነትን፣ ግድያን፣ ጥላቻን ወዘተ ማስወገድና ትብብርን፣ ፍቅርን፣ መረዳዳትን፣ ሰላምን በአጠቃላይ በጎ ተግባራትን ማበልጸግ)
5. የተበጣጠሰ ወገንተኝነትን ማስወገድ የሚሉት ናቸው፡፡

4.1 የሴቶችን እኩልነት ማክበር

“እናትና አባቴ ገበሬዎች ነበሩ፡፡ በእርሻ ስራ ላይ አብረው ይውላሉ፡፡ በጉልጓሎው፣ በአረሙ፣ በአጨዳው፣ በነዶው ሸክም አብረው ይውላሉ፡፡ ማታ ላይ ሲመለሱ ያባቴ ስራ ዱር ቀርቷል፡፡ የእናቴ ስራ እቤት ይቀጥላል፡፡ የእናቴ ስራ ምንድነው? ድስቱ፣ ምጣዱ፣ እንጨት ማቅረቡ፣ ውሃ መቅዳቱ፣ ልጅ ማጫወቱ፣ እግር ማጠቡ፣ ወፍጮው፣ ወፍጮው ደግሞ እንደዛሬው ዘመናዊ ወፍጮ የለም፡፡ እናቴ በእጇ ፈጭታ ነው ቤተሰቡን የምታስተዳድረው፡፡ ይህ ሁሉ ስራ የእናቴ መደበኛ ስራዋ ነው፡፡

ከመደበኛ ስራዋ ውጭ ደግሞ እለታዊ ትዕዛዞች ከአባቴ ወደ እናቴ የሚወርዱ አሉ፡፡ እነዚያን ሁሉ እያሟላች እናቴ ናት የምታከነውን፡፡ እኛ ተኝተን እሷ ሌሊቱን ስትሰራ ታድራለች፡፡ ወደ ንጋት እኛ እንደተኛን የቀኑን ደግሞ ለመስራት በሌሊቱ ተነስታ ትባዝናለች፡፡ አንድ ጊዜ ከወፍጮው አንድ ጊዜ ከምጣዱ፣ አንድ ጊዜ ከውሃው፣ ከልጆቹ የምትባክንበት ጊዜ ብዙ ይሆናል፡፡ ያ ሁሉ ሲሆን ስራው አያልቅላትም፡፡ ስራ ሲበዛና የታዘዘችበት ስራ ወደ ኋላ ሲዘገይ አባቴ ተቀምጠሽ ምን ትሰሪያለሽ? ይላል፡፡ ስድቡ፣ እርግማቱ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ዱላም ያጋጥማታል፡፡

ይህን በምመለከት ጊዜ አእምሮዬ አልፈቅድልኝ ይላል፡፡ እንዴት ነው እናቴ ትርፍ ጉልበት አላት ወይ? የቤቱ ስራ የሷ ስራ ነው፡፡ የዱሩ ስራ የሁላቸው ነው፡፡ እምንመገበው ሁላችንም ቤት ያለነው ልጆች የሁላቸውም ነን፡፡ እና እናቴ የዱሩን ስራ

እንዳገዘች ሁሉ የቤቱን ለምን አያግዛትም? የሚል ዓላማ ነው ያለኝ፡፡ ሲያቅታት ደግሞ ዱላው መምጣቱ ለምንድነው? እናቴ ትርፍ ጉልበት አላት ወይ? ባይሆን እግሩን አይታጠብላትም? እናቴን እማግዝበት ነገር አጣለሁ፡፡ ከሁሉም ቦታ ስትባክን ወፍጮው እዚያ ተዘርግቶ አያለሁ፡፡ ወፍጮ እፈጫለሁ ብዬ ስሞክር ቁመቴ አልደርስ ይላል፡፡ ድንጋይ ቀጥዬ እፈጫለሁ ያልኩ እንደሆን አልደቅልኝ ይላል፡፡ ፍሬዎቹ ይሾልካሉ፡፡ እናም አዝናለሁ፡፡

እናቴን የምረዳበት ቢኖር ትንሽዬ ኮዳ አለች፡፡ በዚያች ወንዝ እየሄድኩኝ ውሃ እያመላለስኩ ከውሃ እንስራዋ መሙላት ነው፡፡ ውሃ ልቀዳ በምሄድበት ጊዜ የአካባቢው ጎረምሶችና ማናቸውም ወጭ ወራጁ ሰው ንግግሬን በጣም ያደምጡኛል፡፡ 'ይህን በይ ይህን በይ' እያሉ እኔ ኮዳዬን ቆሜ ተሸክሜ የነሱን ትዕዛዝ አሚላለሁ ብዬ ሲያናዝዙኝ ይውላሉ፡፡ ለኔ ይኸ መከራዬ ሲሆን ለነሱ ደግሞ ሳቅና ጨዋታቸው ነው፡፡ መሳቂያና መጫወቻ ሲያደርጉኝ ይውላሉ፡፡ እና ለናቴ ውሃ በምቀዳ ጊዜ ውሃ መቅዳቱ ሳይሆን የሚያሳቅቀኝ ስወጣ የሚጋጥሙኝ ጎረምሶችና ይህን አውሪ እያሉ እያዳመጡ በመሳቅ እነሱ ሲደሰቱብኝ የሚውሉት ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ ለእኔ በነፍስና በስጋዬ ተቀርጾ ያሰቀቀኝ ነበር፡፡ ያውም ሆኖ እናቴን ለመርዳት ወደ ኋላ የምልበት ነገር የለም፡፡ ስጋቴን በውስጤ ተሸክሜ ስንቀሳቀስ ነው እምኖር የነበረው፡፡

በአጠቃላይ ይህን የወንድና የሴት የስራ ክፍፍል ሳየው የኔ እናትና አባት ችግር ብቻ ይመስለኝ ነበር፡፡ በሁሉም ቤት እያየሁ ስሄድ የሴቶችና የወንዶች አዳር አንድ አይነት ሆኖ አገኘዋለሁ፡፡ ይህ ነገር ምንድነው? ሴት በሴትነቷ እናት ናት፡፡ ወንድ በወንድነቱ አባት ነው፡፡ እናት በሌለችበት አባት የለም፡፡ አባት በሌለበት እናት የለችም፡፡ እሷ እንደሞግዚት እሱ አንደአዛዥ የሆኑበት ምክንያት ምንድነው? ሚስቶቻችን ስንል ባዕድ መስለው ከሆነ እናቶቻችን እንበላቸው፡፡ እናትና አባት እኩል መብት ያላገኙት ለምንድነው? ወንዶች ጉልበተኛ በመሆናቸው ነው? ወንዶቹ ጉልበተኛ ሁነው ከሆነ ሴቶቹን ሞግዚት ያደረጓቸው ትርፍ ጉልበታቸውን ለምን ለስራ አያውሉትም?

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ባልና ሚስቶች በሚጣሉ ጊዜ ባልየው ሚስቱን ውጭልኝ ከቤቴ፣ ቤቴን ዘግቸ እሄዳለሁ፡፡ ይልና ሴቷን በዱላም በምንም ብሎ ቤቱን ዘግቶባት የሚሄድ እናት ያለችን መሆኑን ነው እማውቀው፡፡ እናም አዕምሮየን ይጎዳኛል፡፡ አሁንም ሴት በሴትነቷ እናት መሆን አለባት ወንድ በወንድነቱ አባት መሆን አለበት፡፡ እኩል መብት ማግኘት አለባቸው፡፡

ሴቶች የሚሰሩትን ስራ ሁሉ እኛ ወንዶች መስራት እንችላለን፡፡ ሴቶችም ወንዶች የሚሰሩትን ስራ መስራት ይችላሉ፡፡ ሴቶች ከወንዶች የሚለዩት ተፈጥሮ በለገሳቸው ማርገዝ፣ መውለድና ማጥባት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት በተለምዶ የወንድ ስራ ተብለው የሚታወቁትን ሴቶችም ሊሰሩት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የሴት ስራ ተብለው የሚታወቁትንም ስራዎች ወንዶች መስራት ይችላሉ፡፡ ሴት የወንድ ስራ ብትሰራ ያባቷ ስራ ነው፡፡ ወንድም የሴት ስራ ቢሰራ የእናቱ ስራ ነው፡፡ ስለሆነም የወንድ ስራና የሴት ስራ የሚለውን ጾታዊ የስራ ክፍፍል አስወግደን ሁላችንም በችሎታችን በየስራ ዘርፉ በመሰማራት ሴቶች እንደ ሞግዚት ሆነው የሚማስኑበትን ስራ ሁሉ እኛ ወንዶችም ተሰማርተን ማገዝ ይኖርብናል፡፡

እኔ የትዳር ጓደኛዬ በምትወልድ ጊዜ የደም ጨርቅና የሽንት ጨርቆችንም እያጠብኩና ዘመናዊ ወፍጮ በሌለበት ጊዜ በእጄ ፈጭቼ አቡክቼ ጋግሬ እኔንም ልጆቼንም የትዳር ጓደኛየንም አስተዳድራለሁ፡፡ ሌላውንም የቤቱን ስራ ሁሉ እየሰራሁ አርሳታለሁ፡፡ ከትዳር ጓደኛዬ ጋር በቤታችን ይህ የወንድ ስራ ይኸኛው ደግሞ የሴት ስራ ነው ብለን በጾታችን ተከፋፍለን ሳይሆን እምንሰራው ችሎታችንን መሰረት አድርገን ነው፡፡ እኔ የሴት ስራ በመስራቴና የትዳር ጓደኛየም የወንድ ስራ በመስራቷ ፆታችን አልተቀየረም፡፡

የተቀየረ ነገር ቢኖር መሀይምነታችን ነው፡፡ በጥቅሉ በኔና በትዳር ጓደኛዬ መካከል በስራ፣ ሀብትን በማስተዳደር፣ ለምንሰራው ስራ ተወያይተን ውሳኔ በመስጠት፣ እኩልነትን መስርተን ነው እምንኖረው፡፡”

4.2 የህፃናት መብትን ማክበር

“ህጻናት እግረ- ተከል ከሆኑ ጀምሮ አቅማቸውን ያላገናዘበ ስራ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚያ አቅማቸው አልፈቀደ ሆኖ ያ ስራ ሲጠፋባቸው፣ ሲበላሽባቸው ለምን አጠፋህ? ለምን አበላሽህ? የሚል ነው፡፡ አቅማቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ የስሜት ማውጫ ነው እሚሰጣቸው፡፡ ያን ጊዜ ለምን ህይወት አይደለም? አቅማቸውን ያላገናዘበ ስራ መሰጠቱ ለምን? እላለሁ፡፡

ወላጆቻችን እኛን ትምህርት አላስተማሩንም፡፡ ወላጆቻችን እኛን ባለማስተማራቸው ጎድተውናል፡፡ እኛ ደግሞ ይህንን በልጆቻችን ላይ መድገም የለብንም፡፡ እኛ ለልጆቻችን የምንሰጣቸውን ስራ እየሰራን እነሱን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ይኖርብናል፡፡ ልጆቻችን መብታቸው ተጠብቆ ማደግ አለባቸው፡፡ ከትምህርት ጊዜያቸው ውጭ አቅማቸውን ያገናዘበ ስራ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ስራ እየሰጠናቸው ስራውን መስራት ባይችሉ ስድቡን፣ እርግመቱና ዱላውን እናስከትላለን፡፡ ይህ መሆን የለበትም፡፡ አቅማቸውን ያገናዘበ ስራ ግን ከቀለም ትምህርቱ በተጨማሪ የተግባራዊ ስራን ምንነት ከልጅነታቸው ጀምሮ ለምደውት እንዲያድጉና ስራ ወዳድ እንዲሆኑ ለማድረግ ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡ በጎ አስተሳሰብን ይዘውና ጎጅ ባህሎችን ጠልተው እንዲያድጉ የዘወትር ክትትልና ምክር መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ሀሳባቸውንም ሳንንቅ በእኩል እይታ ተቀብለን በጎ ከሆነ በማበረታታት ስተት ካለበት ደግሞ ታግሰን በማስተማር መልካም ትውልድ መፍጠር ይኖርብናል፡፡”

4.3 በእርጅና ሆነ በጤና እጦት ለስራ ብቁ ያልሆኑ ደካሞችን መንከባከብ

ዙምራ ከ4 ዓመት እድሜው ጀምሮ ከሚያነሳቸው መሰረታዊ ሀሳቦች አንዱ በጤና እጦትም ሆነ በእርጅና ምክንያት ለስራ ብቁ ያልሆኑ አቅመ-ደካሞችን መርዳት ነው፡፡ ይህንም እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡፡

“የወደቁ ደካሞች በጤናም ሆነ በእርጅና ከስራ ተፈናቅለው በየሜዳው ወድቀው ይበሉት ይጠጡት ያጡ ሆነው አያለሁ፡፡ ጠንካራው ከጠንካራው ጋር አብሮ ስቆ ተጫውቶ በልቶ ጠጥቶ ሲወጣ ደካሞችን የሚያስባቸው የለም፡፡ ደካሞች እንደኛ ሰው ናቸው፡፡ መስራት አቅቷቸው ተሰናክለው ወድቀው እንጅ እኛ እንደምንበላው እንደምንጠጣው እነሱም መብላት መጠጣት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ያንን እንዲያገኙ አቅም የላቸውም፡፡ እኛ ጥለናቸው ከሄድን ማን ይደርስላቸዋል? ***ለሰው ደራሹ ሰው ነው ሌላ ማን ይመጣለታል****? እኛ ጥለናቸው ከሄድን እኛም አንድ ቀን እንወድቅ ይሆናል፡፡ በምንወድቅ ጊዜ እሚያስበን እንፈልጋለን፡፡ እኛ እሚያስበን እንደምንፈልግ ሁሉ ለምን እነሱን ጥለናቸው እንራመዳለን?”*

ይህንን መሰረታዊ ሀሳቡን ተግባር ላይ ማዋል የጀመረው ሀሳቡን የሚጋራው ህብረተሰብ ፍለጋ ከ13 ዓመት እድሜው ጀምሮ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡ ዙምራ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በሚሄድበት ቦታ ሁሉ የሚያጋጥሙትን በእረጅናም ሆነ በህመም ምክንያት ለስራ ብቁ ያልሁኑ ሰዎችን ያለውን አቅም ሁሉ አሟጦ ማህበረሰብ መመስረት እስከቻለበት ጊዜ ድረስ በመርዳት ሲታደጋቸው ኖሯል፡፡

4.4 መጥፎ አነጋገርና መጥፎ አሰራርን ማስወገድ

ዙምራ 4ኛ መሰረታዊ ሀሳቡን እንዲህ በማለት ለሰዎቹ አካፍሏቸዋል፡፡

"ሰውን ሰው ሲሰድበው፣ ሲረግመው፣ ሲዋሸው፣ ሲሰርቀው፣ ሲቀማው፣ ሲመቀኘው፣ ሲደበድበው፣ አልፎ አልፎም ሲገድለው አያለሁ፤ እሰማለሁ፡፡ እነዚህ ደግሞ መጥፎ አሰራርንና መጥፎ አነጋገርን የሚያመላክቱ በመሆናቸው ማስወገድ ይኖርብናል፡፡ እነዚህን መጥፎ ድርጊቶች አስወግደን በምትካቸው በጎ ምግባሮችን ማለትም ትብብርን፣ ታማኝነትን፣ ፍቅርን፣ መረዳዳትን፣ ሩህሩህነትን፣ ቀናነትን፣ ሐቀኝነትን፣ ሰላምንና ማበልጸግ ይኖርብናል፡፡

1. ***ሌብነት (ስርቆት)፡-*** *ሌብነት ማለት የራስ ያልሆነን ንብረት ወይም ጉልበት መውሰድ ወይም መዝረፍ ወይም ለግል ጥቅም ማዋል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በራስ ላይ እንዲደርስ የማይፈለግ ተግባርና ሌላው ንብረቱን ለማፍራት በስራ ሲታገል የኖረበትን ቁጭ ብሎ ከርሞ በመውሰድ ሰውን ከሰው ከትልቁ ገንዘብ ጋር የሚያናቁር፣ ሰላምን የሚያናጋ፣ ለሀገር እድገት እንቅፋት የሚሆን፣ ህሌናንም ረፍት የሚነሳና በሚያልቅ ገንዘብ የማያልቅ የሌብነት ስም ሰጥቶ የሚሄድ ስለሆነ እንዲወገድ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡*

2. ***ውሸት፡-*** *ማለት የሆነውን አልሆነም፣ ያልሆነውን ሆኗል፣ ያለውን የለም፣ የሌለውን አለ በማለት የተሳሳተ መረጃ መስጠት ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተግባብቶና ተማምኖ ለመኖርና ወደ እድገት ጎዳና ለመሄድ ቀንደኛ እንቅፋት ነው፡፡ በጥቅሉ ውሸት የማህበራዊ ኑሮን ቀውስ የሚያስከትል ስለሆነ እንዲጠፋ ማድረግ ነው፡፡*

3. ***ነገረኝነት፡-*** *ማለት የተሰራውን እንዳልተሰራ፣ ያልተሰራውን አንደተሰራ፣ አድርጎ አስመስሎ በማውራት ሰውን በሀሰት በሌለበት መወንጀል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሀገርና ለወገን በጎ አሳቢዎችንና ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሰዎችን ያሳጣል፡፡*

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ሀሳቦች በመተግበር በራሳችን ላይ እንዲደረግልን የምንፈልገውን ነገር ሁሉ በሰዎች ላይ እንዲደረግላቸው ማድረግና በሰዎች ላይ እንዲደርስባቸው የማይፈለጉ መጥፎ ድርጊቶችን በሰዎች ላይ እንዳይደርሱ ማድረግ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ማንም ሰው መጥፎ ድርጊቶች በራሱ ላይ እንዲደርሱበት የሚፈልግ የለም፡፡ በጎ ነገሮችም ከራሱ ላይ ቢርቁት እንዲሁ አይፈልግም፡፡ ስለሆነም እነዚህን መጥፎና በራሳችን ላይ እንዲደርሱብን የማንፈልጋቸው መጥፎ ድርጊቶች ሌሎች ሰዎችም እንዳይደርሱባቸው ማድረግና በሰው ልጆች ላይ እንዲደረጉ የሚፈለጉትን በጎ ምግባሮች ሁሉ እንዲስፋፉ እያደረግንና እኛ በተግባር እየተረጎምን የሰው ልጆችን ማስተማር ይጠበቅብናል፡፡ በራሳችን እንዲደርስብን የማንፈልገውን በሰዎች ላይ

የምናደርግ ከሆነ ከሌሎች እንስሳት የተሻልንበት ነገር ምንድነው? ሌሎች እንስሳት እንስሳት የተባሉት ጎጅና ጠቃሚውን ኢያውቁም፣ በእቅድ ኢይመሩም፣ ቀምተው ይበላሉ፣ ይገሉታል፣ ሲወድቅ ጥለውት ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ ወገናቸውን ባለማሰባቸው እንስሳት ይባላሉ፡፡ እኛም ለወገኖቻችን ብለን የማናዝን ከሆነ፣ ሊደረግብን የማይገባውን በወገኖቻችን ላይ የምናደርግ ከሆነ ከሌሎች እንስሳት የተሻልንበት ነገር ምንድነው? ያን ጊዜ ሰው እንደሚያስበው አይደለም እምታስበው፡፡ ሰው እንደሚሰራው መስራት አልፈለክም፡፡ "እማይወጣ ጥጃ ከማሰሪያው ይታወቃል" ይባላልና ዛሬ ይኸን እምታስብ ከሆነ ነገ ምን እንደምትሰራ አናውቅም፡፡ ለነገሩ ወደህ አይደለም ታመህ ነው፡፡ አሞህ ነው፣ ታመህ ነው ሲሉኝ እውነት አሞኝ ነው? ብዬ እራሴን እጠይቃለሁ፡፡ እራሴን በምጠይቅ ጊዜ እመሜን አጣለሁ፡፡ እንተሳሰብ፣ እንተዛዘን ነው ያልኩት እመሜ ከምን ላይ ነው? ታሞ እየተባልኩ ከወላጆቼ ጋር አብሬ ለብዙ ዓመታት ቆይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ሀሳቦች ያነሳኋቸው በ4 ዓመት እድሜዬ ነው፡፡ እነዚህ ሀሳቦቼም እናንተን እስካገኘሁበት ጊዜ ድረስ ከሰዎች እንድለይና ባይተዋር እንድሆን ያደረጉኝ ሲሆኑ በራሴ ተግባራዊ ሳደርጋቸው ቆይቻለሁ፡፡"

4.5 የተበጣጠሰ ወገንተኝነትን ማስወገድ

"ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ሀሳቤን የሚጋራኝ ህብረተሰብ ሳጣ ተመልሼ ከወላጆቼ ጋር ተደባልቄ ትዳር ልይዝ ነው ሴት ፈልጉልኝ ስላቸው ደስታ ተሰማቸው፡፡ አብዶ፣ ታሞ፣ ከቦታ ቦታ እየዞረ ሲሉ የነበሩት ትዳር ልይዝ ነው ብዬ ስላቸው ትዳር ካሰበ በሽታው ለቆት ነው፡፡ በሽታው ባይለቀው ኖሮ ትዳር አያስብም ነበር የሚለውን ያስቡና ደስ ብሏቸው ወዲያው ሴቷን ፈለጉልኝ፡፡ እኔም ትዳሬን መስርቼ እንደ ወላጆቼ እርሻ እያረስኩ በየዓመቱ ያገኘኋትን ምርት በአካባቢው ለሚገኙ ደካሞች ማከፋፈል ጀመርኩ፡፡ ይህን በማከፋፍል ጊዜ አይ አይድንም የሚድን በሽታ አይደለም፡፡ እሱ አይበላም፣ አይለብስም፣ አይጠጣም፣ አልታደለም፡፡ የሱን ገንዘቡን ዘመድ አያገኘውም፡፡ ለባዕድ ነው እሚሰጠው አሉ፡፡

እዚህ ላይ ለኔ አንድ ግርምት ነው፡፡ ከሰው ልጆች ላይ *ባዕዱ ማንነው? ባዕድ እምትሉት የትኛውን ነው? ዘመድ እምትሉትስ የትኛውን ነው? በኔ በኩል ነጭም ሆነ ጥቁር ራሱን ነጭ ወይም ጥቁር አድርጎ የፈጠረ የለም፡፡ ነጭ ጥቁር ማድረግ የፈጣሪ ስራ ነው፡፡ ነጭ ጥቁር ማድረግ ሰውን ብቻ አይደለም፡፡ እንስሳትንም መሬትንም ብንወስድ ነጭ ጥቁር ማድረግ የፈጣሪ አሰራር ነው፡፡ ሰዎች በሰውነታችን ግን የአንድ አዳምና ሄዋን ልጆች የአንድ ሀረግ ፍሬዎች ነን፡፡ የአዳም ዘር ሳይቀየር ባዕድነት በየት አልፎ ገባ?* የሚል ጥያቄ ነው እምጠይቅ፡፡ ይህን በምጠይቅ ጊዜ አሞህ እኮ ነው ባዕድና ዘመድ *መለየት ያቃተህ ታመህ ነው፡፡ ብታውቅ! አንተ ሁሉን ዘመድ አድርገህ የምትኖረው አሞህ ነው፡፡ ከሰባት ትውልድ በኋላ ያለው ባዕድ ነው* አሉ፡፡

እዚህ ላይ ደግሞ ለኔ ሌላ ግርምት ነው፡፡ *ሰባት ትውልድ ከደረሳችሁ በኋላ ባዕድነት ትፈጥራላችሁ ያለው ማነው? ባዕድነትን እንፈጥራለን፡፡ ባዕድነት ጥላቻን፣ ጥላቻ ጠብን፣ እየፈጠረ ሰውን ሰው እንደ አውሬ እየፈራው እምንሄደው* እኛው እምንስለው ነው፡፡ እህቴ ወንድሜ ብለን ብንሄድ ኖሮ ልዩነት ባልሰፋ ነበር የሚለውን አስብና በሀሳብ ብቻየን ነኝ፡፡

አምስተኛውን መሰረታዊ ሃሳቤን በዚህ ሁኔታ ነው ያነሳሁት፡፡ ሁላችንም የሰው ልጆች ነጭም ሆነ ጥቁር ያለምንም ልዩነት እህት ወንድም ሆነን፣ የተበጣጠሰ ወገንተኝነትን በማስወገድና ጥቅል ወገናዊነትን በማስፈን በመካከላችን መተማመን፣ መተሳሰብና መረዳዳት ተለምዶ የሰላምና የፍቅር ኑሮን እንዲሰፍን ማድረግ አለብን፡፡"

5. የአውራ አምባ ማህበረሰብ አኗኗር

5.1 መዋቅራዊ አደረጃጀት

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ራዕዩንና ተልኮውን ለማሳካት ያመቸው ዘንድ በአንድ ዐብይ ኮሚቴና በ12 ንዑሳን ኮሚቴዎች ይመራል፡፡



የማህበረሰቡ መዋቅራዊ አደረጃጀት

5.1.1 የልማት ኮሚቴ፡- አምስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ኃላፊነትም በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎችና ሁሉንም ንዑሳን ኮሚቴዎች የመከታተልና ማስተባበር ነው፡፡

5.1.2 ሳምንታዊ የልማት ኮሚቴ፡- አምስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር በየሳምንቱ ማክሰኞ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት የሚሳተፉበት የገቢ ማስገኛ የልማት ቀን የሚሰሩ ስራዎችን፣ የተገኙ ገቢዎችን ይከታተላል፤ ያስተባብራልም፡፡

5.1.3 እንግዳ ተቀባይ ኮሚቴ፡- አራት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የከሚቴው ተግባር ማህበረሰቡን ለመጎብኘትና የማህበረሰቡን መልካም ተሞክሮዎች ለመጋራት የሚመጡ እንግዶችን ማስተናገድ፣ ተሞክሮዎቹን ማካፈል ነው፡፡

5.1.4 ደንብ አውጭ ኮሚቴ፡- አስራ አምስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር ማህበረሰቡ የሚመራባቸውን ደንቦች ማውጣት፣ መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ማሻሻልና አፈጻጸማቸውንም መከታተል ነው፡፡

5.1.5 ወድቆ የተገኘ ገንዘብ አስቀማጭ ኮሚቴ፡- ሦስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ኃላፊነት በማንኛውም ቦታ ወድቀው በማህበረሰቡ

አባላት የተገኙ ንብረቶችን /ገንዘቦችን/ ገንዘቡን ያገኘው ሰው ማን እንደሆነ፣ የት ቦታና መቼ እንደተገኘ መረጃዎችን መዝግቦ መያዝና ገንዘቡን የኔ ነው ባይ ከመጣና አሳማኝ መረጃ ካገኘ ለባለቤቱ ተመላሽ ያደርጋል፡፡ የኔ ነው ባይ ከሌለው ደግሞ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ይደረግ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ለወገን ደራሽ ለሆነው ድርጅት ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

5.1.6 የአረጋዊያን ተንከባካቢ ኮሚቴ፡- አምስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር በማህበረሰቡ እንክብካቤ የሚደረግላቸውን አረጋዊያን የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ በየጊዜው የልብ ትርታቸውን እያዳመጠና እየተከታተለ እንዲሟላላቸው ማድረግ ነው፡፡

5.1.7 የህመምተኛና አራስ ተረኛ መዳቢ ኮሚቴ፡- አምስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር በማህበረሰቡ ውስጥ የታመሙ ሰዎችና የወለዱ ሴቶች ሲኖሩ ተረኞችን በመመደብ በቤት ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፡፡

5.1.8 ችግር አጥኚና መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ፡- ሦስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የከሚቴው ተግባር በማህበረሰቡ ውስጥ ችግር የደረሰባቸው ሰዎች ካሉ ጥናት ማደረግና ለሳምንታዊ የልማት ኮሚቴ በማቅረብ ለችግረኞቹ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፡፡

5.1.9 ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፡- ሶስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር በማህበረሰቡ አንዳንድ ጥቃቅን ችግሮች /አለመግባባት/ ቢከሰቱ አለመግባባቱ የተከሰተባቸውን ሰዎች ዕለት በዕለት በማወያየት ችግሩን እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡ ይህ ችግር ከኮሚቴው አቅም በላይ ከሆነ ኮሚቴው ለጠቅላላ አባላቱ ያቀርብና ችግሮቹ በጠቅላላ አባላቱ እንዲፈቱ ማድረግ ነው፡፡

5.1.10 ጸጥታ ኮሚቴ፡- ሦስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር የአካባቢውን (የሰፈሩን) ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ እንደተከበረ እንዲኖርና በአንዳንድ ቀማኞች የማህበረሰቡ ሀብትና ንብረት እንዳይዘረፍ የሰፈሩን አባላት በየአቅጣጫው በመመደብ የአካባቢውን ደህንነት እንዲጠበቅ ማደርግ ነው፡፡

5.1.11 የትምህርት ኮሚቴ፡- አምስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር የመማሪያ ቁሳቁሶችን ማሟላት፣ የመዋዕለ ህፃናት ት/ቤቱን በአግባቡና በተገቢው መልኩ እንዲያዙ ማድረግ፣ ህፃናት ፊደል እንዲቆጥሩና በጥሩ ስነ-ምግባር

ታንጸው ወደ መደበኛ ት/ቤት እንዲገቡና ጎልማሶችም ለትምህርታቸው የጠነከረ ትኩረት ሰጥተው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡

5.1.12 ጤናና የጽዳት ኮሚቴ፡- ሦስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ የኮሚቴው ተግባር የአካባቢው ጽዳት ጎድሎ ማህበረሰቡ ለተለያዩ በሽታዎች እንዳይጋለጥ ማህበረሰቡን በማስተባበር ጽዳቱ እንዲጠበቅ ማድረግና አካባቢውን በመቃኘት (በመከታተል) ጽዳቱ እንዲጠበቅ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

5.1.13 የመስክ ስራ መዳቢ ኮሚቴ፡- ሦስት የስራ አስፈጻሚ አመራር አባላት አሉት፡፡ ከልማት ኮሚቴ የሚወርዱለትን የስራ እቅድ የማስተባበር፣ የማህበረሰቡን አባላት በየስራ መስኩ እንደችሎታቸው መመደብና ስራው በተገቢው መልኩ እየሄደ መሆኑን መከታተል ነው፡፡

5.2 የቤት አሰራርና አያያዝ

የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት ከ1964 ዓ.ም እስከ ከ1978 ዓ.ም ድረስ ከተለያዩ ጎረቤታማ ቀበሌዎች በተበታተነ መልኩ ነበር ሲኖሩ የነበረው፡፡ በዚህ ጊዜ የማህበረሰቡ አባላት የመጠለያ ጎጆ አሰራር በአካባቢው ከሚኖረው የገበሬ ማህበረሰብ ምንም ዓይነት ልዩነት አልነበረውም፡፡ የማህበረሰቡ አባላት መጠለያ ጎጆዎች እንደማንኛውም የገጠር ገበሬ ነዋሪ ከእንጨት፣ ከጭቃና ከሳር የተሰሩ የክብ ቤቶች ነበሩ፡፡ ከ1978 ዓ.ም ወዲህ የማህበረሰቡ አባላት በአንድ ላይ ተሰባስበው ማህበር ፈጥረው መኖር ከጀመሩ በኋላ ግን የክብ መጠለያ ጎጆ አሰራር ወደ ሰቀላ (አሞራ ክንፍ) ቤት አሰራር ተቀየረ፡፡ የሰቀላ ቤቶቹ የሚሰሩት ከእንጨት፣ ከጭቃና ከሳር ነው፡፡ የቤት አሰራሩ ወደ ሰቀላ ቤት መቀየር ያስፈለገው ወጭን ለመቆጠብ፣ የደን መራቆትን ለመቀነስና ለውስጥ የቤቱ የተለያዩ ማስዋቢያ ስራዎች ምቹ እንዲሆን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

የሰቀላ ቤት (ከ1993 ዓ.ም በፊት)

ማህበረሰቡ በመፈነቃቀል በነበረበት ጊዜ ከደረሰበት ዘርፈ ብዙ ውስብስብ ችግሮች የተነሳ ለጎጆ መስሪያ የሚሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት ባለመቻሉ ደሳሳ ጎጆዎቹ እንደነገሩ ከጊዜው ዝናብና ፀሀይ በከፊል ለመከላል ያህል ተደርገው ነበር የተሰሩት፡፡ እነዚህ ጎጆዎች የቆሎ ተማሪ መጠለያ የሚመስሉ ሆነው ግድግዳቸው ጨፈቃ ሲሆን ጣራቸው ደግሞ ከአባሎ ቅጠል የተከደነ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ከዝናብ ፍሳሽ የሚከላከሉ አልነበሩም፡፡ በጎጆው ውስጥ የሚንጠባጠበውን ፍሳሽ ለመቀነስ ጣራቸው የሚሰራው ወደታች ገደል ተደርገው ነበር፡፡ ጎጆዎቹ ለተለያዩ የቤት ውስጥ አደረጃጀት አመቺ በሆነ ሁኔታ የተከፋፈሉ አልነበሩም፡፡ ምድጃው፣ መኝታው፣ ሳሎኑ፣ እቃው ሁሉ የሚትርመሰመሰው በዛችው ከዝናብ ፍሳሽ ከማታድን በአንዲ በጠባቧ ክፍል ላይ ነበር፡፡

ከተወሰኑ ዓመታት ቆይታ በኋላ ማህበረሰቡ በኢኮኖሚ በተወሰነ ደረጃ ሲለወጥ እንደገና እርስበርሳቸው የተያያዙና ስፋታቸውም የተሻሉ የሰቀላ (አሞራ ክንፍ) ጎጆዎች መስራት ቻለ፡፡ ጎጆዎቹ ከውጭ በኩል ሲታዩ ለእይታ የማይስቡ ቢሆኑም ውስጣቸውን ሲያይዋቸው ግን ከዘመናዊ የከተማ ቤቶች ውበትና አደረጃጀት ያልተናነሱ ነበሩ፡፡ ጎጆዎቹ ውስጣቸው በጭቃ በደንብ ይመረግና አመድና እበትን በመቀላቀል ተለቅልቀው ውበታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በቤቶቹ ውስጥ የተለያዩ ለዓይን የሚማርኩና በጽዳት የተያዙ የመኝታ ክፍል፣ የእቃ፣ ክፍልና የሳሎን ክፍሎች የተከፋፈሉ በመሆናቸው ውበታቸውንና ጽዳታቸውን እንዲጎላ ያደርገዋል፡፡

የመኝታ ክፍሉ ከድንጋይ ከእንጨትና፣ ከጭቃ የሚሰራ የሞዝቦልድ ቅርፅ ያለው አልጋ ይኖረዋል፡፡ ፍራሹም በቀጭን በቀጭኑ ከተተለተለ የበቆሎ ሽልቃቂ ገለባና ከማዳበሪያ ይዘጋጃል፡፡ አልጋው በአባላቱ እጅ በተሰሩ አልባሳት እንዲለብስ ይደረጋል፡፡ በኋላም በጣም ውብና ማራኪ የአልጋ ክፍል ይሆናል ማለት ነው፡፡

የእቃ ክፍሉ በቤት ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ዕቃዎች በዓይነት- በዓይነት በመከፋፈል ለመያዝ በሚያስችል መልኩ በስርዓት ተደርድረው እንዲቀመጡና መደርደሪያ የሚያስፈልጋቸው እንዲሁ በአካባቢው በሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም መደርደሪያዎቹን በማዘጋጀት እቃዎቹ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይቀመጣሉ፡፡

ሳሎኑ የተለያየ ድዛይን ያላቸው ሶፋ የመሰሉ ወንበሮች ከእንጨት፣ ከድንጋይና ከጭቃ፣ ይዘጋጁና ማዳበሪያ እንዲለብሱ ይደረጋሉ፡፡ በዚሁ ክፍል የምግብ ማቅረቢያ፣ ውሃ መጠጫና የመሳሰሉት ዕቃዎች የሚቀመጡበት መደርደሪያ ከእንጨትና ከጭቃ በማዘጋጀት እቃዎቹ ውበትን በሚያጎናፅፍ መልክ ተደርድረው እንዲቀመጡ ይደረጋሉ፡፡

ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ

ሌላው በሳሎን ውስጥ የሚገኘው ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ነው፡፡ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃው የክቡር ዶክተር ዙምራ ፈጠራ ነው፡፡ የክቡር ዶክተር ዙምራም ማገዶ ቆጣቢ ምድጃውን እንዴት እንደሰራው እንዲህ ሲል ተናግሯል፡፡

የወላጆቻችን ምድጃ ሳሎን ላይ ሆኖ በሶስት ጉልቻ ነው እሚጣደው፡፡ እሳቱን ንፋስ ሲያግለበልበው ሙቀቱን ለተጣደው ነገር አይሰጥም፡፡ ሙቀቱን ለተጣደው ነገር ለማምጣት ሲባል ብዙ ማገዶ ይገባል፡፡ የገባው ማገዶም ብዙ ጢስና ነበልባል ያወጣል፡፡ ጢሱና ነበልባሉ ደግሞ አብሳዮቹን ይጎዳል፡፡ የተጣደውም ነገር ሲወጣ ብዙ ረመጥ ስላለው ልጆችን ለአደጋ ያጋልጣል፡፡

ወለል ላይ ያለው ምድጃ ልጆችን ለአደጋ እንዳያጋልጥ፣ አብሳዮችንም እንዳይጎዳ፣ አመዱ ሳሎኑን እንዳያበላሸውና ብዙ እንጨት እንዳይፈጅ ምድጃውን አልጋ ላይ ብሰቅለው አይሻልም ወይ ብዬ በማሰብ አልጋ አበጅቼ አልጋውን ከአፈር በተዘጋጀ ጭቃ መረግሁና ምድጃውን አልጋው ላይ ሰቅዬ ነፋስ እንዳይገባ ዙሪያውን ክብ ሰርቼ ለማገዶው ማስገቢያ ብቻ ክፍት ቦታ አስቀረሁለት፡፡ ከዚም ምጣዱን ሰቅዬ ማገዶውን በክፍቱ ቦታ አስገብቼ እሳቱን አንድጄ እንጀራውን ለመጋገር ስሞክር ጢሱ መውጫ አጣና በማገዶ ማስገቢያው ክፍተት ዞሮ መጣ፡፡ ጢሱ ሲያፍነው እሳቱ አልነድ አለ፡፡ ይህ ሲሆንብኝ ጢሱን በየት በኩል ባስወጣሁት ብዬ አሰብኩና ለጢሱ መውጫ በአንድ በኩል ሽንቆርኩለት፡፡ ጢሱም በተሸነቆረው ቀዳዳ እየወጣ ጣራውን ሁሉ በትቀርሻ አቆሸሸው፡፡ ጣራው እንዳይቆሸሽ ጢሱን ወደ ውጭ ማስወጣት እንዳለብኝ አምኜ ጢሱን ወደ ውጭ ቱቦ በማዘጋጀት እንዲወጣ አደረኩት፡፡

ከዚያ በኋላ ከጭቃ የተሰራውን ምድጃ እሳቱ እየበላ አስቸገረኝ፡፡ ይህ ሲሆንብኝ ደግሞ ቆም ብዬ አሰብኩና እሳት እማይበላው ነገር ምንድነው? ብየ እራሴን በመጠየቅ አመድ አንዴ ነዶ ካበቃ በኋላ እንደማይቃጠል አወቅኩኝ፡፡ ታዲያ ለምን በአመድ አልሰራውም? ብየ አመዱን አቡክቼ ለመስራት ስሞክር አመዱ እየቀለጠ አልቆምልኝ አለ፡፡ ለዚህም ትንሽ አፈር ከአመዱ ጋር ቀላቅየ ሰራሁት፡፡ በኋለም ለመጠን እንዲመቸኝ 3 እጅ አመድና 1 እጅ አፈር በማድረግ ምድጃውን ሰራሁት፡፡

የክቡር ዶክተር ዙምራ ምድጃውን በዚህ ምጥጥን ሲሰራው በእሳት እንዳይበላ አድርጎታል፡፡ የማገዶ ቆጣቢ ምድጃው የምጣድ መጣጃና የድስት መጣጃዎች ለየብቻ ይሰራሉ፡፡ የምጣዱና የድስቱ የጭስ መውጫ ቱቦዎች በአንድ ቱቦ እንዲገናኙ ተደርገው ጭሱን ወደ ውጭ በማስወጣት በቤት ውስጥ እየተትመሰመሰ እንዳያፍንና የቤት ውስጡን ንፅህና እንዳያበላሽ ይደረጋል፡፡ የጭስ መውጫው ቱቦው ከግድግዳው ጋር በሚገናኝበት በኩል ግድግዳውን እሳቱ እንዳይበላው ድንጋዮችን ከለላ በማድረግ ይዘጋጃል፡፡

የድስቱንና የምጣዱን ጭስ በአንድ ተገናኝቶ እንዲወጣ ከሚያደርገው ቦታ ትንሽ ከፍ ብሎ አንድ ቀዳዳ ይኖራል፡፡ ይህ ቀዳዳ አብዛኛውን ጊዜ ተዘግቶ ነው እሚቀመጠው፡፡ ቀዳዳው 3 ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1. እንጀራ በሚጋገርበት ወይም ወጥ በሚሰራበት ጊዜ ውሃ ማሞቅ ቢያስፈልግ ውሃ ከቀዳዳው ላይ አድርጎ ለማሞቅ
2. የጭስ መውጫ ቱቦው በፀዳል ከተሞላ ጭሱን ስለሚዘጋው በቀዳዳው ጨርቅ የተጠመጠመበት እንጨት በማስገባት ፀዳሉን ለመጥረግ
3. በክረምት ወቅት ቤቱ በሚቀዘቅዝበት ጊዜ ቀዳዳዋን በመክፈት ሙቀትን ለመጨመር፡፡

ይህ የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ አሰራርና አጠቃቀም ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ በማህበረሰቡ ሲሰራበት የቆየ ነው፡፡

ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ

ጭስ መውጫ

የማህበረሰቡ የቤት አሰራር ሂደት በዚህ ተወስኖ እሚቀር አይደለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ በፊት ከነበረው በተሻለ መልኩ የቆርቆሮ ቤቶች እየተሰሩና የጭስ ቤቶችም ራሳቸውን ችለው ተለይተው ተሰርተው የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ተሰርቶባቸው እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡ ይህ መሻሻል የመጣው ማህበረሰቡ በሚዲያ መታወቅ ከጀመረ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ነው፡፡ ከዚያ በኋላም በየዓመቱ ከፍተኛ መሻሻል እየታየ ነው ያለው፡፡ ወደፊት ማን ያውቃል? ማህበረሰቡ በዚህ ሁኔታ ከሰራ የማይደርስበት ነገር የለም፡፡

አሞራ ክንፍ ቤቶች (በ2000 ዓ.ም)

የቆርቆሮ ቤቶች (2003 ዓ.ም)

5.3 የስራ ባህል

ማህበረሰቡ ከተመሰረተ ጊዜ አንስቶና ከስደት እስኪመለስ ድረስ የሚተዳደረው በእርሻ ስራ ነበር፡፡ ከስደት መልስ ግን ህይወቱን ሲመራበት የነበረውን የእርሻ ስራ በመሬት እጥረት ምክንያት ለመቀጠል አልቻለም፡፡ ይህንንም ለመቅረፍ በተለያዩ የሙያ መስኮች በመሰማራት ህይወቱን ለመምራት ሞከረ፡፡ ከእነዚህም ዋናው ባህላዊ የሽመና ስራ ነው፡፡ ምንም እንኳ ትርፋማ ባይሆንም ሁሉንም የማህበረሰብ አባላት በስራ አሳትፎ የኢኮኖሚ ምንጭ የነበረው የሽመና ሙያ ነው፡፡ ሆኖም ማህበረሰቡ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ኑሮ ለማምለጥ ሳይችል ለብዙ ዓመታት ቆይቷል፡፡

ማህበረሰቡ ኑሮውን ለማሸነፍ በሸክላ ስራና ብረት የመቀጥቀጥ ስራን ለመልመድ ሞክሯል፡፡ በዚህን ጊዜ አንዳንድ ከአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች ነበሩ፡፡ "እነሀ ሰዎች ፊትም አላማረባቸው፡፡ ደሞ ብለው- ብለው ብረት የመቀጥቀጥንና የሸክላ ስራን ጀመሩ? ባለ-እጅ ሆኑ? እንግዲህ ከነዚህ ሰዎች ጋር አንጋባም" አሉ፡፡ ዙምራም "እንኳንም ባለ-እጅ ሆንን፡፡ እኛም ብትፈልጉ እጅ የሌለው አናገባም፡፡ ባለ-እጅ ማለት ሰራተኛና አምራች ማለት ነው፡፡ እኛ ደግሞ እምንፈልገው ሰራተኛና አምራች መሆናችንን ነው፡፡ ባለ-እጅ ስለተባልንም ደስተኞች ነን" አለ፡፡

የቀጥቃጭ ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የፋቂ ስራ፣ የሸማ ስራና ሌሎችንም የስራ ጥበብን ሰርተው በማሳየት የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የእድገት ምንጭ አመላካቾች ናቸው፡፡ የነሱን ስራዎች ማጥላላቱ የእድገት ምንጫችንን መቅበር ነው፡፡ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ለሁሉም ማህበረሰብ የስራ ውጤቶቻቸውን በየቤቱ እዲጠቀምበት አስችለዋል፡፡ ጥበብንም አሳይተዋል፡፡ ለነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ስራዎቻቸውን በበለጠ መንገድ እንዲቀጥሉና የስራ ውጤቶቻቸውንም በተሻሻለ መልኩ የሚያመርቱበት ስልት ልናመቻችላቸው ይገባል፡፡

ሰዎች እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ማበረታታት ሲገባቸው እንደተለየ የሰው ፍጡር ማየቱ አግባብነት የለውም፡፡ እነሱም እንደማንኛውም ሰው የአዳምና ሄዋን ልጆችና ከማንኛውን ሰው ጋር ወንድም እህት ናቸው፡፡ እነሱ ከሌላው የሕብረተሰብ ክፍል የተለዩበት ነገር ቢኖር ስራን ሰርተው ጥበበኛ ሆነው ሌላውን ህብረተሰብ በስራ ውጤታቸው ተጠቃሚ ማድረጋቸው ነው፡፡ መሆን ያለበት በነሱ ላይ ልዩነት ፈጥረን እነሱን ማሸማቀቅ ሳይሆን እነሱ ሰርተው ባመረቱት ምርት ተጠቃሚ በመሆናችን ምስጋናችንን መቸርና ከጎናቸው መቆም ነው፡፡፡

በአገራችን (ይህን ስራ ነው እንጅ ይህኛውን ስራ አልሰራም) እያልን ስራን እምናማርጠው አገራችን በድህነት ማጥ ውስጥ ገብታ እንድትማቅቅ አድርጓታል፡፡ በመሆኑም ይህንን ያረጀና ያፈጀ አመለካከት ጥለን እንደየትርፋማነታቸው በሁሉም የስራ ዘርፎች በመሰማራት አገራችንን መለወጣችን ነው እሚሻለው፡፡ በብረታብረትና ሸክላ ስራ ሙያዎች የተሰማሩትንም ሙያተኞች በሙያቸው እንዲገፉበትና በየጊዜው እያሻሻሉ እንዲሰሩት መንገዶችን ልናመቻችላቸውና ልንደግፋቸው ይገባል፡፡”

በማህበረሰቡ የተጀመረው የብረታ ብረትና የሸክላ ስራ ለስራው ግብዓት የሚሆኑትን ማቴሪያሎችና የአፈር ዓይነቶች አጥንቶ ለማወቅ ስላልተቻለ የስራ ውጤቱ አጥጋቢ አልሆነም፡፡ በስራው በውጤታማነት መቀጠል ቢቻል ኖሮ ማህበረሰቡን ጨብጦ የያዘውን ድህነት ለመቅረፍ በተቻለ ነበር፡፡ ነገር ግን ማህበረሰቡ ለሙያው የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች ለማሟላት ካለመቻሉ የተነሳ በሙያው ላይ በቀጣይነት መዝለቅ አልቻለም፡፡ ስለሆነም በስራው ብዙም ሳይገፋበት የተጀመረው ስራ መቋረጡ ግድ ሆኗል፡፡

በእርሻ መሬት እጥረት ምክንያት ከዚህ በፊት ማህበረሰቡ የማያውቀውን ስራ ሁሉ ለመልመድና በስራውም ውጤታማ ሆኖ ከተጋረጠበት ችግር ለመላቀቅ ብዙ ጥረት አድርጎ ነበር፡፡ ይሁንና ለመልመድ የተነሳባቸውና የጀመራቸው ሙያዎች ውጤታቸው ብዙም አጥጋቢ ሆኖ አላገኛቸውም፡፡ በዚህ የተነሳ ችግሮችም እየተባባሱ ሄዱ፡፡ ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ በዚህ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ እየኖረ የመደጋገፍ፣ የመረዳዳት፣ የፍቅርና የሰላም ኑሮው እክል አልገጠመውም፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ የመረዳዳት ባህሉን አጠናክሮ ለለበርካታ ዓመታት ኖሯል፡፡ ማህበረሰቡ በዚህ የመረዳዳት ሂደት አቅም በፈቀደ ደካማ ወገኖችን የመርዳት፣ በገንዘብ ችግር ምክንያት ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ተማሪዎችን የማስተማር፣ የፈጠራ ችሎታ ኖሯቸው በጉልበትም ሆነ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ፈጠራቸው እንዳይስተጓጎል በማድረግ በኩል ሰፊ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ ማህበረሰቡ መረዳዳት ባህሉ ቢሆንም ልመናን ያወግዛል፡፡ የተረጅነት ስሜት በማህበረሰቡ እንዲሰርፅ አይፈልግም፡፡ ስራን በራሱ ሰርቶ ማደግ እንዳለበት በማመን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሌት ተቀን ሳይመርጥ ይሰራል፡፡ ከገጠሙት ችግሮች ለመውጣት የራሱን ጥረት ያደርጋል፡፡

ሆኖም ከማህበረሰቡ አቅም በላይ የሆኑና ማህበረሰቡ ሊሻገራቸው የማይችላቸው ችግሮቹን ለመሻገር ከጎኑ በመቆም ችግሮቹን ለመቅረፍ አቅምና ፍላጎት ያለው አጋር ካለ በሩ ዝግ አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ የተጋረጠበትን ቴክኒካዊ የሙያ ክፍተቶች በመሙላት ችግሩን ለማስወገድ የሚንቀሳቀስ አጋር ካገኘ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማደግ አያዳግተውም፡፡

በ1994 ዓ.ም ጥቃቅን የተሻሻለ የሽመና ስራና የፈትል ስራ ስልጠና ለሁለት ወራት ያህል ማህበረሰቡን አሰልጥኗል፡፡ ዙምራም አሰልጣኞቹ ለስልጠና ያመጧቸውን መሸመኛ መሳሪያዎች በመመልከት ስልጠናው ከመጠናቀቁ በፊት ከአካባቢው የተገኙ እንጨቶችን ጠርቦ በመገጣጠም አንድ መሸመኛ መሳሪያ ለሰልጣኞቹ ሰርቶ አቅርቦላቸዋል፡፡ ዙምራ የመሸመኛውን እቃ ጠርቦና ገጣጥሞ ማቅረቡ ሰልጣኞቹ ስልጠናውን እንዳይረሱትና ከስልጠናው በኋላ በሰለጠኑት ሙያ ላይ በመሰማራት የሰለጠኑበትን ሙያ ሳያቋርጡ እንዲቀጥሉበት ረድቷቸዋል፡፡ ሰልጣኞቹ ይህንን ተጠቅመው ከስልጠናው በኋላ የተለያዩ ድዛይኖችን በመጠቀም ፎጣዎችን፣ ስካርፎችን፣ ብርድ ልብሶችን፣ ሸሚዞችን፣ ሱሪዎችንና የተለያዩ አልባሳትን ለመስራት ችለዋል፡፡

የቀድሞው (ባህላዊ) የሽመና ስራ

የተሻለው የሽመና ስራ ከ1994 ዓ.ም በኋላ

ጥቃቅን በ1995 የሞተር ወፍጮ ፈጪና ለወፍጮው ቴክንካዊ ስራ ባለሙያ ሊሆኑ ለሚችሉ 5 የማህበረሰቡ አባላት ሰልጣኞች ለሶስት ወራት አሰልጥኗል፡፡ ከስልጠናው በኋላም በስልጠናው የተካፈሉት ግለሰቦች ሌሎችንም የማህበረሰቡ አባላት የሰለጠኑትን ሙያ በማካፈል ወፍጮ የመፍጨት ስራን በማስፋፋት ለማህበረሰቡ፣ በቀበሌውና በአጎራባች ቀበሌዎች ለሚመጡ ተገልጋዮች በጥሩ ስነ-ምግባር፣ በታማኝነትና በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

በ1998 ደግሞ እንዲሁ ለጨርቃጨርቅ ማቅለሚያና ማተሚያ ባለሙያ የሚሆኑ ለ2 የማህበረሰቡ አባላት ሰልጣኞች ስልጠና ሰጥቷል፡፡ ከስልጠናው በኋላም በዘመናዊና በተሻሻለው የሽመና ስራ የሚመረቱ አልባሳትን የማቅለምና የማተም ስራውን በማካሄድ የማህበረሰቡን የአልባሳት ምርት በተለያዩ ቀለማት በማስዋብና የህትመት ስራውንም በመስራት የማህበረሰቡን ምርት ለመሸጥና ለማስተዋወቅ ተችሏል፡፡

አክሽን ኤድ በ1998 ለ10 የማህበረሰቡ አባላት በዘመናዊ ተወንጫፊ የሽመና ስራ ስልጠና ለ15 ቀናት ሰጥቷል፡፡ ይህ ስልጠና በፊት ሲሰራበት ከነበረው ዘመናዊና የተሻሻለ የሽመና ስራ በበለጠ የተሻለ ፍጥነት ባለው ሁኔታ የሚሰራና የሚያመርተውም ምርት ወርዱ ከበፊቱ ከተሻሻለው የሽመና ስራ በእጥፍ እንዲጨምር አስችሏል፡፡

የተሻሻለው ዘመናዊ ተወንጫፊ የሽመና ስራ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ

ማህበረሰቡ እሚፈልገው ትንሽ የስልጠና ፍንጭ እንዲያገኝ እንጅ ትንሽ ፍንጭ ከተሰጠው የራሱን ጥበብ እየጨመረና የተለያዩ ድዛይኖችን እያወጣ ምርቱን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ እያመረተ ለሽያጭ በማቅረብ ራሱን ለመለወጥ በመፍጨርጨርና ለሌላው ማህበረሰብ ምሳሌ ሊሆን ችሏል፡፡

የማህበረሰቡ አባላት የተለያየ ስልጠና ማግኘታቸው ራሳቸውን በተለያዩ የስራ መስኮች በማስገባት ሁሉንም የማህበሩን አባላት በሚችሉት የስራ መስክ በማሰማራት የማህበሩን ገቢ ከዓመት ዓመት እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ ለማህበሩ የገቢ ምንጭ የሚሆኑት የስራ መስኮች፣ በእጅ የሚሰራ ዘመናዊ የተሻሻለ የሽመና ስራ፣ የወፍጮ ስራ፣ የንግድ ስራ፣ በመጠኑም ቢሆን የልብስ ስፌት ስራ፣ የወተት ላም እርባታ ስራ ገቢ የሚያገኝባቸው የስራ ዘርፎች ናቸው፡፡

የአባላት የስራ መግቢያ ጧት 2፡00 ሰዓት ሲሆን መውጫ ደግሞ ማታ በ11፡00 ሰዓት ነው፡፡ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት ደግሞ የምሳ ረፍት ይኖራል፡፡ ይሁን እንጅ አባላት በእቅድ ከተያዘው ሰዓት አልፎ እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት ድረስ የማህበሩን ስራ ሲሰሩ ይቆያሉ፡፡ ይህ ደግሞ አባላቱ በግላቸው ከሚሰሩት ስራ ይልቅ ለማህበረሱ ስራ ትኩረት ሰጥተው የመስራት ልምድ ያላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡

በማህበረሰቡ ሰባቱ ቀናት የስራ ቀናት ናቸው፡፡ ከነዚህ ሰባት የስራ ቀናት ውስጥ በየሳምንቱ ማክሰኞ ሁሉም የማህበረሰቡ አባለት የሚሳተፍበት ለወገን ደራሽ የገቢ ማሰባሰቢያ የስራ ቀን ነው፡፡ በየሳምንቱ እሁድ ደግሞ የአባላት የጧስ ቀን ነው፡፡ የጧስ

ቀን ማለት የማህበሩ አባላት ከማህበሩ ውጭ በግላቸው የሚሰሩበት ሲሆን በዚህ ቀን አባላት ልብሳቸውን የሚያጥቡበትና ሌሎችንም በግላቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለማሟላት የሚችሉበት ቀን ነው፡፡ ከዚህ ቀን በተጫማሪ ደግሞ በሁሉም ቀናት ማታ-ማታ ከጥበቃ ስራ የተረፈችውን ጊዜያት የግላቸው ስራ የሚያከናውኑበት ሊሆን ይችላል፡፡ መዝናናት ከፈለጉም እንዲሁ በዚሁ የጢስ ቀን ይዝናኑበታል፡፡ የማህበሩ ስራ በጣም አንገብጋቢ ሆኖ ከተገኘ ግን ይህ በየሳምንቱ የሚገኘው የጢስ ቀን ይሰረዝና የማህበር ስራ ሲሰራበት ይችላል፡፡

የማህበረሰቡ አባላት በሙሉ ቀን-ቀን በየስራ ምድባቸው ሲሰሩ ከመዋላቸውም በተጨማሪ ማታ ማታ የአካባቢውን (ሰፈሩን) በማህበረሰቡ የጸጥታ ኮሚቴ አማካይነት ተመዳድበው ሲጠብቁ ያድራሉ፡፡ ጥበቃው የሚሆነው በየምድቦቹ ያሉት የፀጥታ ኮሚቴ የመደቧቸው አስተባባሪዎች እንደማህበረሰቡ አባላት ብዛት ሌሊቱን ከ4 ወይም ከ5 ተራ በመመደብ ሁሉም አባላት በተሰጠው ተራ መሰረት አካባቢውን ይጠብቃል፡፡ ተራውም የሚሆነው በሮቴሽን (በቅይይር) ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ሮንደኛ በዛሬው ምሽት ከአንድ እስከ ሶስት ሰዓት ጠብቆ ከሆነ በነጋታው ሌሊት ከሶስት እስከ አምስት ሰዓት ይጠብቃል፡፡ በሚቀጥለው ሌሊት ደግሞ ከአምስት እሰከ ሰባት ሰዓት እያለ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉም ተረኞች ይቀያየራሉ፡፡ ይህም የሚደረገው ከማህበረሰቡ ውጭ ያሉ አንዳንድ መጥፎ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ግለሰቦች ወደ ማህበረሰቡ ገብተው የማህበረሰቡን ሰላም እንዳያናጉ ለመከላከል ነው፡፡

በማህበሩ ሁሉም አባላት በየተመደበበት የስራ ዘርፍ ተሰማርቶ እቅዱን ለማሳካት የአቅሙን ያህል ሲጥርና ሲፍጨረጨር ይውላል፡፡ ሁሉም የተመደበበትን ስራ ባቀደው እቅድ መሰረት ከእቅዱ ለመድረስና ከእቅዱም በላይ ከልቡ ውጤታማ ስራ ሰርቶ ለመዋል ጤናማ በሆነ የውድድር መንፈስ ስራውን ያጣድፋል፡፡ የስራው ውጤት ከአቅም ልዩነት አኳያ አንዱ ከአንደኛው ሊበላለጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም እንዲሰራ እሚፈለገው እንዳቅሙ ነው፡፡ ሁሉም ያለምንም ልግመት በጢስ ቀኑ ከሚሰራው በበለጠ መልኩ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በየተመደበበት የስራ ዘርፍ ስራውን ሲያከናውን ይውላል፡፡ ይህ ደግሞ ከኔ ይልቅ ለወንድሜ ወይም ከኔ ይልቅ ለእህቴ ጥሩ ነገር እንዲሆንለት ወይም እንዲሆንላት የመተሳሰብ ኑሮን ያመላክታል፡፡

አብዛኞቹ የማህበሩ አባላት የስራ ምድባቸው መደበኛ ነው፡፡ ቋሚ ያልሆኑ አዳዲስ በየቀኑ የሚቀያየሩ የስራ ዘርፎች ካሉ እንዳስፈላጊነቱ ከአንደኛው የስራ ዘርፍ ወደ ሌላው የስራ ዘርፍ በመቀያየር የሚመቻችበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ አንዱን አባል ከአንደኛው

የስራ ዘርፍ አንስቶ አንገብጋቢ ወደሆነው አዲሱ ቋሚ ያልሆነ የስራ ዘርፍ ይመደባል፡፡ ለዚህም እንዲያመች ጢት-ጢት አባላት ተገናኝተው ስለአስተዳደራቸው ሰላምታ እሚለዋወጡበትና የስራ ምድብ የሚቀያየሩበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ብዙውን ጊዜ ሰላምታ የሚለዋወጡት ለሰው ልጆች በሙሉ ከፍተኛ ክብር የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ለማመላከት ወደ ግለሰቡ/ቧ/ ወይም ወደ ግለሰቦቹ ዘወር በማለት አንገታቸውን ዝቅ አድርጎ ቀና በማድረግ ነው፡፡

በተለያየ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው ሲሰሩ የዋሉ አባላት ሁሉ ማታ-ማታ እንዲሁ ይገናኛሉ፡፡ በግንኙነቱም ወቅት የክቡር ዶክተር ዙምራ የተሰባሰብነውን አባላት እንዴት ዋላችሁ? ብሎ ይጠይቃል፡፡ አባለቱም ደህና ብለው በሙሉ ድምፅ ይመልሳሉ፡፡ ክቡር ዶክተር ዙምራ በመቀጠልም ስራ እንዴት ነው? ይላል፡፡ ይህ ማለት በስራው ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ በአንድ ላይ ተወያይተው ለችግሮቹ ቶሎ መፍትሂ ለመሻት እንዲያመች ነው፡፡ ችግሮች ካሉ ችግሮቹ ተገልጸው ይወያዩባቸዋል፡፡ መፍትሂያቸውን አግኝተው ለቀጣዩ ቀን ችግሮቹ እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ አባላቱ ችግሮች ከሌሉ ስራ ደህና ነው ይላሉ፡፡ ዙምራም በመቀጠል ሌላው ምንድነው? ብሎ ይጠይቃል፡፡ አባላቱም እንዲሁ ሌላው ሰላም ነው ይላሉ፡፡ ዙምራም ንፁህ ሰላምታ? ብሎ እንደገና ይጠይቃል፡፡ አባላቱም ሁሉም ነገር ሰላም ከሆነ አዎ ንፁህ ሰላምታ ነው ይላሉ፡፡ የክቡር ዶክተር ዙምራም በመጨረሻ ስራ ጥሩ ከሆነ፣ ውሎ ሰላም ከሆነ እረፍት ነው ይላል፡፡ እረፍት ነው ከተባለ በኋላ እቤቱ ሂዶ ስራ ለመስራት የቸኮለ ወደቤቱ ሂዶ ስራውን ይሰራል፡፡ ትንሽ ሲጨዋወት ለመቆየት የፈለገ እዛው ቁጭ ብሎ በማህበረሰቡ ላይ ስላለው አጠቃላይ ሁኔታና ሊጎበኙ የመጡ ጎብኚዎች ምን አስተያየት እንደሰጡ ሲጨዋወቱና ገጠመኞቻቸውን ሲለዋወጡ ከቆዩ በኋላ ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

በየስራ ዘርፉ ያለው የስራ ምርት (ገንዘብ) ሁሉ በማህበሩ የገቢና የወጪ ሰነዶች እየተያዘ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ በዚህ አሰራር የተገኘውም ገንዘብ ለካፒታል፣ ለተቋማት ማስፋፊያ ከሚውለውና ለንግድ ተቋማት ማንቀሳቀሻ ከሚውለው በጀት ውጭ ያለው በዓመት አንድ ጊዜ ለአባላት ለክፍፍል ይውላል፡፡ ክፍፍሉም ለሁሉም የማህበሩ አባላት እኩል ነው፡፡

5.4 የሴቶች እኩልነት

በማህበረሰቡ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የሴት ስራ የወንድ ስራ ተብሎ የተለየውን ተለምዷዊ የሆነውን ያታን መሰረት ያደረገ የስራ ባህል ንዶ የራሱን አዲስ ባህል ገንብቶ የሴት- የወንድ የሚለውን ስራ አስቀርቶ ስራን በችሎታ ብቻ

በመከፋፈል አዲስና የራሱ የሆነውን የህይወት ጎዳና ይመራል፡፡ በማህበረሰቡ ፆታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል የለም፡፡ ሴት የወንድ ስራ ብትሰራ ያባቷ ስራ ነው፡፡ ወንድም የሴት ስራ ቢሰራ የእናቱ ስራ ነው፡፡ እናት በሌለችበት አባት የለም፡፡ አባት በሌለበት እናት የለችም፡፡ በመሆኑም ሴትና ወንድ እኩል መሆን አለባቸው፡፡ ሁሉም ስራ የሁሉም ነው፡፡ ወንዶች ሴቶችን የማይጋሯቸውና የሴቶች ስራ ብቻ የሆነው ተፈጥሮ የለገሰላቸው ማርገዝ፣ መውለድና ማጥባት ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው ሁሉም ስራ የሁሉም /የሴቱም የወንዱም/ ነው፡፡

ሴቷም ሆነች ወንዱ በሚችሉት አቅም የቤት ውስጡንም ሆነ የውጩን ስራ፣ ችሎታን መሰረት ባደረገ የስራ ምድብ ይሰማራሉ፡፡ ወንዱ እንጀራ ይጋግራል፣ ወጥ ይሰራል፣ ውሃ ይቀዳል፣ ህፃን ልጅን ይንከባከባል፣ ሌሎችንም በተለምዶ የሴት ስራ ተብለው የሚታወቁትን ስራዎች ሁሉ ያከናውናል፡፡ ሴቷም እርሻ ታርሳለች፣ ሽመና ትሸመናለች፣ ሌሎችንም በተለምዶ የወንድ ስራ ተብለው የሚታወቁትን ስራዎች ሁሉ ትሰራለች፡፡ ይህ ስራን የወንድ የሴት ሳይሉ ሁሉንም መስራት ጥገኝነትን ያስቀራል፡፡ ሴቷ ራሷን ችላ በወንዶች ጥገኛ ሳትሆን ስራዋን ለመስራት ይረዳታል፡፡ ወንዱም እንዲሁ በሴቶች ጥገኛ ሳይሆን በራሱ ስራዎቹን እያከናወነ ከሴቶች ጥገኝነት እንዲወጣ ይረዳዋል፡፡ ይህም ስራን አንድን ፆታ ብቻ በመጠበቅ ተርፎ እንዳያድር ያደርጋል፡፡ በማህበረሰቡ የሴቶች እኩልነት በስራ ብቻ ሳይሆን ንብረትን በማስተዳደር፣ እኩል ተወያይቶ ውሳኔ በመስጠት፣ በማህበረሰቡ ባሉት አደረጃጀቶች እኩል ተሳትፎ በማድረግ ሁሉ የሴቶች መብት ተጠብቆ ነው እሚሄደው፡፡

የሴቶችና የወንዶች የስራ ተሳትፎ

5.5 ቱሪዝም

የአውራ አምባ ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ በ1993 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ቴሌቪዥን ሚዲያ ላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮ የማህበረሰቡን ባህል፣ አኗኗርና እምነት በበለጠ ሁኔታ ለመረዳት ጎብኚዎች ከየአቅጣጫው ወደ ማህበረሰቡ በመምጣት ከእንግዳ

ተቀባይ ኮሚቴ አባላት በተለይም ከማህበረሰቡ መስራች ከክቡር ዶክተር ዙምራ ኑሩ ስለማህበረሰቡ አጠቃላይ መረጃ ማግኘት ቻሉ፡፡ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች እንዲሁ ከበቂ በላይ መልሶችን አግኝተው ወደሚኖሩበት አካባቢ ሲመለሱ ለአካባቢያቸው ማህበረሰብ ስለ አውራ አምባ ማህበረሰብ ትንታኔ በመስጠታቸው የጎብኚዎችን ቁጥር ከአደር አደር እንዲጨምር አደረገው፡፡ ማህበረሰቡን ከሚጎበኙት ጎብኚዎች መካከል የአገር ውስጥ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የግል ድርጅቶች፣ ጋዜጠኞችና የውጭ ቱሪስቶችም ጭምር ናቸው፡፡

የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ጎብኚዎች

የአውራ አምባ ማህበረሰብን ለመጎብኘት የሚመጣው የህብረተሰብ ክፍል ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ ሲሄድ የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ከማህበረሰቡ ጋር በመነጋገር በልዩ ሁኔታ ለሁሉም የሰው ልጆች (ለአገር ውስጥም ይሁን ለውጭ አገር ዜጎች) እኩል የጉብኝት ክፍያ እንዲሆን በመስማማት በሚያዚያ 5, 2000 ዓ.ም ላይ የአውራ አምባ ማህበረሰብ የቱሪዝም መዳረሻ እንዲሆን እውቅና ተሰጠው፡፡ በዚህ ጊዜ የነበረው የጎብኝት ክፍያ ለተማሪዎች 1 ብርና ለሌሎች 3 ብር ነበር፡፡ ከ1994 ጀምሮ እስከ ሚያዚያ 4 2000 ድረስ ማህበረሰቡን ለመጎብኘት የመጡ ጎብኚዎች ከክፍያ ነፃ ሆነው ሲስተናገዱ ቆይተዋል፡፡ ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የጉብኝት ክፍያው በጎብኚዎች አስተያየት ለተማሪ 3 ብርና ለሌሎች 5 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አሁን ላይም እንደገና በጎብኝዎች አስተያየት ለተማሪ 6 ብርና ለሌሎች 20 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ ከጎብኚዎች ክፍያ የሚሰባሰበው ገንዘብ ለወገን ደራሽ ተብሎ ይሰባሰብና ችግር ለደረሰባቸው ግለሰቦች መታደጊያ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመሆኑም የጉብኝት ክፍያ ለአባላት ክፍፍል አይውልም፡፡

<u>በአውራ አምባ የቱሪዝም መዳረሻ የየዓመቱን የጎብኚዎች ስታስቲክስ</u>

የጉብኝት ዘመን	የአገር ውስጥ ጎብኚዎች			የውጭ አገር ጎብኚዎች			ጠቅላላ ድምር		
	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ
1994	13	1	14	0	0	0	13	1	**14**
1995	316	26	342	54	36	90	370	62	**432**
1996	1152	198	1350	18	22	40	1170	220	**1390**
1997	1412	434	1846	26	35	61	1438	469	**1907**
1998	3597	1030	4627	70	74	144	3667	1104	**4771**
1999	6349	2258	8607	331	70	401	6680	2328	**9008**
2000	4327	1799	6126	316	245	561	4643	2044	**6687**
2001	4600	1606	6206	289	343	632	4889	1949	**6838**
2002	4220	2285	6505	351	458	809	4571	2743	**7314**
2003	3266	1802	5068	498	583	1081	3764	2385	**6149**
2004	3864	1889	5753	577	629	1206	4441	2518	**6959**
2005	3651	2078	5729	755	906	1661	4406	2984	**7390**
2006	3545	1942	5487	1453	1690	3143	4998	3632	**8630**
ድምር	**40312**	**17348**	**57660**	**4738**	**5091**	**9829**	**45050**	**22439**	**67489**

5.6 ለወገን ደራሽ

ዙምራ ከ4 ዓመት እድሜው ጀምሮ ከሚያነሳቸው መሰረታዊ ሀሳቦች አንዱ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ለስራ ብቁ ያልሆኑ አቅመ-ደካሞችን መርዳት ነው፡፡ ይህንንም ከ13 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ በሚያገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲታደጋቸው ቆይቷል፡፡ በ1964 ዓ.ም ማህበረሰብ ከመሰረተ በኋላም እንዲሁ ማህበረሰቡን እያስተባበረ መፈነቃቀሉም ሳያግደው የአቅመ ደካሞችን እርሻ እንዲታረስላቸው በማድረግና ችግረኞችንም የገንዘብ ድጋፍ ተደርጎላቸው ከችግራቸው ተወግደው የራሳቸውን ስራ ፈጥረው እንዲሄዱ እያደረገ እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ ቆይቷል፡፡

ማህበረሰቡ ከስደት ሲመለስ ደግሞ የእርሻ መሬት እጥረቱ የጎላ ስለነበር ደካሞችን ለመታደግ አላመቻቸውም፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ደካሞችንና ችግረኞችን ለመታደግ ከእርሻ ስራ የተለየ የገቢ ማስገኛ የሚሆን ስራ ማፈላለግ ነበረበት፡፡ ለገቢ ማስገኛ ስራው የተገኘው አማራጭ ጥጥ በመፍተልና የተፈተለውን ጥጥ በየሳምንቱ ማክሰኞ በመሸመን ትርፍ ማግኘትና በትርፉ አቅመ-ደካሞችን በሚቻለው አቅም ሁሉ መርዳት ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ መቋቋሚያ ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በ1986 ዓ.ም የማህበረሰቡ አባላት ሁሉ አንድ-አንድ ብር አዋጥተው ባሰባሰቡት ገንዘብ ጥጥ ገዙ፡፡ ከዚያም በየሳምንቱ ማክሰኞ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ተገኝተውና ተሰባስበው ጥጡን እየፈተሉና የተፈተለውን እየሸመኑ የተወሰነች ገቢ ለማግኘት በቅተዋል፡፡

ለወገን ደራሽ ገቢ ማስገኛ እየተሳተፉ ያሉ አባላት

በዚህ በማክሰኞ የልማት ቀን የሚሰባሰበው ገቢ ለወገን ደራሽ ይባላል፡፡ የወገን ደራሽ ገንዘቡ የሚደግፈው አቅመ-ደካሞችን፣ ታምመው መታከሚያ ያጡ የማህበረሰቡ አባላትን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችንና አልፎ ተርፎም ከማህበረሰቡ ውጭ ያሉ በጣም የባሰ ችግር ያለባቸው ግለሰቦችንም ጭምር ነው፡፡ ቤታቸው የፈረሰባቸውና ቤት የሌላቸውንም ቤታቸውን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ የወገን ደራሽ በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚገኙ አቅመ-ደካሞችና ከሌላው ከማህበረሰቡ አባላት በተለየ መልኩ ችግር ውስጥ ወድቀው ለሚገኙ አባላት ከችግራቸው እንዲገላገሉ ያደርጋል፡፡

ችግረኞቹም የሚለዩት በችግር አጥኚና መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ነው፡፡ ይህ ኮሚቴ በማህበረሰቡ ውስጥ የባሰ ችግር ያለባቸውን የማህበረሰቡን አባላት በደንብ ለይቶ ካጠና በኋላ ለሳምንታዊ የልማት ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ሳምንታዊ የልማት ኮሚቴውም ካለው የወገን ደራሽ ገንዘብ ጋር በማጣጣም ችግር ውስጥ ለወደቁት ግለሰቦች ገንዘቡን ይለግሳል፡፡

የወገን ደራሽ ገንዘቡ እያደገ ከሄደ ከማህበረሰቡ አልፎ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ አቅመ ደካሞችን ለመታደግ ይውላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እስካሁን ድረስ ባሉት ጊዜያት ከማህበረሰቡ ውጭ ላሉ ለተወሰኑ እጅግ በጣም ችግር ውስጥ ለወደቁ አቅመ- ደካሞች ብቻ

ነው መድረስ የቻለው፡፡ አቅሙ እየተጠናከረ ሲሄድ ግን ራዕዩ በጣም ሰፊና ዓለማቀፋዊ ነው፡፡ ከአውራ አምባ ማህበረሰብና በአካባቢው ከሚገኘው ማህበረሰብ ወጥቶ በችግር ውስጥ ላሉ ለሁሉም የሰው ልጆች ይደርሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በየሳምንቱ በልማት ቀኑ ማክሰኞ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት በስራ ተሰማርቶ ከሚገኘው ገቢ በተጨማሪ ማህበረሰቡን ለመጎብኘት ከሚመጡት ጎብኚዎች የሚከፈለው የመግቢያ ክፍያ የሚገባው ወደዚኸው የወገን ደራሽ ነው፡፡ የወገን ደራሽ ተብሎ የተሰበሰበው ገንዘብ አንድ ሰው ችግር ውስጥ ወድቆ የተገኘ እንደሆነ ለችግሩ ደርሶ ዋስትና እንዲሆን ነው፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ትልቁ ሀብት ሰው ነው፤ ሌላው ቀጥሎ የሚገኘው ነው ብሎ ያምናል፡፡ ቀጥሎ የሚገኘው ገንዘብ ትልቁን ሀብት ሰውን ለመመገብ የሚሆንና ተሰርቶ የሚገኝ ነው፡፡ ዕቃ ሰርቶ- ሰርቶ ስራውን ሲጨርስ ይጣላል፡፡ የሰው ልጅ ግን ትልቁ ገንዘብ ስለሆነ እንደ አረጀ ዕቃ መጣል የለበትም፡፡ ለሰው ደራሹ ሰው እንጅ ሌላ ማን ይመጣለታል? ስለሆነም በእረጅናም ሆነ በጤና ችግር ምክንያት ራሳቸውን ሰርተው መደገፍ የማይችሉ ደካሞችን ዋስትናቸውን የሚሸፍነው ማህበረሰቡ ነው፡፡ ማህበረሰቡም እንክብካቤውን ለማድረግ ያመች ዘንድ የራሱ ከሚቴ አለው፡፡ ይህ ኮሚቴውም ከወገን ደራሽ ያገኘውን ገንዘብ እንደ አስፈላጊነቱ ወጭ እያደረገ ለአረጋዊያኑ በሚመቻቸው መልኩ እንዲቀርብላቸውና ያለች ቀሪ ህይወታቸውን ተደስተው እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በቀን ሶስት ጊዜ ቁርስ፣ ምሳና እራት ጊዜያቸውን ጠብቀው ይቀርቡላቸዋል፡፡ በየቀኑ የመኖሪያ ግቢያቸው ይፀዳል፡፡ በየሶስት ቀኑ ገላቸው ይታጠባል፡፡ በየሳመንቱም ልብሳቸው ይታጠብላቸዋል፡፡

የአረጋዊያን ተንከባካቢ ኮሚቴ በማህበረሰቡ ውስጥ ወላጆቻቸው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩባቸው ህፃናት ቢኖሩም ዕድሜያቸው 18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ አስፈላጊው እንክብካቤ ሁሉ እያደረገ ያሳድጋቸዋል፡፡ እንደማንኛውም የማህበረሰቡ ህፃናት ትምህርታቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ በተቻለ መጠን ይቀርብላቸዋል፡፡ 18 ዓመት ከሞላቸው በኋላ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የመወሰን መብቱ የነሱው ነው፡፡ ከማህበረሰቡ ጋር ማህበረሰቡ እንደሆነው ሆነው መኖር ከፈለጉ በማህበረሰቡ ታቅፈው እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ከማህበረሰቡም ወጣ ብለው የራሳቸውን ስራ ፈጥረው መኖር ቢፈልጉም እንዲሁ ምርጫው የራሳቸው ነው፡፡ ማህበረሰቡ እነዚህን 18 ዓመት የሞላቸውን ልጆች አሳድገናችኋልና እኛ ባዘዝናችሁ ትሄዳላችሁ ብሎ አያስገድዳቸውም፡፡ የራሳቸው ስራ ፈልገው መሄድ የሚችሉበት እድሉ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በማህበረሰቡ እንክብካቤ እየተደረገላቸው ያሉ አረጋዊያን 2003 ዓ.ም

5.7 የህጻናት አስተዳደግ

ህጻናት እግረ ተከል ከሆኑ ጀምሮ የማህበረሰቡን እሴቶች በህፃን አእምሮአቸው ተቀርፆ እንዲያድጉ ትምህርቱ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ በሰራው የመዋዕለ ህጻናት ት/ቤት በማህበረሰቡ አባላት ፊደሎችን እንዲለዩና ወደ መደበኛ ት/ቤት ከመግባታቸው በፊት ማወቅ የሚገባቸውን ሁሉ እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ ህፃናቱ ተምረው ከት/ቤቱ ሲወጡ በየቀኑ መፈክራቸውን ያሰማሉ፡፡ መፈክራቸውም እንዲህ ይነበባል፡፡

እኛ ታዳጊ ህፃናት የሰውን ገንዘብ አንነካም፣
ወድቆ ብናገኝ ለባለቤቱ እንመልሳለን፣
በመተባበር በመተዛዘን እየሰራን እናመርታለን፣
የሰላም ኑሯችን ይለመልማል፡፡

ይህች መፈክር ለህፃናት ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም ቃል እምታስገባ ናት፡፡ ሁለት መልዕክቶችን ይዛለች፡፡ አንደኛው መልክት አገራችን ኢትዮጵያ ማደግ እያማራት እድገቷን ያላገኘች ገና ታዳጊ አገር ናት፡፡ ተባብረን ተዛዝነንና ተደጋግፈን ከሄድን አገራችን ካደጉት አገሮች የማትደርስበትና የኛም የሰላም ኑሯችን የማይለመልምበት ምክንያት የለም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው መልዕክት ደግሞ ማህበረሰቡ በስራ፣ በሽልማትና በስጦታ የተገኘ ሀብት የራስ ገንዘብ መሆኑን ያውቃል፡፡ ማህበረሰቡ የራሱ ያልሆነን ገንዘብ ከየትኛውም ቦታ ቢያገኝ ወገናችን ሲለፋ ኖሮ ወድቆበት ብሎ አዝኖ አፈላልጎ ለባለቤቱ ይሰጣል፡፡ ባለቤቱ ካልተገኘ ደግሞ ማህበረሰቡ በመዋቅራዊ አደረጃጀቱ መርጦ ላስቀመጠው ወድቆ ለተገኘ ገንዘብ ያዥ ኮሚቴ የተገኘውን ንብረት ከነሙሉ መረጃው ያስረክባል፡፡ ኮሚቴውም በተቀበለው መረጃ መሰረት ንብረቱ ለባለቤቱ የሚመለስበትን ስልት ያመቻቻል፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ የሰው ገንዘብ መብላት ወንጀል ነው፡፡ ከወንጀልም አልፎ አንዷት ሳንቲም እንኳ መንካት እርም ነው ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ራስን ለማጥራት አንድ ሳንቲም ወደነሱ ከምትመጣባቸው ይልቅ ወደ ወገናቸው እንድትሄድ ነው ምርጫቸውን የሚያደርጉት፡፡ ማህበረሰቡ ጠቃሚና መጥፎ አካሄዶችን ለይቶ በመያዝ መጥፎዎችን ከስራቸው ነቅሎና በምትካቸው ጠቃሚ አካሄዶችን ዘርግቶ በተግባር እያሳየ ነው ህጻናቱን እሚያስተምረው፡፡ ማህበረሰቡ ስራና ንግግር በአንድ ላይ መሄድ አለባቸው ብሎ ያምናል፡፡ *እኛ መጥፎ እየሰራን ለልጆቻችን ስለ በጎ ነገር እምናስተምራቸው ከሆነ ምን ዘርተን ምን ልናመርት እንፈልጋለን? ልጆቻችን ወደ በጎው ከመሄድ ይልቅ እኛ ስናደርግ ያዩትን መጥፎ ነገር መስራት ነው የሚቀላቸው፡፡* በመሆኑም ማህበረሰቡ *ስራና ንግግር ተነጣጥለው የሚሄዱ ከሆነ ከቅዠት ተለይቶ አይታይም* ይላል፡፡

የመዋዕለ ህፃናት ትምህርት የሚከታተሉ ህጻናት በመዝናናት ላይ 20006 ዓ.ም

ህፃናቱም የመዋእለ ህፃናቱን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ 7 እና 8 ዓመት ሲሞላቸው ወደ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ሄደው ይገባሉ፡፡ ተማሪዎቹ ወደ መደበኛ ትምህርት ከገቡም በኋላም ከት/ቤት መልስ ያለውን ጊዜያቸውን ቀኗን ከሶስት በመከፋፈል ማለትም የስራ ጊዜ፣ የጥናት ጊዜና የጨዋታ ጊዜ ብለው ከፋፍለው በማቀድ በእቅዳቸው ይመራሉ፡፡ የማህበረሰቡ እሴቶች በተማሪዎቹ ላይ ሰርጸው እንዲሄዱ ዘወትር ከሚሰጣቸው ምክርና ትምህርት ባሻገር ት/ቤት በሚማሩት ትምህርት ተመራምረው የራሳቸው ፈጠራ ኖሯቸው ራሳቸውን ለመምራት የሚያስችላቸውንና ለሀገርም እድገት ወሳኝ ሊሆን የሚችል የፈጠራ ትምህርት ቀስመው በራሳቸው ፈጠራ ራሳቸውን ሊያስተዳድሩበት የሚችሉበትን ትምህርት እየተሰጡ እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡

ዙምራ የማህበረሰቡ ተማሪዎችን እንዴት ብለው ተምረውና ስራን ፈጥረው መሄድ እንዳለባቸው እንዲህ በማለት ነው የሚመክራቸው፡፡

ገበሬ መሀይም ነው ብላችሁ እንደሆነ ተሳስታችኋል፡፡ ገበሬ መሀይም አይደለም፡፡ የቆየ ሳይንስም ቢሆን አጁን እግር አድርጎ ሰርቶ ባመረተው ምርት የዓለም የሰው

ልጆችን የሚመግብ ገበሬ ነው፡፡ ገበሬ ምሁር ነው፡፡ መሀይም አይደለም፡፡ እናንተን ደግሞ ከገበሬ የሌለውንና ገበሬ እማያገኘውን ሰርታችሁ ልታመጡልን እያስተማርናችሁ ነው፡፡ ፈረንጅ በተግባር እየሰራ ነው የጫፈው፡፡ ኢንጅነሪንግ፣ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር የሆነው በተግባር እየሰራ ነው፡፡ እናንተ በተግባር ሳታሳዩ ዝምብላችሁ አንብባችሁ ብቻ ኢንጅነሪነግ፣ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር እምትሆኑ ከሆነ ወደኛ በምትመጡ ጊዜ ገበሬ ይወዳደራችኋል፡፡ ገበሬ እጁን እግር አድርጎ የሰራውንና ያመረተውን ምርት ይዞ ሰውን ይሰበስብና ምርቶቹን በዓይነት በጆንያ ቁጭ- ቁጭ አድርጎ ይኸው የገበሬ ምርት በማለት ገበሬ የተባለበትን እጁን እግር አድርጎ ያመረተውን ምርት በማቅረብ እስቲ እናንተም ከገበሬ የሌለውን ያመረታችሁትን ምርት አሳዩን ይሏችኋል፡፡ እናንተ የራሳችሁ የሆነ ከገበሬ የሌለውን ምርት ሰርታችሁ ካሳያችሁ ዶክተሬታችሁ ይኖራል፡፡ ሰርታችሁ ካላሳያችሁ ስማችሁን ፈልጉ ይላል፡፡ ስምን ፈልጎ ማስጠራት ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ምንም ሰርታችሁ የምታሳዩት ከሌላችሁ ደግሞ የመማራችሁ ትርጉም ምንድነው?

እናንተ ዳቢችሁን ሳታበስሉ ገበሬዎች ካበሰሉት መስመር ላይ ሆናችሁ እነሱን መስደብ ማለት መሀይም ምሁርን መስደብ ማለት ነው፡፡ ምሁርነት የበሰለውን ዳቦ መብላት ሳይሆን ያልበሰለውን ዳቦ አብስሎ ለተተኪው ትውልድ ማቅረብ ነው፡፡ እናንተ የራሳችሁን ፈጠራ ከፈጠራችሁ ግን ገበሬዎች ይሆን ሰርታችኋል፡፡ እኛ ደግሞ በአቅማችን ይሆን ሰርተናል ትላላችሁ፡፡ የፈጠራችሁት በሌለ ነገር ገበሬን መጫንና መርገጥ አይገባም፡፡ እናንተ ፊደል ቆጥራችሁ ብቻ የምትመጡ ከሆነ ብር መቁጠር እንደሆነ ገበሬም አያቅተው፡፡ ፈረንጅ ስራን ስራ እየፈጠረለት ከሽክላና ብረታ ብረት ተነስቶ ነው ሰማይ ላይ የበረረው እንጅ ሰማይ ላይ አልተፈጠረም፡፡ እኛ ግን የዳቦ መብያ ሳህን እንኳ አልሰራንም፡፡ የሰራው ፈረንጅ ነው፡፡ ፈረንጅም ሰው እኛም ሰው፡፡ የኔ ቁጭት ፈረንጅም ሰው ከሆነ እኛም ሰው ከሆንን ሰው የሰራውን እንዴት ያቅተናል? ፈረንጅም ከሰማይ እንደዝናብ አልወረደለትም፡፡ እንደ እንጉዳይም ከመሬት አልወጣለትም፡፡ የኛ ችግር ሽንፈታችንን አለማወቃችን ነው፡፡ ሽንፈታችንን ብናውቅ ቁጭት ይመጣ ነበር፡፡ ቁጭት ከመጣ ደግሞ ወደስራው እንገባ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የስልጣኔ መጀመሪያ ነበረች እንላለን፡፡ ስልጣኔያችን ምን ስንል አመለጠን? እንዳናነሳስ የገደበን ማነው?

እናም ተምራችሁ ሲያበቃ በአንድ ዳቦ ላይ የተንጠለጠለ ህይወት የትም አያደርስም፡፡ አንድ ዳቦ ማለት ምንድነው? ተምረን መንግስት ቢቀጥረን ብሎ አንድን መስመር ብቻ ማየት ነው፡፡ እውን የመሬቱን ህዝብ መንግስት ሊቀጥር ይችላል? ይቅጠረው ካልንስ ቢሮው ከጠበበ ምን ልትሆኑ ነው? የቢሮ ምቀኛ ልንሆን ነው? ከቀጠረስ ዳቦውንስ ማን ያብስለው? ስትማሩ በምትማሩበት ትምህርት የምታገኙትን ተግባር ይዛችሁ የፈጠራ ሙያችሁን እያዳበራችሁ በራሳችሁ መተማመን ይኖርባችኋል፡፡ መንግስት ፈልጎ ከቀጠረ ይቀጥራችኋል፡፡ ካልቀጠራችሁ ደግሞ ተምራችሁ በወጣችሁበት ውጤት እራሳችሁን ትመራላችሁ፤ አገርንም ታስተዳድራላችሁ፡፡

አለበለዚያ መሬት እየጠበበች ነው የመጣችው፡፡ መሬት ተከፋፍላ በካርታ ገብታለች፡፡ ያቺ መሬት እንኳን እኛ ተጨምረንባት ለአባቶቻችንም አልበቃች፡፡ ተምረን ሳበቃ በራስ መተማመን ይኑር፡፡ ተምረን ወላጆቻችንን እምንረዳበት፣ አገርን እምንጠቅምበትና እራሳችንንም የምንመራበት ነገር መኖር አለበት፡፡ በምትማሩት ትምህርት የራሳችሁ የሆነ ፈጠራ ፈጥራችሁ መሄድና በምትፈጥሩት ፈጠራ መተዳደር ይኖርባችኋል፡፡ ፈጠራ ሳትፈጥሩ ዝምብላችሁ ፈረንጅ በተግባር እየሰራ የጫፈውን አንብባችሁ ብቻ ብትመጡ ዋጋ የለውም፡፡

እያለ ተማሪዎች በፈጠራ ስራ ላይ ትኩረት ሰጥተው መሄድ እንዳለባቸው ነው አበክሮ እሚመክረው፡፡ ዙምራ ይህንን ምክር ከጧት ከማታ በቅርቡ ለሚያገኛቸው የማህበረሰቡ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ነው የሚመክራቸው፡፡ ከማህበረሰቡ ልጆች በተጨማሪም በዚሁ ሰፈር በሚገኙት በ1ኛ ደረጃና በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎችም ጭምር በት/ቤቶቹ ፕሮግራም ተይዞለት ምክሩን በመለገስ ላይ ይገኛል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ዙምራ ማህበረሰቡን ለመጎብኘት ለሚመጡት ፈቃደኛ ለሆኑ የመንግስት ሰራተኞችም የቤት ስራ ይሰጣል፡፡ የቤት ስራው ምንድነው? የቤት ስራው በራሱ በዙምራ አንደበት እንዲህ ቀርቧል፡፡

ከመንግስት ስራ ውጭ ባለው ጊዜያችሁ (ስራ ላይ በማትሆኑበት ጊዜ) ቡድን ፈጥራችሁ ማህበር ግቡ፡፡ ማህበር ገብታችሁ ከብዙ ጭንቅላት ብዙ ሀሳብ አለ፡፡ ፈረንጅ እንደሚያደርገው አንዲንና አንዷቱን ጅማት አገናኝታችሁ አንድ ነገር ለመፍጠር ሞክሩ፡፡ ያችን ለመፍጠር እየሞከራችሁ በራሳችሁ እየጣራችሁ በሂዳችሁ ጊዜ ልጆቻችሁ እናንተን ያያሉ፡፡ ከናንተ የሚያዩትን ነገር ለማንሳት ይታገላሉ፡፡ እናንተ ውጤት ልታመጡም ላታመጡም ትችላላችሁ፡፡ ከእናንተ ትግል ተነስተው እናንተ የተሸነፋችሁበትን ልጆቻችሁ ሊያመጡት ይችላሉ፡፡ ልጆቻችሁን ወዴት መምራት እንዳለባቸው ጅምሩ መኖር አለበት፡፡ እና ይሄ የቤት ስራ ነው፡፡

እያለ ከአውራ አምባ ማህበረሰብና በቅርቡ ካሉት ት/ቤቶች ውጭ ያሉ ልጆች የስራ ፈጠራ ባህላቸውን በዚህ መልኩ እንዲያዳብሩ ዙምራ ምክሩን ለጎብኝዎቹ በመለገስ ላይ ይገኛል፡፡

5.8 የቤተሰብ ውይይት (ሰላምን ፍለጋ)

የሰላም ፍለጋ ውይይት ዓላማና ተግባር ሁሉም የዓለም የሰው ልጆች በሙሉ በየቤታቸው እየተወያዩ ችግሮቻቸውን ሁሉ እየፈቱ እድገትና ሰላምን ለማምጣት ውይይቱ ቁልፍ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሁሉም በየቤቱ በሰላም ፍላጋ ውይይት ሰላምን ይዞ ከመጣ ዓለም ሰላም ትሆናለች ብሎ ያምናል፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት በሙሉ በየ15 ቀኑ አንድ ጊዜ የቤተሰብ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ ውይይቱ የሚካሄደው በጉርብትና የሚቀራረቡ ከ3-4 የሚሆኑ ቤተሰቦች አንድ ላይ ተሰባስበው ወይም አንዱ ቤተሰብ ብቻውን ሊሆን ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የውይይቱ መድረክ መሪ በተወያዮቹ ቤተሰብ አባላት ጉባኤ ይመረጣል፡፡ ለመድረክ መሪነት በእጩነት የሚቀርቡት ከህፃናት እስከ አዋቂ ድረስ ያሉት የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ናቸው፡፡ ከዚያ ውስጥ አንዱ የቤተሰብ አወያይ ሆኖ ይመረጣል፡፡ ቤተሰብ አወያይነት አንዴ የተመረጠው ግለሰብ ሁልጊዜ መሪነቱ ይዞ እንዲቀጥል አይደረግም፡፡

የቤተሰብ አወያዩ /መድረክ መሪው/ ለተወሰኑ ጊዜያት(4 ጊዜ ነው ግን እንደቤተሰቡ ዓባላት) ካወያየ በኋላ ሌላ አወያይ እንዲመረጥ መድረክ መሪው ለቤቱ ያቀርባል፡፡ የቤተሰብ ተወያዩ አባላትም የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ይዳረስ ዘንድ ሌላ አወያይ እንዲመረጥ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ የነበረው አወያይ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

ለቤተሰብ ውይይቱ አጀንዳ ሆነው የሚቀርቡት የስራ እቅድ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ፣ መጥፎ አሰራርንና መጥፎ አነጋገርን መዋጋትን በተመለከተና ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ይሆናል፡፡ መድረክ መሪው ቤቱ የሚወያይባቸውን አጀንዳዎች ለቤቱ ያቀርብና እያንዳንዱ የውይይቱ ተካፋይ በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ ያለበትን ደረጃ በራሱ ግለ ሂስ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡ ግለ-ሂሱን እንዲያቀርብ የተጠየቀው ግለሰብ አጀንዳዎቹን በተመለከተ በራሱ ላይ የተከሰቱ ችግሮች ካሉበት ሁሉንም ያቀርባል፡፡ ግለሰቡ ችግሮቹን በራሱ ካቀረበ በኋላ የዘነጋሁት ካለ በቤቱ ይቅረብልኝና ተምሬበት እሄዳለሁ ብሎ በቤቱ እንዲቀርብለት ይጠይቃል፡፡ ግለ-ሂሱ ከቀረበ በኋላ የውይቱ ተካፋዮች ሂሱን ያቀረበውን ግለሰብ እሱ ካቀረበው የተለየ አቅርበው የሚያስተምሩት ካገኙ ሂሱን አቅርበው እንዲማር ያደርጋሉ፡፡ ትምርቱን ያገኘውም አካል እንዴት ያጋልጠኛል ማለት ሳይሆን እንኳን ችግሬን ገልፀህ ትምህርቱን እንድወስድ አደረግከኝ በማለት ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ሁሉም የውይይቱ ተካፋ እስኪዳረስ ድረስ ተራ በተራ ነው፡፡

ይህ የቤተሰብ ውይይት ህፃናት ከትላልቆች ጋር እኩል መብት እንዲኖራቸው፣ ከሁሉም የቤተሰብ አባላት ጋር እኩል የመወያየትና መድረኩንም እኩል የመምራት መብት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በውይይቱም ህፃናት የመድረኩ መሪ እየሆኑ የመድረክ አመራርን እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ የመድረክ አመራሩ በየተራ እየዞረ የቤተሰብ አባላቱ እንዲዳረሱ ይደረጋል፡፡ ህፃናት ከወላጆቻቸው ላይ ችግር ሲያዩ ለምንድነው ይኽ ችግር የተከሰተው ብለው ጠይቀው ለተፈጠረው ችግር ከወላጆቻቸው መልስ ማግኘት ከቻሉ ወይም ተቀባይነት ካገኙ በቤተሰብ ውይይቱ አያቀርቡትም፡፡ ለችግሩ ደግሞ አጥጋቢ መልስ ማግኘት ካልቻሉ በቤተሰብ ውይይት አጀንዳ አስይዘው ውይይት ተደረጎበት ህፃናት ወላጆቻቸውን፣ ወላጆች ደግም ልጆቻቸውን አስተምረው ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋሉ፡፡

በቤተሰብ ውይይት ወቅት አንዳንድ ጥቃቅን ችግሮች ቢከሰቱ በየጊዜውና በየቀኑ ችግሮቻቸውን እየተራረሙት ስለሚሄዱ ብዙውን ጊዜ ምንም ችግር በውይይቱ ተካፋዮች ሳይቀርብ ይቀራል፡፡ በዚህ ጊዜ መድረክ መሪው የውይይቱን ተካፋዮች ቀጥሉበት ብሎ

እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡ አልፎ-አልፎ አንዳንድ ጥቃቅን ችግሮች በውይይቱ የሚቀርቡ ከተገኙም ለወደፊቱ ችግሮቹ ታርመው እንዲሄዱና ደግመው እንዳይከሰቱ በውይይታቸው ላይ አጽድቀው ለቀጣይ 15 ቀናት የራሳቸውን የስራ እቅድ ይይዛሉ፡፡ በመጨረሻም አሰተያቶች ቀርበው ውይይቱ ይጠናቀቃል፡፡ አስተያየቶቹ የሚሰጡት ውይይቱ ተካፋዮች ከተሰጡ በኋላ መደረክ መሪው አስተያየቱን ሰጥቶበት ውይይቱ ይጠናቀቃል፡፡

5.9 ትምህርትና የመማማር ሂደት

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ትምህርትን እንደ አንድ የገቢ ማስገኛ ምንጭ በመቁጠር ለትምህርት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ከወላጆቻቸው ምንም ዓይነት የትምህርት እድል አላገኙም፡፡ በ1978 ዓ.ም በተሰባሰበ ሁኔታ መኖር ሲጀመር ከማህበር አባላቱ መካከል ጥቂቶቹ ወጣቶች በመሰረተ ትምህርት ባገኙት ትምህርት ማንበብና መጻፍ የጀመሩ ነበሩ፡፡ ክቡር ዶክተር ዙምራም *"ወላጆቻችን እኛን ባያስተምሩን ጎድተውናል፡፡ ይህን ደግሞ ወላጆቻችን አላስተማሩንም ብለን እኛ እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ የለብንም፡፡ በአንዳንዶቻችን ላይ ያለውን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ተጠቅመን የእርስ በርስ ትምህርታችንን መቀጠል ይኖርብናል"* በማለት የእርስ በርስ የመማማር ተግባሩ የተሻለውን ለአስተማሪነት በመምረጥ ተጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ከትንሽ እስከ ትልቅ ያለው አባላት ሁሉ በእርስ በርስ ትምህርቱ ላይ ተሳታፊ ሆነ፡፡

ክቡር ዶክተር ዙምራ በመቀጠልም ወላጆቻችን እኛን ባያስተምሩንም እኛ ደግሞ ይህን በልጆቻችን ላይ መድገም የለብንም፡፡ እኛው በእኛው ከምንማማረው ትምህርት በተጨማሪ ህጻናት ወደ መደበኛው ትምህርት ገብተው ትምህርታቸውን እንዲማሩ እናድርግ ብሎ ከማህበረሰቡ ጋር በመመካከር በ1980 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ጥቂት ህጻናት ወደ መደበኛው ትምህርት ገብተው እንዲማሩ ማድረግ ተጀመረ፡፡

ከ1980-1981 ማህበረሰቡ ስደት ላይ ስለነበር ሁኔታው የመማር አለመማር ጥያቄ የሚጠየቅበት ሳይሆን የመኖር ያለመኖር ትንቅንቅ በመሆኑ የመማማር ሂደቱም እንቅፋት ገጥሞት የተጀመሩት የመማማር ጅምሮችና ሌሎችም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች መሰንካከል ደርሶባቸዋል፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ክስተት ምክንያት የመኖር አለመኖር ጥያቄ መልስ እስኪያገኝ የርስ በርስ የመማማሩም ሂደትም ሆነ የህጻናት የመደበኛ ትምህርት ከ1980- 1981 መጨረሻ ድረስ ለሁለት ዓመታት ያህል መቋረጡ ግድ ሆኗል፡፡

በ1982 ስደት ላይ የመኖር አለመኖር ጥያቄው በተወሰነ መልኩ መረጋጋት አግኝቶ ጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ማግኘት ባይቻልም ነጭ አፈርን እንደ-ጠመኔ፣ ብረት ምጣድን እንደ ጥቁር ሰሌዳ በመጠቀም የመማሪያ ክፍል እስኪሰራ ድረስ ከዛፍ ጥላ ስር የእርስ በእርስ

የመማማር ሂደቱ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ ከእርስ በእርስ የመማማር ሂደቱ ጎን ለጎንም ተቋርጦ የነበረው የህፃናት መደበኛ ትምህርት እንዲያገኙ የማድረግ ጅምር እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

ከጊዜ በኋላም በአካባቢው በሚገኝ ግብዓት ትንሽ የመማሪያ ክፍል በመስራት ከድንጋይና ከጭቃ ከተሰሩ ያማሩ ወንበሮች፣ በመጠቀምና ከወረዳው ት/ጽ/ቤት ጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ በመጠየቅ የእርስ በርስ የመማማር ሂደቱን ለማስቀጠል ተችሏል፡፡ በዚህ ጊዜ የአገሬው ተወላጆችም “ለካስ እንዲህም ሆኖ መማር ይቻላል” ብለው ከማህበረሰቡ ጋር አብረው የሚማሩበትን እድል አመቻችተው ትምህርታቸውን ቀጥለዋል፡፡ በዚህ የእርስ በርስ የመማማር ሂደት ላይ ክቡር ዶክተር ዙምራም አንዱ ተሳታፊ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ በመማማር ሂደቱ ለተወሰነ ጊዜ አብሮ ሲከተል ከቆየ በኋላ ትምህርቱ እየተሰጠ መሆኑን ይረሳና በራሱ ዓለም ጭልጥ ብሎ ይሄዳል፡፡ አስተማሪው ለተማሪዎቹ የሚሰሩት ስራ ሰጥቷቸው ሲሰሩ ዙምራ ደግሞ አሁንም የተሰጠውን ስራ መስራቱን ያቋርጥና በራሱ ሀሳቡ ተመልሶ ይሰምጣል፡፡ የሚሰራ ስራ የተሰጠ መሆኑን የሚያስታውሰው አስተማሪው *የክፍል ስራውው ሰራህ?* ብሎ የጠየቀው እንደሆ ነው፡፡ ክቡር ዶክተር ዙምራም ይህ ሁኔታ እየተደጋገመ ሲያስቸግረውና ዓይኑንም ስለሚያመው በመማማር ሂደቱ ላይ ያለውን የግሉን ተሳትፎ ያቋረጠው ቢሆንም የሌሎችን የማህበረሰቡን አባላት የመማማር ሂደት ቀጣይነት እንዲኖረው የዕለት ተዕለት የማበረታታቱን ጉዳይ ወደኋላ አላለም፡፡

በ1986 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ማህበረሰቡ ከስደት ተመልሶ ወደ አውራ አምባ ሲመጣ የማረፊያ ቦታና ሌሎች በርካታ ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በመከሰታቸው የእርስበርስ የመማማር ሂደቱና የመደበኛ ትምህርቱ መስተጓጎላቸው አልቀረም፡፡ በዚህ ወቅት ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ማስቀጠል ሳይሆን ስደት ላይ ተከስቶ እንደነበረው የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ሆኗል ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ፡፡

በ1987 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የተጋረጡትን ዘርፈ ብዙ ውስብስብ ችግሮች በመታገል የርስ በርስ የመማማር ሂደቱን መቀጠል መጀመሩ ማህበረሰቡ ለትምህርት ለሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ማሳያ ነው፡፡ የመደበኛ ት/ቤቶች ማህበረሰቡ ከሚኖርበት ቦታ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀው መገኘታቸው በስደት ጊዜ የመደበኛ ትምህርታቸውን ጀምረው የነበሩት የተወሰኑ ተማሪዎች እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ትምህርታቸውን ከአንድ ዓመት ማቋረጥ በኋላ እንዲቀጥሉና ሌሎችም አዲስ ገቢ ተማሪዎችም ወደ ት/ቤት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይህ ሁኔታ እሰከ 1993 ዓ.ም ድረስ የመደበኛ ትምህርት የመማር ሂደት በአስቸጋሪ ሁኔታ ነው የቀጠለው፡፡

የአጸደ-ህጻናትና የርስ-በርስ ትምህርት ቤት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ

በዚህ መሰናክሎቹ በበዙባቸው ዓመታት የመደበኛ ትምህርት መማር የነበረባቸው ሁሉም የማህበረሰቡ ልጆች በመደበኛ ትምህርት መሳተፍ ባይችሉም እርስ በርስ የመማማር ሂደቱ ውስጥ ያለፉና ትምህርቱም ቀጣይነት ያለው በመሆኑ በዚህ የትምህርት ሂደት ላይ ያለፉት የማህበረሰቡ አባላት የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ማግኘት ከሚችሉት እውቀት፣ አመለካከትና ክህሎት ባልተናነሰ መልኩ ማግኘት ችለዋል፡፡ በመሆኑም ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት የሚችሉ ናቸው፡፡

ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ግን በማህበረሰቡ ላይ ተጋርጠው የነበሩት ዘርፈ ብዙ ውስብስብ ችግሮች ደረጃ በደረጃ እየተቀረፉ መምጣት በመጀመራቸው ሁሉም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ የማህበረሰቡ ህፃናት በማህበረሰቡ መዋዕለ ህጻናት ፊደሎችን ለይተውና ከማህበረሰቡ እሴቶች ጋር ተዋውቀው ወደ መደበኛ ት/ቤት በመግባት የመደበኛ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን የሚከታተሉት ከመኖሪያ ቦታቸው በ2 ኪሎ ሜትር ርቀት ገደማ ወንዝ ተሻግረው ሄደው ነው፡፡ ይህ ት/ቤትም ከ1-4ኛ ክፍል ነው፡፡ ህጻናቱ 4ኛ ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ የቀጣዩን የክፍል ደረጃ ትምህርት ለመከታተል የሚችሉት ከ8-15ኪ.ሜ ገደማ ተጉዘው ነው፡፡ የ8 ኪሎ ሜትር ርቀት ወዳለው ት/ቤት ተማሪዎቹ የሚሄዱት በየቀኑ በእግር እየተመላለሱ በመሆኑ በተማሪዎቹ ላይ የድካም ስሜት ስለሚኖር በትምህርት ውጤታቸው ላይ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ 15 ኪ.ሜ የሚጓዙት ደግሞ በየሳምንቱ ስንቃቸውን ተሸክመው በመመላለስ ነው ትምህርታቸውን የሚከታተሉት፡፡ ይህም ህጻናቱ ገና እድሜያቸው ሳይጠናና ክፉና ደጉን በደንብ ሳይለዩ ያን ያህል ርቀት ከቤተሰብ ተለይቶ ካደጉበት ማህበረሰብ የተለየ ባህልና ልምድ ወዳለበት ቦታ ሂዶ በስንቅ መማሩ በህጻናቱ ላይ የስነ-ልቦና ችግር ማሳደርና በትምህርታቸውም የተፈለገውን ያህል ውጤት ለማምጣት አስቸጋሪ ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡

ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ግን በ2 ኪሜትር ርቀት ገደማ የሚገኘው ከ1ኛ-4ኛ ክፍል የሆነው ት/ቤት ወደ ሙሉ ሳይክልነት ደረጃ ያደገ በመሆኑ በቦታ እርቀት ምክንያት ይቸገሩ የነበሩት የአውራ አምባ ማህበረሰብና የአካባቢው የ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ችግር በተወሰነ ደረጃ ተቀርፏል፡፡ ሆኖም የአውራ አምባ ማህበረሰብ ተማሪዎች በጧት በማታ ከክቡር ዶክተር ዙምራ ጋር እየተገናኙ የዙምራን አስተሳሰብ ለመውሰድ የተመቻቸ ሁኔታ ቢያገኙም ከአውራ አምባ ማህበረሰብ ውጭ ያሉት በዚሁ ት/ቤት በመማር ላይ የሚገኙት የአካባቢውና የአጎራባች ቀበሌዎች ተማሪዎች ደግሞ የክቡር ዶክተር ዙምራን አስተሳሰብ በቅረበት ሆነው ለመውሰድ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አይደሉም፡፡

ክቡር ዶክተር ዙምራ ገና ከልጅነት እድሜው ጀምሮ ሀሳቡን ለተማሩ ሰዎች ለማድረስ ህይወቱን መስዋዕት አድርጎ ሲታገል ቆይታል፡፡ ከብዙ ትግል በኋላ በ1964 ዓ.ም ሀሳቡን የሚረዱለት አጋሮች አግኝቶና ማህበረሰብ መስርቶ ሀሳቡን ከተረዱለት ማህበረሰቡ ጋር ሆኖም ማህበረሰብ እስኪመሰርትበት ጊዜ ድረስ ካለው ባልተናነሰ መልኩ እስከ 1993 ዓ.ም ሀሳቡን ለተማሩ ሰዎች እስኪያደርስ ድረስ የህይወት መስዋእትነት የመክፈል ሂደቱን ቀጥሏል፡፡ በ1993 ዓ.ም ሀሳቡ ሚዲያ ላይ መዋል ሲጀምር ከመሰረተው ማህበረስብ በተጨማሪ የተማሩ ሰዎች ወደ እሱ እየመጡ እየጠየቁና ሀሳቡን እየተረዱለት ይገኛሉ፡፡ ይህን ሀሳቡን በበለጠ ለሰው ልጆች እንዲዳረስና ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ የተማሩ ሰዎችን ወደ እሱ እንዲቀርቡና ሀሳቡን ተረድተው ወደ ህዝቦቻቸው እንዲያስተላልፉለት ማድረግ ነው፡፡ የተማሩ ሰዎችን ለማቅረብ ደግሞ ት/ቤት በአካባቢው መክፈት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አዲስ ራዕይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት በክልሉ መንግስት የተገነባና በ2002 ዓ.ም ስራ የጀመረ

የተማሩ ሰዎችን ወደ አካባቢው ለማቅረብና ከላይ የተጠቀሱትን የትምህር ችግሮች ለመፍታት ይቻል ዘንድ ማህበረሰቡ በአካባቢው አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ት/ቤት ተከፍቶ የማህበረሰቡንና በአካባቢው ያሉ ህጻናት በአቅራቢያቸው ሆነው

የማህበረሰቡን መልካም እሴቶች በህጻናቱ ሰርጸው እንዲሄዱ ለማድረግ ለክልሉ መንግስት ጥያቄ አቀረበ፡፡ የክልሉ መንግስትም ጥያቄውን በመቀበል በ2002 ዓ.ም ደረጃውን የጠበቀ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳክል ት/ቤት ገንብቶ በማጠናቀቅ በዚሁ ዓመት ስራ እንዲጀምር አድርጓል፡፡ ት/ቤቱ ስራ ሲጀምርም የነበረው የክፍል ደረጃ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ነው፡፡

የማህበረሰቡ ተማሪዎች በሰልፍ ወደ ት/ቤት ሲሄዱና ወደቤታቸው ሲመለሱ 2002 ዓ.ም

ማህበረሰቡ የ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ት/ቤት በቦታው መከፈቱን እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር በ2002 ዓ.ም ደግሞ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤትም በአካባቢው መከፈት እንዳለበት በማመን የ2ኛ ደረጃ ት/ቤትን አስፈላጊነት ከአካባቢው ማህበረሰብና እንዲሁም ከአጎራባች ቀበሌዎች ጋር ሰፊ ውይይት አካሂዷል፡፡ ከውይይቱም በኋላ የውይይቱ ተሳታፊዎችም ት/ቤቱ መከፈት እንዳለበትና የበኩላቸውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብም ያለችውን ጥቂት መሬት ቀንሶ ለት/ቤት ግንባታ የሚሆን ቦታ በማመቻቸት ግንባታው እንዲፈቀድለት የወረዳውን አስተዳደር ጠይቆ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ ከዚያም ወደስራው በመግባት ከሰኔ መጨረሻ እስከ ነሐሴ መጨረሻ 2002 ዓ.ም ድረስ ባሉት ሁለት ወራት እልህ አስጨራሽ የስራ ርብርብ በኋላ 4 መማሪያ ክፍል ያለው አንድ ብሎክ ለመገንባት ተችሏል፡፡

አዲስ ራዕይ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት (በማህበረሰቡ የተገነባና በ2003 ዓ.ም ስራ የጀመረ)

ይህ ት/ቤት በ2003 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ተከፍቶ 180 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ችሏል፡፡ በመቀጠልም አንድ የቤተ-ሙከራ ብሎክ፣ አንድ የቤተ-

መጻህፍት ብሎክና አንድ የአስተዳደር ብሎክ ተገንብቷል፡፡ በ2004 ዓ.ም ደግሞ አንድ ባለ 4 ክፍል መማሪያ ብሎክ፣ 3 መጸዳጃ ቤቶች ተገንብተዋል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን ግንባታዎች ለመገንባት ጉልበትን ጨምሮ 2,630,909.75 ብር ወጭ ሆኗል፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቱን ገንብቶ ካጠናቀቀ በኋላ ለመንግስት አስረክቧል፡፡ በዚህ ት/ቤት ትምህርታቸውን የሚከታተሉት የአውራ አምባ ማህበረሰብ ተማሪዎች ቁጥር 10 ከመቶው እንኳ አይሞሉም፡፡ ከ90 በመቶው በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች ከአውራ አምባ ማህበረሰብ ውጭ ያሉ ናቸው፡፡

<u>ለግንባታው የተሳተፉት አካላትና የተሳትፏቸው መጠን</u>

- የወጅ አውራ አምባ ቀበሌ አስተዳደር 34,613 ብር
- የአካባቢው ህብረተሰብ 45,730 ብር
- የፎገራ ወረዳ አስተዳደር 260,346 ብር
- የአውራ አምባ ማህበረሰብ 2,290,220.73 ብር

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ለዚህ ት/ቤት ግንባታ ከ87% በላይ የሚሆነውን ወጭ ሸፍኗል፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ት/ቤቶችን ለመክፈት የተነሳሳባቸው ሁለት ዓላማዎች ናቸው፡፡

1. የማህበረሰቡን እሴቶችና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር
   - ✓ ዙምራን የተማሩ ሰዎች እንዲቀርቡት እና ሀሳቡን በመረዳት ለሌላው ማስፋት እንዲችሉ
   - ✓ የማህበረሰቡን እሴቶች ወደሌላው ማህበረሰብ ለማስተላለፍ እንዲቻል
   - ✓ የመልካም ስነምግባር ባለቤት የሆኑ፣ ስራ ወዳድ፣ ስራ ፈጣሪ እና ለሀገሪቱ አምባሳደር ሊሆኑ የሚችሉ ትውልዶች እንዲፈጠሩ
   - ✓ የአውራምባና የአካባቢውን ማህበረሰብ የእርስ በርስ ግንኙነት ለማጠናከር
   - ✓ የተሞክሮ መፍለቂያ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል ለማድረግ

2. የአካባቢውን ማህበረሰብ የትምህርት ችግር ለመፍታት
   - ✓ በቦታ ርቀትና በኢኮኖሚ እጥረት ምክንያት ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ የሚችሉ ተማሪዎችን በቅርበት እንዲቀጥሉ ለማስቻል
   - ✓ ተማሪዎች ከቦታቸው ርቀው ሲሄዱ ያልተለመዱ ጠቃሚ ያልሆኑ ልምዶችን ይዘው ይመጣሉ በሚል ስጋት ወላጆቻቸው የሚያስቀሯቸውን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ለማስቻል
   - ✓ የአካባቢውን ማህበረሰብ ለትምህርት ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ
   - ✓ በረጅም ርቀት ጉዞ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለማስቀረት

5.10 ኪነ-ጥበብ

የአውራ አምባ ማህበረሰብ በ1979 ዓ.ም የኪነት ቡድን በማደራጀት የማህበረሰቡን እሴቶች የሚያንጸባርቁ ግጥሞች በማህበረሰቡ አባላት እየተገጠሙ ማህበረሰቡን እያዝናና ትምህርት ለማስጨበጥ የማድረግ ሙከራ ተጀምሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ለረጅም ዓመታት ዘርፈ ብዙ ችግሮች በማህበረሰቡ ላይ በመጋረጣቸውና ምቹ ሁኔታዎች ባለመፈጠራቸው ምክንያት የኪነት ቡድኑ የሚጠበቅበትን ለመወጣት አልቻለም፡፡ የኪነት ቡድኑ በተጠናከረ መልኩ እንደገና ተደራጅቶ የተሻለ ስራ እንዲሰራ የተደረገው ከመስከረም 1995 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኪነት ቡድኑ ስለልማት፣ ስለአገር እድገት፣ ስለሰው ልጆች ክብር፣ ስለሴቶች እኩልነት፣ በሰው ልጆች መካከል መኖር ስላለበት ፍቅር፣ ስለመረዳዳት፣ ስለሰላምና በመሳሰሉት ጭብጦች ዙሪያ ግጥሞች እየተገጠሙ የሚቀነቀኑበትና ማህበረሰቡን እያዝናኑ ትምህርት የሚሰጡበት መድረክ ተዘርግቷል፡፡

ይህ የማቀንቀኑና የማዝናናቱ ተግባር በየዓመቱ በሚመጣው የዘመን መለወጫ አዲስ ዓመትና ጊዜያዊ መድረኮች ላይ ድምቀት ሰጥቶ ይውላል፡፡ የኪነት ቡድኑ አባላት የዘመን መለወጫው ሲቃረብ ማህበረሰቡን ለማዝናናትና ለማስተማር ቅድመ-ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ በተወሰኑ ቀናት ዝግጅቱ ይጠናቀቅና በዘመን መለወጫው ዕለት ታዳሚውን የተለያዩ ጣዕመ ዜማዎችንና ውዝዋዜዎችን በማቅረብ እያዝናኑ ትምህርት ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ቀን ከኪነት ቡድኑ በተጨማሪም የማህበረሰቡ አባላት እንደየችሎታቸው ልዩልዩ ስነ-ጽሁፎችንና ውዝዋዜዎችን በማቅረብ እያዝናኑ ትምህርት የመስጠቱን ሒደትን እንዲደምቅ ያደርጋሉ፡፡ ውዝዋዜው ሁሉንም የማህበረሰቡን አባላት በየተራ ሳይነካ አያልፍም፡፡

ይህን ፕሮግራም እሚታደሙት የአውራአምባ ማህበረሰብ አባላት ብቻ ሳይሆኑ በዙሪያው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችም ከየአቅጣጫው እየጎረፉ ከማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀል ይዝናናሉ፡፡ የኪነት ቡድኑ ከሚያቀነቅኑት ዜማም ትምህርት ያገኛሉ፡፡ የራሳቸውን ዘፈንና ውዝዋዜም ፕሮግራም ተይዞላቸው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ይህም በዙሪያው ባለው የህብረተሰብ ክፍልና በአውራ አምባ ማህበረሰብ መካከል ለዓመታት ሻክሮ የነበረው ግንኙነት እንዲፈታና የሰላም መስመር ለመዘርጋት አመቺ ሆኗል፡፡

የኪነት ቡድኑ በዘመን መለወጫ ታዳሚውን ሲያዝናና (2006-2007 ዘመን መለወጫ)

5.11 የጋብቻ ስነ ስርዓት

በማህበረሰቡ ጋብቻ የሚመሰረተው በሁለቱ ተጋቢዎች ነጻ ፍላጎት ታዘልቀኛለች ያዘልቀኛል ተባብለው ነው፡፡ በሁለቱ ፍላጎት ጋብቻው ከተፈጸመ ለትዳራቸው መሰረት ይጥላሉ፡፡ ጠለፋንም ያስቀራል፡፡ በወላጆች ተገደው ጋብቻው የተፈጸመ ከሆነ ጋብቻው ቀጣይነት አይኖረውም፡፡ የልብ ፍላጎት አይደለምና፡፡ ትዳሩ በሚመሰረትበት ጊዜ እድሜያቸው ዘለግ ማለት አለበት፡፡ እድሜያቸው ለጋ ከሆነ አስተሳሰባቸውም ለጋ ስለሚሆን ነው፡፡ ጋብቻ ሲመሰረት ሴቷ 19 ዓመትና በላይ ወንዱ ደግሞ 20 ዓመት በላይ መሆን አለበት፡፡ ይህም የተደረገውም ትዳራቸውን የሚመሰርቱት ተጋቢዎች በራሳቸው ማመዛዘን እንዲችሉ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ከጋብቻ በፊት ወንዱም ሴት፣ ሴቷም ወንድ አያውቁም፡፡ ከጋብቻ በኋልም ከትዳር ጓደኛቸው ውጭ አይሄዱም፡፡ ይህን አልፈው የሚሄዱ ከሆነ የሰማኒያ ትርጉሙ ምንድነው? ከሌሎች እንስሳት በምን እንለያለን? ሰማኒያ ትልቅ ህግ ነው፡፡ ሌሎች እንስሳት ሰማኒያ አያውቁም እንደፈለጉ ነው እሚሄዱት፡፡ እኛ ሰዎች ግን ሰማኒያ አለን፣ በእቅድ እንመራለን፣ ጎጅና ጠቃሚ ነገሮችን ለይተን እናውቃለን፡፡

ተጋቢዎቹ ትዳራቸውን በሚመሰርቱበት ጊዜ በአካባቢ በተገኙ ሽማግሌዎች አማካይነት የውል ፊርማቸውን ይፈራረማሉ፡፡ በማህበረሰቡ አጋቢ አፋች ተብሎ የተቀመጠ ሽማግሌ የለም፡፡ ማንኛውም በአካባቢው የተገኘ ወንድም ሆነ ሴት ሊያፈራርማቸው ይችላል፡፡ ተጋቢዎቹ ተፈራርመው ትዳራቸውን ከመሰረቱ በኋላ እኔ ሙሽራ ነኝ ብሎ መቀመጥ የለም፡፡ ጋብቻው እንደተፈፀመ ሁለቱም ወደ ስራ ነው እሚሄዱት፡፡ ሰርግ የሚባል ነገር አይታወቅም፡፡ ሻይም እንኳ አይፈላም፡፡ ከሩቅ የመጣ እንግዳ ከሆነ ግን ምሳውን በልቶ ይሄዳል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በብዙ ዘመናት የተሰበሰበውን ገንዘብ በሰርግ ምክንያት ማውደም አስፈላጊ ባለመሆኑ ነው፡፡ ይልቁንም ለሰርግ ተብሎ የሚወጣውን ወጪ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሁለቱ ተጋቢዎች መቋቋሚያ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ሰርግ ለጠለፋም መንስኤ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ቤተሰቦቹ ለሰርግ የሚያወጡት ገንዘብ ባይኖራቸው በትዳር ለመተሳሰር ፍላጎት ያላቸው ተጋቢዎች ጋብቻቸው በገንዘብ እጥረት ምክንያት እንደሚቀርባቸው ሲያውቁ ጠለፋን እንደመፍትሄ ሊጠቀሙ ስለሚችሉ ነው፡፡

የተጋቢዎቹ የመኖሪያ ቦታ ምርጫ የሁለቱ ስምምነት ይሆናል፡፡ ጥንዶችም በመረጡት መኖሪያ ቦታ ሆነው ተዋደው ተከባብረውና ተዛዝነው አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ ተባብለው ቤታቸውን ሁለቱም በእኩልነት እየተወያዩ ያስተዳድራሉ፡፡

በማህበረሰቡ ጋብቻ አንድ ለአንድና ቋሚ ነው፡፡ ይህም የሚወልዷቸውን ልጆች መብት እንዲጠበቅና መሰረታቸውንም እንዳይንዱ ያደርጋል፡፡ ሁለቱ ባለትዳሮች ልጆች ከወለዱ በኋላ ቢለያዩ የልጆቻቸውን መብት ለመጠበቅ አያስችልም፡፡ ልጆች ከወለዷቸው እናት አባታቸው ጋር ማደግን ይመርጣሉ፡፡ መለያየት ከመጣ ደግሞ ከእናታቸው ጋር ቢሄዱ አባታቸውን ያጣሉ፡፡ ከአባታቸውም ጋር ቢሄዱም እንዲሁ እናታቸውን ያጣሉ፡፡ በመሆኑም ትዳር በተልካሻ ምክንያት እንዲፈርስ አይደረግም፡፡ ነገር ግን ባለትዳሮች አብሮ ሊያኖራቸው የማያስችል ችግር ከገጠማቸው ትዳራቸው ሊፈርስ ይችላል፡፡ ትዳርን ሊያፈርሱ የሚችሉ ችግሮችም፡-

- ✓ በህክምና የማይድን ለግብረ-ስጋ ግንኙነት የማያበቃ ችግር ከተከሰተ
- ✓ በሁለቱ መካከል ሊፈታ ያልቻለ ቀጣይነት ያለው ጭቅጭቅ ከተፈጠረ
- ✓ ከባለትዳሮች መካከል አንደኛው ለማህበረሰቡ ውስጠ-ደንብ ተገዥ ካልሆነና
- ✓ ከባለ ትዳሮቹ መካከል የመካንነት ችግር ከተከሰተ ናቸው፡፡

በማህበረሰቡ ትዳር ሊፈርስ የሚችለው በመጀመሪያ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የባለ ትዳሮችን ችግር ያየዋል፡፡ የባለትዳሮችን ችግር ኮሚቴው በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ችግራቸውን መፍታት ከቻለ እልባት ሰጥቶ ትዳራቸው ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ችግሩ ከኮሚቴው አቅም በላይ ከሆነና ችግሩን መፍታት ካልቻለ ችግራቸውን ለጠቅላላ የማህበረሰቡ አባላት ጉባኤ ያቀርባል፡፡ አባላቱ የባለትዳሮቹን ችግር እንዲሁ በጥልቀት መርምሮ ከላይ ከተዘረዘሩት ጋብቻን ሊያፈርሱ ከሚችሉት ችግሮች ውጭ ከሆነ ባለትዳሮቹን መክሮ ትዳራቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡ ችግሮቻቸው ከላይ ከተጠቀሱት ትዳርን ሊያፈርሱ የሚችሉ ከሆነ ደግሞ አባላቱ ትዳራቸው እንዲፈረስ ይወስናል፡፡ ጋብቻቸው የፈረሰ ባለትዳሮች በቤታቸው ያፈሯቸውን ገንዘብና ንብረት መኖሪያ ቤትን ጨምሮ እኩል እንዲካፈሉ ይደረጋል፡፡

5.12 እምነት

የአውራ አምባ ማህበረሰብ ሰማይና መሬትን፣ ሌትና ቀንን፣ ሴትና ወንድን አየርን፣ ፀሀይንና ሁሉንም በመሬት ላይ ያሉ ነገሮችን የፈጠረ አንድ ፈጣሪ እንዳለና እምነትም የሚገለፀው በበጎ ስራ እንደሆነ ያምናል፡፡ በመሆኑም በራስ ላይ እንዲደረጉ የሚፈለጉትን መልካም ነገሮች በሰዎች ላይ እንዲደረጉ በማድረግና በራስ ላይ እንዳይደርሱ የሚፈለጉትን መጥፎ ድርጊቶች በሰዎች ላይ እንዳይፈጸሙ እያደረገ ነው እሚኖረው፡፡

ማህበረሰቡን ለመጎብኘት የሚመጡ ጎብኚዎች የማህበረሰቡን መስራች ዙምራን ስለ እምነት ሲጠይቁት እንዲህ በማለት ነው መልስ እሚሰጣቸው፡፡

ስለ እምት ብትጠይቁኝ አልተማርኩም፡፡ ስለቀለም ትምህርትም አልተማርኩም፡፡ ዕድሉን አላገኘሁትም፡፡ ስለእምነት መናገርም አልፈልግም፡፡ ስትጠይቁኝ ጠይቄ የተረዳሁትንና የያዝኩትን መናገሬ ስለማይቀር ነው እንጅ፡፡

እናቴ ስለእምነት በሁለት ዓመቴ ነው የጠየቀው እምትለኝ፡፡ እኔ ሁለት ዓመቴ መሆኑን አላውቀውም፡፡ ግን ሃሳቡን መግለጤን አውቃለሁ፡፡ እንዲያውም ለኔ ታሞ፣ አብዶ፣ ሀሳቡ ከሰው ተለይቶ ነበር እምትለኝ፡፡ ይህንን ስትናገር የሰማኋት በ1964 ዓ.ም እነዚህን ሰዎች አግኝቼ ከነሱ ጋር በምወያይበት ጊዜ ለነሱ ስትናገር ነው፡፡ እናቴ በ6 ወሩ ቆሞ ሄደ፣ በሁለት ዓመቱ የመጠየቅና የመመለስ አቅሙ እንደትልቅ ሰው ነበር ትለኛለች፡፡

ሁለት ዓመት ሲሆነኝ ወደ ጎረቤታችን ሰዎች አንዳንዴ እንሄድ ነበር፡፡ የኔ ወላጆች ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ግን ክርስቲያን ዘመዶች አሏቸው፡፡ በአንድ መንደር ነው የተቀመጡት፡፡ ቡና በአንድ ይጣጣሉ፡፡ በስራ ላይ በወንፈል እየተወናፈሉ ይውላሉ፡፡ እኛ ልጆች ደግሞ በአንድ ነው እየተጫወትን የምንውለው፡፡ አንድ ቀን ከክርስቲያን ጎረቤቶቻችን ቤት ሄጄ ልጆች ምግብ ሲበሉ አገኘኋቸው፡፡ ወላጆቼ ቢኖሩ አይሰጡኝም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሙስሊም መሆኔን ስለሚያውቁ፡፡ ልጆቹ ደግሞ እንደኔ አያውቁም፡፡ ምግቡ የስጋ ምግብ ነው፡፡ እኔ የስጋ ምግብ እንጅ ክርስቲያን ሙስሊም እሚባል አላውቅም፡፡ ያችን ምግብ እየጣመችኝ ግጥም አድርጌ እበላና እዛው ጨርሼ ብሄድ ጥሩ ትራፊዬን ይዤ ወደቤቴ እመለሳለሁ፡፡

እናቴ ስታየኝ እንዲህ አለችኝ

- እሱን ስጋ ከምን አገኘኸው?

እኔም እንዲህ ስል መለስኩላት

- እንደኔ ይጥማታል ብዬ ከነእተዋ ዘንድ ልጆቹ ሰጥተውኝ፡፡

አወይ የክርስቲያኑን ስጋ! ብላ ያችን ስጋ እኔን እየጣመችኝ እያለች እጄን እንዳይነካት በቅጠል ነገር አንጠልጥላ እኔን ከእጄ ቀምታ ወደ ደጅ ወረወረችብኝ፡፡ አይኔ ስጋዬ ጋር ሲሄድ ዶሮ ስትነጭ ውሻ ቀምታ ትሄዳለች፡፡ እሷ ደግሞ የክርስቲያን ስጋ ነክቼ እቃ እንደልነካባት እጄን ታጥባለች፡፡

እጄን እየታጠብኩ፡፡

- እናቴ ስጋዬን የቀማሽኝ ለምንድን ነው?
- የክርስቲያን ስጋ ሆኖ፡፡
- ክርስቲያን ማለት ምንድነው?
- ሰው፡፡
- ታዲያ እኛ ምንድን ነን? ሰው አይደለንም?
- እኛማ ሙስሊሞች ነን ፡፡
- ሙስሊም ሰው አይደለም?
- ሰው ነው፡፡
- ታዲያ ሰው የበላውን አይደል የበላሁ ስጋዬን ለምን ጣልሽ?
- አንተ የክርስቲያን ስጋ አይበላም ነው የምልህ! ብላ ቆጣ ትላለች፡፡
- ክርስቲያን የምን ስጋ ነው የሚበላው? እላለሁ ሃሳቤን ቀይሬ፡፡
- የከብት

- እኛ የምን ስጋ ነው የምንበላው?
- የከብት
- ሁላችንም የከብት ስጋ ከበላን ሁላችንም ሰው ከሆን ስጋዬን ለምን ቀማሽ?

ብዬ ስጠይቃት መልስ አልሰጠችኝም፡፡ አባቴ ትንሽዬ የቃልችነት ትምህርት ተምሯል፡፡ አጠገባችን ሆኖ ቃለ-ምልልሳችንን ከሰማ በኋላ አሁንስ እኛ የማንመልሰው ጥያቄ ነው የተጠየቅሽው ይልና እዛው መልሽ ብሎ ትቷት ሄደ፡፡ ከዚያማ እኔም እሷን አልጠየቅኳትም፡፡ እንኳንም ሁላችንም የከብት ስጋ በላን፡፡ እንኳንም ሁላችንም ሰው ሆንን ብዙም አልገረመኝ፡፡ የገረመኝ ቢኖር ሁላችንም ሰው ሆነን ሳለ አንዱ ሙስሊም አንዱ ክርስቲያን መሆናቸው ነው፡፡ ሙስሊም ክርስቲያን የሚባለው ነገር ብቻ ግን በጣም ገርሞኛል፡፡ ምንድነው ሙስሊም ክርስቲያን ማለት? ስላቸው ያው ሙስሊም ክርስቲያን ነው ሌላ ምን ልትጠይቅ ፈለግህ? ይሉኛል፡፡ ይህን እያሉ ሲያስቸግሩኝ፡-

- መጀመሪያ ላይ ክርስቲያን እንዴት ተፈጠረ?
- ከአዳምና ሄዋን፡፡
- ሙስሊምስ?
- ከአደምና ሃዋ፡፡
- ሁለት ወንዶች ሁለት ሴቶች ናቸው የመጀመሪዎቹ ሰው ሲፈጠር የተፈጠሩት?
- አይደሉም፡፡ አንድ ወንድና አንድ ሴት ናቸው፡፡
- እንግዲያ ሁለት ወንድና ሁለት ሴት አደረጋችኋቸው እሳ አሁን?
- ይህማ የአገር ቋንቋ ነው፡፡ እንጅ እነሱ አንድ ወንድና አንድ ሴት ናቸው፡፡
- ሰው ሲፈጠር የተፈጠሩት አንድ ወንድና አንድ ሴት ናቸው ካላችሁ እምነት ደግሞ ከነሱ ጋ ከመጣ ከሁለቱ ሰዎች ከአዳምና ሄዋን መካከል ማንኛው ሙስሊም ማንኛው ክርስቲያን ነበሩ?
- እዚያ ጋ እኮ የለም ነበር፡፡
- እንግዲያ ኋላ እንዴት ሊፈጠር ቻለ?
- እምነት በብዙ ነባይቶች ሲወርድ ሲዋረድ ከቆየ በኋላ ነው እዚህ የደረሰው፡፡
- ሁለት ሆነው ነው ወይ አላህና እግዚአብሄር ሆነው ይህችን ዓለም እኛን ጨምረው ሲፈጥሩ?
- አይ ፈጣሪ እኮ አንድ ነው፡፡ ሁለት ሊሆን አይችልም፡፡
- እንግዲያ ስሙ ለምን ሁለት ሆነ?
- አላህ እግዚአብሄር የሚለው የአገር ቋንቋ ነው እንጅ ፈጣሪ አንድ ነው፡፡
- እሺ እምነትስ እንዴት ይገለጣል? ስላቸው
- እምነት በበጎ ስራ ነው የሚገለጠው፡፡ ሙስሊም ነኝ ክርስቲያን ነኝ ስላለ እምነት አይገኝም፡፡ ሲሉኝ

እምነት በበጎ ስራ የሚገለጥ ከሆነ፣ ፈጣሪ አንድ ከሆነ፣ ፈጣሪ አንድ ሆኖ እምነትን በበጎ ስራ እየገለጥን ሁላችንም የአንድ አዳምና ሄዋን ልጆች ከሆንን፣ የአንድ ሀረግ ፍሬዎች ከሆንን፣ ወንድማማች እህትማማች ሆነን ፈጣሪ አንድ ነው እምነታችን በበጎ ስራ ይገለጣል ብለን የማንሄድ? ለምን ፈጣሪ አንድ አይሆንም? ስም እያወጣን እምንሄድ ከሆነ ወዴት

እንደርሳለን ብለህ አልክ ትለኛለች እናቴ፡፡ ዛሬ ስም ማውጣት ስላልቻገረ እምነት ከሺህ በላይ ዘልቋል፡፡

ከፍ ስል ደግሞ ሀሳብህና ስራህ ሁሉ ጥሩ ነበር፡፡ ግን ቤተክርስቲያን ወይም መስጊድ ቢኖርህ? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ሀሳቡን ተስማማሁበት፡፡ በእጄ እምሰራው እስከሆነ ድረስ፡፡ ቤተ-ክርስቲያን ወይም መስጊድ መስራቱ አልከበደኝም፡፡ ይህን በእጄ እምሰራው ነገር ነው፡፡ ፈጣሪ የት ቦታ ነው ያለው? ቤት ልስራለት ስላቸው እሱማ የትም ቦታ ነው እሚገኘው አሉኝ፡፡ መኖሪያ አልቸገረውም ማለት ነው? አልኩና ላሳህስ የት ቦታ ነው ያለው ልስራለት? ስላቸው አላህ የትም ቦታ ግኝ ነው አሉኝ፡፡ በሀሳቡ ይስማማሉ፡፡ የሚለያዩት በስሙ ነው፡፡ እሱ የትም ቦታ ሆኖ እኔ አንድ ቦታ ላይ ቤት ሰርቼ ስወጣ የምዘጋው፣ ስገባ የምከፍተው ለማድረግ አእምሮዬ ይፈቅዳል ወይ? የእናንተ አእምሯችሁ ፈቅዶላችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ እሱ እኔን ይቆጣጠራል እንጅ እኔ እሱን እዚህ ግባ እዚህ ውጣ ብዬ ልቆጣጠር እችላለሁ ወይ? ይልቅስ እሱ የሰራን ህንፃ እኛ አይደለንም ወይ? ያ እኛ የሰራነው ነው፡፡ ለምን የሱ ቤተክርስቲያን /መስጊድ/ እኛ አንሆንም? እሱ ራሱ በሰራን አይን ያለው፣ ጆሮ ያለው፣ መነጋገሪያ ቋንቋ ያለው፣ ማሰቢያ ልብ ያለው፣ እጅ እግር ያለው አድረጎ የሰራን እኛን አይደለም ወይ? እኛም የትም ቦታ እሱም የትም ቦታ ነው እምንገኝ፡፡ የሞቀ አየር እያወጣ ቀዝቃዛ አየር እየመገበ የያዘን እኛ ጋር ሆኖ እንጅ ከሰራነው ቤት ሆኖ ነው?

እንደ አውራ አምባ ማህረሰብ እምነት ማለት ስለ ሰላም ማሰብና ሰላምን ፈጥሮ መሂድ ነው፡፡ የአውራ አምባ ማህረሰብ ሰላምን አልፎ ወደ ሌላ አይሄድም፡፡ ሰላምን ዘርግቶ፣ ደካማን ደግፎ፣ ሌላውን እንደራሱ ወዶ፣ ለራሱ እንዲሆንለት እሚፈልገውን ለሌላውም እንዲሆንለት አድርጎ፣ በራሱ ላይ እንዲሆን እማይፈልገውን በሌሎችም ላይ እንዳይደረስ አርቆ አስወግዶ ነው እሚሄደው፡፡ እና በጥቅሉ እምነታችን ይህን ይመስላል፡፡

በመቀጠልም ዙምራ የአውራ አምባ ማህረሰብ እምነት የለውም፡፡ ለሚሉ ሰዎች የቤት ስራዎችን ይሰጣል፡፡ የቤት ስራዎቹም፡-

- የአውራ አምባ ማህረሰብ እምነት የለውም እምንል ሰዎች የአውራ አምባ ማህበረሰብ ምን እያደረገ ነው? ምን እየተናገረ ነው? ምን እያሰበ ነው?
- እኛ እምነት አለን እምንልስ ሰዎች እኛ ምን እየሰራ ነው? ምን እየተናገርን ነው? ምን እያደረግን ነው?
- ጊዜስ ምን እየጠየቀ ነው?

5.13 የሀዘን ስነ-ስርዓት

እንደ አውራ አምባ ማህበረሰብ ሀዘን ማለት አንድ ሰው በህይወት እያለ በሰዎች መካከል ሆኖ ለሚገጥመው ችግር ዋስትና በመሆን ደስታውንም ሆነ ችግሩን በጋራ በመካፈል ሰውየው ከገጠመው ችግር መታደግ መቻል ማለት ነው፡፡ በማህበረሰቡ አንድ ሰው ለሌላው ሰው የደስታውም ሆነ የሀዘኑ ተካፋይ ነው፡፡ አንድ ሰው የገጠመው ችግር ካለ

ሰውየው ከችግሩ እንዲወጣ ከፈጣሪ በታች ማህበረሰቡ የቻለውን ሁሉ እንዲሚላለት ያደርጋል፡፡ በዚህም ሁኔታ ማህበረሰቡ ፀፀት የሌለበት ኑሮ ይኖራል ማለት ነው፡፡ እሚፈለገውም ይኸው ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ፈጣሪ ወደመሬት ያመጣውን ዕቃ መልሶ ከወሰደ ምን ማድረግ ይቻላል? ወደዚች ምድር መምጣት እንዳለ ሁሉ ሞት አይቀሬ ነው፡፡ ሲመጣ እንግዳ እየሆነብን ነው እንጅ፡፡ ከአቅም በላይ ሆኖ በማህበረሰቡ አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ከውስጥ የመነጨ ስሜት ነውና እንባ ማፍሰስ አይቀርም፡፡ ነገር ግን ወዮ እያሉ፣ ደረትን እየደቁ፣ ፊትን እየነጩ ሙሾ በመደርደር ማልቀሱ ያን የሞተን ሰው አይተካም፡፡ ሀዘን በማብዛት ሟቹን ወደ ህይወት መመለስ የሚቻል ቢሆን ኖሮ ሰውን ሁሉ ሰብስቦ ማስለቀስ ይቻል ነበር፡፡ ይልቁንም ሀዘን ማብዛት የሚያስከትለው ነገር ቢኖር ጉዳት ነው፡፡

1ኛ. ወገናችን ተጎዳን
2ኛ. ጊዜን ደግሞ ልንጎዳ ነው
3ኛ. በማይገኝ ነገር ላይ አእምሯችንን ጎዳን
4ኛ. የሟች ቤተሰብን ኢኮኖሚ ማድቀቅ ነው እሚሆነው፡፡

አስከሬኑ ወደ ቀብር ቦታ ሲሄድ

አባላት የሟች ቤተሰብን ሲያጽናኑ

የቀብሩ ስነ-ስርዓት የሚፈፀመው ይችላሉ በተባሉ ሰዎች ነው፡፡ የተረፉት የሟቹን ቤተሰብ ሲያፅናኑ ይቆያሉ፡፡ የቀብር ስነስርዓቱን ለመፈፀም የሄዱት ሰዎች ስነስርዓቱን አጠናቅቀው ከተመለሱ በኋላ የሟቹን ቤተሰብ ሀዘኑን እንዲረሱት ለማድረግ ወደ ስራ ይዘዋቸው ይሄዳሉ፡፡ እዚህ ላይ ሀዘኑ ያበቃል ማለት ነው፡፡ ከዚያ ጊዜ በኋላ ከየትም እየመጡ ለመርሳት የተሞከረውን ሀዘን እንደገና እያነሱ እንዲያስለቅሱ ማድረግ አይፈለግም፡፡ በሀዘኑ ጊዜ የሚሰባሰበው ሰው ገንዘብ እንዲያወጣም ወይም የሟች ቤተሰብ የተሰበሰበውን ሰው እንዲያስተናግድ አይደረግም፡፡ በስሚ ስሚ ከሩቅ ቦታ የሚያድር እንግዳ እንኳ ቢመጣ ማህበረሰቡ የራስ የራሱን አውጥቶ እንግዳውን ያስተናግዳሉ እንጅ

የሟቹን ቤተሰብ ሀብት እንብላ ማለት የለም፡፡ ሟቹ ከሞተ ጊዜም ጀምሮ ከሟች ቤተሰብ ቅንጣት ያህል የሚወጣ ገንዘብ የለም፡፡ የማቹ ቤተሰብ ገንዘብ ካለው ለልጆቹ ማሳደጊያ ይሆናል፡፡ ገንዘብ ከሌለውም የሟች ቤተሰብ መከፋት የማህበረሰቡም መከፋት ጭምር ስለሆነ ማህበረሰቡ የሟቹን ቤተሰብ ይረዳል፡፡ በጥቅሉ ሃዘን ማለት ህይወታችን ሳለ በቁም መረዳዳት ነው፡፡

6. ከጎብኚዎች አስተያየት

1. የዙምራ አስተሳሰብ ይህን ሁሉ ውጣ ውረድ ወጥቶ ወረዶ እቅዱ ከሞላ ጎደል ተሳክቶለት በማየቴ ደስ ሊለው ይገባል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት ያልተገኘ ከዚህም በኋላ ይመጣል ተብሎ የማይጠረጠር የፈጣሪ ቃል ነው ብዬ እደመድማለሁ፡፡ በርቱ ተበራቱ! በዚሁ ቀጥሉበት

   ማርታ አዲሱ

2. የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነኝ፡፡ በዚህ ሀጢያት በበዛበት ምድር እንዲህ ዓይነት ንጹህን ፍጡራንን በማየቴ በእጅጉ ገረመኝ፡፡ ምናልባት ሁሉም ሰው እንደነዚህ ሰዎች ቢያስብ ዓለማችን ምድራዊ ገነት በሆነች ነበር፡፡ እምነት በተግባር ካልዋለ አማኝ ነኝ ማለት ትርጉም የለውም፡፡ እግዚያብሄር አምላክ ሆይ በቸርነትህ ጠብቃቸው፡፡

   ክንዱ ፈንቴ (ህዝብ ማመላለሻ ስምሪት፣ ወረታ)

3. ዓለም በግሎባላይዜሽን ትስስር አንድ ሆናለች ከተባለ ሁሉም ዓለም የአውራ አምባን መንደር መሆን አለበት፡፡ አውራ አምባ ያልተማረ ግን ያስተማረ ማህበረሰብ፤ ዙምራ ደግሞ ትልቅ የምድር ገነትን የፈጠረ የምድር ትንቢተኛ፣ ብልህና ትጉህ ማህበረሰብ መፍጠር የቻለ ፈላስፋ ነው፡፡ አውራ አምባ ውስጥ ትልቅ መንፈስ አለ፡፡ ያ ትልቅ መንፈስ ዙምራና የዙምራ ፍልስፍና የሆነው ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ማዕድ ሁሉም ሊቋደስ ይገባል፡፡ እኛ አውራ አምባን ለመሆን ቆርጠናል፡፡

   የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የጤና ሙያተኞች

4. የተመለከትኩት ሁሉ በጣም የሚያስገርምና ሁሉም ማህበረሰብ ጊዜው ሳይመሽበት ትምህርት ሊወስድበት የሚገባ ነው፡፡ ምንም ማቅማማት ሳይገባን የአውራ አምባን ልምድ የራስ ልምድ በማድረግ እራስን መለወጥ ጊዜ የማይሰጠው ነው እላለሁ፡፡

   አበራ አስፋው

5. እውነተኛ ማንነት የሚገለፅበት፣ ሰዎች በጋራ፣ በሰላም፣ ተፈቃቅሮ፣ ተከባብሮ፣ በጋራ ሰርቶ በጋራ መኖር የሚቻልበት፣ ለዓለም ተሞክሮ መሆን የሚችል እውነትም የእውነት “አውራ አምባ”፡፡ ማህበረሰቡን ለማስተዋወቅ ያቅሜን እጥራለሁ፡፡

   ቢኒያም ደመረ (አዲስ አበባ)

6. ዙምራ እውነተኛ ዓለም ውስጥ ያለና የራሱን ዓለም ፈጥሮ እንደተባለው ብዙ የዓለም ምሁራን፣ ፈላስፎች፣ የዓለም መንግስታት እየተጨነቁበት በነበረው ግን ባልተሳካው ሀሳባቸው ውስጥ ሆነው የተጨነቁበትን የፈፀመው ይህ ማህበረሰብ በእውነት ከልብ የሚወደድ ነው፡፡ ከአሁን በኋላም የዚህ ዓላማ፣ የዚህ ፍልስፍና ተከታይ በመሆን እምነቴን ይገፍ ባለሁበት ዓለምና ቦታዎች ሁሉ የዚህን አቋም ለማራመድ ከጎናችሁ ነው፡፡ አውራ አምባ ለዘላለም ይኑር እኛም ተከታዮቹ፡፡

   አድማሱ ካሳ (በደላንታ ወረዳ ህዝብና መንግስት አካላት)

7. በንድፈ-ሀሳብና በጽሁፍ ብቻ ብዙ ታላላቅ ፈላስፎች ያሰፈሩትን ባልጠበቅኩትና ባላሰብኩት ሁኔታ በተግባር እየሰሩ ያሉ ሰዎችን ለማየት፣ ለማነጋገርና ታሪካቸውን ለማወቅ በመቻሌ እድለኛ ያድርገኛል፡፡

መኮንን ምንዳ (ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት)

8. በእውነት ከሆነ ይኸ ማህበረሰብ ኢትዮጵያን ሊወክል የሚችል ወይም የኢትዮጵ ስም በአውራ አምባ መጠራት አለበት የሚል ስሜት ይሰማኛል፡፡ ምክንያቱም እምነት፣ ስራ ባህል፣ መተሳሰብ፣ ስነ-ምግባር ሁሉም ማለት ይቻላል፡፡ ሎጂካል ናቸው፡፡ ማንኛውም ህብረተሰብ ሊቀበለው የሚገባው፡፡ ዙምራን አደንቃለሁ፤ የምድር መላእክም ብየዋለሁ፡፡

መ/ርት ፍሬህይወት ካሳ (ንጋት ት/ቤት፣ ባህር ዳር)

9. በህይወቴ ከአፍ ያለፈ ተግባር የተመለከትኩበት ብቸኛ ቦታ፡፡ አምላኬ ይህን የኢትዮጵያና የዓለም ሲሳይ ሊሆን የሚችል ማህበረሰብና የማህበረሰብ መስራች ሀሳብ ከሀገሬ አልፈህ ለዓለም በትንልኝ! ለኢትዮጵያ ትንሳኤ የሆነ ሀሳባቸውን ለዓለም አድርስ፡፡

አለማየሁ አያሌው (አዲስ አበባ)

10. የእምነታችሁ መሰረት "ጥረህ ግረህ በግንባርህ ወዝ ብላ" ከሚለው አምላካዊ ቃል ልዩነት የለውም፡፡ ማህበረሰቡ የነገይቱ ኢትዮጵያ እርሾ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ተብትቦና ቀይዶ የያዘንን ድህነት እናንተ ገጥማችሁታልና፡፡ አውራ አምባ ከእንግዲህ በኋላ ብቻውን አይደለም፡፡ የእልፍ አዕላፍ ስራ ወዳዶች ድጋፍ ከጎኑ ነውና፡፡

ሺህ የልማት ጀግና ሺህ በሺህ ተባዝቶ፣
እልፍ አዕላፍ ጥረት እልፍ ልማት ገዝቶ፡፡
ተጠምደው በስራ ተባባሪ እጆች፣
ይጽደቁ የፈሉት ሚሊዮን ችግኞች፡፡

በማለት ወደፊት አቅሜ በፈቀደው ሁሉ ከጎናችሁ ለመቆም የተሰናዳሁ!

ላዕከማሪያም ተሾመ (እንስሳት ጤና ጥበቃ፣ ባህር ዳር)

11. እጅግ ደስ ትላላችሁ! ኑሩልን! እደጉ! ተመንደጉ! ብዙ ተባዙ! ሁሉንም ውረሱት! ወደናንተ ይጠቃለል! እባካችሁ ግን ቀጥሉበት!! እንዳትሸነፉ! እንዳትዋጡ!

ተስፋዬ ኃ/ኪሮስ ወለላ

12. አውራ አምባ ማህበረሰብ እጅግ አስደናቂ ባህልና መመሪያ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ነው፡፡ ከባህልም ጠቃሚንና ጎጂን ለይቶ እየሰራ ነው፡፡ ይህን የፈጠሩት መስራቹ አባታቸውም ተሰሚ በመሆናቸው ውጤታማ ሆነዋል፡፡ ለወደፊቱም እንደሚሰሩ እናምናለን፡፡ የማህበረሰቡና የአባታቸው ዕድሜ እንዲኖራቸው እንመኛለን፡፡

አስማማው ታየና ጋሻው ሞገስ (1994)

13. ምንጊዜም በህሌናዬ አይጠፉም፡፡ ዘወትር ያቺ መንደር የት ደረሰች? እንዴት ነች? ብዬ አስባታለሁ፡፡

ሰለሞን ባዘዘው (ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን)

14. በዛሬው እለት የአውራ አምባን ማህበረሰብ አኗኗር፣ የሰው ክቡርነት፣ የስራ ፍቅር፣ ጥልቀት ያላቸው ጥሩ አስተሳሰቦች፣ በቦታው ተገኝተን በማየታችን ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶናል፡፡ ስለዚህ ለወደፊት የዚህን ማህበረሰብ ችግር ለመፍታት የአቅማችንን ለማድረግ ከጎናችሁ መሆናችንን እናረጋግጥላችኋለን፡፡ የናንተንም ጥሩ ፍልስፍና በማስተማር የበኩላችንን እንወጣለን፡፡

ሻምበል ኃይሌ (ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ 1995)

15.የማህበረሰቡ አኗኗር በጠቅላላው፣ ግጭት እንዳይነሳ የሚያደርጉት ጥረትና ወንጀልን ለመከላከል የሚከተሉት ስልት ለሌላው ህብረተሰብ ትምህርት ሊሆን የሚችልና በመንግስት በኩል ሊደገፍና ሊበረታታ የሚገባው ነው፡፡

አሊ መሐመድ አሊ

16. መንደሯን ለማየት በጣም ጉጉት ነበረኝ፡፡ በማየቴም ደስተኛ ነኝ፡፡ ህይወትን ለማሸነፍ የምታደርጉት ጥረት አርኪና የሚያስደንቅ ነው፡፡ ከራሳችሁ ባለፈ ለሌላው ህብረተሰብ አርአያነታችሁ ይታየኛል፡፡

ሀሰን ጅብሪል (ደሴ)

17. አገራችን ኢትዮጵያ ባልሰለጠነችበት በአሁኑ ጊዜ በአውራ አምባ የሚካሄደው አሰራር ለኢትዮጵያ ሞዴል ሊሆን እንደሚችል እረግጠኛ ነኝ፡፡

በጋሻው ደስታ (ከመተማ)

18. በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሰማሁትንና ያየሁትን በአካል መጥቼ ስመለከተው በጣም አስደንቆኛል፡፡ ከሰማሁት በላይ ግሩም ድንቅ ነው፡፡ በወንዱም በሴቱም የሚካሄደው ማህበራዊ ስራ ለቀሪው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ትምህርት ሰጭ ነው፡፡ በርቱ ተበራቱ!!

አክሎግ ደስታ

19. በአውራ አምባ ማህበረሰብ በጉብኝቴ ወቅት ትልቅ ትምህርት አግኝቸበታለሁ፡፡ ይህ ማህበረሰብ በልማት፣ በመተጋገዝ፣ በእኩልነት ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ስለሆነ ለአገሪቱ ትልቅ ሞዴል ነው፡፡

አበበ ተስፋይ (ማህበራዊ ረድኤት ትግራይ፣ መቀሌ)

20. አንድነታችሁ፣ መተሳሰቡ፣ ለስራ ያላችሁ ፍቅርና መነሳሳት፣ እንዲሁም ማህበራዊ አኗኗራችሁ እጅግ በጣም የሚያስደስትና ለሌሎቻችንም አርአያ በመሆኑ አሁን ያለውን ሁኔታ ለወደፊት እንድታቆዩት!!

ሻምበል ገመቹ (ስምጥ ሸለቆ የህፃናትና ሴቶች ልማት፣ አዲስ አበ)

21. ስራ የማንነት መለኪያ ነው፡፡ የስራ ባህል ደግሞ የእድገት ቁልፍ ነው፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ ደግሞ ዛሬ ፈር ቀዳጅ የሆነ ስራ እየፈፀማችሁ ነው፡፡ ያታዊ የስራ ክፍፍልን መደምሰሳችሁ ለብዙዎቻችን በአርአያነት የሚያስጠቅሳችሁ ነው፡፡ ሁላችንም እንደናንተ ጠንካራ የስራ ባህል ካሳደርን ኢትዮጵያን በአጭር ጊዜ መለወጥ ከባድ አይሆንም፡፡ በርቱ!!

አስቻለው ጌታቸው (ኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ 1995)

22. የአውራ አምባ ማህበረሰብን ልምድ በማየቴ እኔም በስራ ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደምችል አምኜ እንድቀበል ረድቶኛል፡፡ መልካም እድገት እመኝላኋለሁ፡፡

ወርቅነሽ መምአ (ደቡብ ኢትዮጵያ)

23. የአውራ አምባን ማህበረሰብ በመገናኛ ብዙሃን ብቻ ሳይሆን በአካል ለመመልከት በመቻሌ ከፍተኛ እድል አግንቻለሁ፡፡ ማህበረሰቡ በራዕይና በጠንካራ እሴቶች የሚመራና በትንሽ ዕቅድ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በትግልና በጥረት የማይለወጥ ዓላማ እንደሌለም በግልፅ አሳይተዋል፡፡ ለሁላችን መምህሮች ናቸው፡፡

በረከት ስምኦን (የማስታወቂያ ሚኒስትር፣ 1996)

24.በክልላችን አንድ ትንሽ ሻማ ተለኮሰች፡፡ ትንሽ ብርሃን ፈነጠቀች፡፡

ወንዴ እንግዳ (ከአመልድ ህዝብ ግንኙነት፣ 1994)

25. በዛሬው ቀን የአውራ አምባ መንደርን በመጎብኘቴ በህይወቴ በኢትዮጵያ እንደዚህ ዓይነት ኮሌጅ ይኖራል ብዬ አልገመትኩም፡፡ የተቀናጀ የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ማስተማሪያ ተቋም መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡

ይታየው አበበ (ባህር ዳር)

26. ህይወቴን ዛሬ አስተዋልኳት፡፡ በመሬት ላይ ገነት ገባሁ፡፡ ምክንቱም የጌታችን መድሃኒታችን ቃል ካለበት በየአውራ አምባ ማህበረሰብ መንደር ስለገባሁ፣ እዚህ ቦታ የእግዚያብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ ስለተፈፀመና የሰው ልጅ ክብር የተሰጠበት መንደር በመሆኑ፡፡ ሁልጊዜም ሰላም ለእናንተ ይሁን!!

ብርሃን ገላው

27. የአውራ አምባ ማህበረሰብን ባህልና አሰራር ለሁሉም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ እንዲያውቁትና ተግባራዊ የሚያደርጉበት ምቹ ሁኔታ ቢፈጠር ጠቀሜታው የጎላ ነው ብየ አምናለሁ፡፡

ሙላቱ አበበ

28. የአውራ አምባ ማህበረሰብ የዓለም ሰላም ጠባቂዎች ናችሁ፡፡ ዓለም እኔ ልብላ እናንተ ጦም እደሩ እያለ ሲተራመስበትና ሲመሰቃቀልበት የሰው ልጆች ችግር ዋነኛ ጥያቄ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ስለዚህ ለኢትዮጵያ መርህ የምትሆኑ ጀግኖች ስለሆናችሁ በጣም የምወዳችሁና የማመሰግናችሁ ዓለምን መቀየር የሚያስችል ርዮተ ዓለም ስላላችሁ በርቱ! ከጎናችሁ ሚሊዮኖች ይሰለፋሉ፡፡

ከበደ ተስፉ (ባህር ዳር፣ 1997)

29. የሰውን ጭንቅላት መቀየር ከባድ ቢሆንም ዙምራ ግን እንደሚቻል አሳይቶናል፡፡ ወደፊትም ኢትዮጵያ ሊገጥሟት ከሚችሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ ሀሳቦች የአውራ አምባ ማህበረሰብ መልስ ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ የአገር ቅርስ ናቸውና ሁላችንም ብንሰማቸው፣ ብናከብራቸው፣ ብናደምጣቸው...

አክሊሊ ጣቂ (አግሪ ሰረቪስ ኢትዮጵያ)

30. ስለአውራ አምባ ማህበረሰብ የአኗኗር ባህልና የወደፊት ራዕይ በተደረገልኝ ገለፃና በአካል ያየሁት ሁሉ በጣም የሚያስደንቅና ለወደፊት የአገራችን ትልቁ ት/ቤት ነው ብል ይቀለኛል፡፡ ይህን ት/ቤት አጠናክራችሁ በማስተማር ግፉበት፡፡ በጣም እድለኞች ናችሁ፡፡

ይኩኖአምላክ አምባዬ (ከተክለ ብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን)

31. ሁለንተናዊ እንቅስቃሴያቸውንና የማህበረሰቡን ማንነት በመረዳቴ በህይወቴ ውስጥ ካሳለፍኩት ጊዜ ሁሉ ደስታን ያገኘሁበት ዕለትና ትልቅ ትምህርት የቀሰምኩበት ዕለት በመሆኑ በህይወት ታሪኬ ትልቅ ቦታ ይኖረዋል፡፡ የማህበረሰቡ ባህልና ሰላም ይበልጥ ጎልብቶ የአገራችን አርአያ ሆኖ እንዲቀጥል በግሌም ሆነ በድርጅቴ አማካይነት የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግና ለማያውቁትም ለማስተዋወቅ ቃል እገባለሁ፡፡

ሻምበል ዋለ (ከደ/ጎንደር ቀይ መስቀል ቅ/ጽ/ ቤት)

32. አውራ አምባዎች በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ ብዙ መፃህፍት ከማንበብ የበለጠ የእናንተን ህይወት ማየት ያስተምራል፡፡ ከዚህ በበለጠ አድጋችሁ በመተዛዘንና በመዋደድ እየሰራችሁ የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ህዝብ የሚያውቃችሁ እንድትሆኑ ምኞቴና ፀሎቴ ነው፡፡ ዳግም ስመጣ አድጋችሁ እንደማገኛችሁ ተስፋ አለኝ፡፡

እታገኝ ደሳለኝ (ኢልማናዴንሳ ሴቶች ጉዳይ)

33. በሀገሬ ልጆች ኮርቻለሁ፡፡ ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያዊያን የሚያስተባብረን ካገኘን ብዙ መስራትና ማምረት እንደምንችል በዚች አነስተኛ የገጠር መንደር በጣም በርካታ

በአርአያነታቸው ሊጠቀሱ የሚችሉ ተግባራትን ተመልክቻለሁ፡፡ በርቱ! ጠንክሩ!! አርአያነታችሁ በመላ አገሪቱ ይስረፅ፡፡

ሚሊዮንና ጓደኞቹ (ኢ..መ.ባ ጎንደር ዲስተሪክት)

34. ባየሁት ነገር ሁሉ ተገርሜአለሁ፡፡ የጀመራችሁት መተሳሰብ፣ ፍቅር ወንድማማችነት፣ የሚያነግስ መንገድ ለሌሎች አርአያ የሚሆን ነው፡፡ በእኔ እምነት ድህነትን ለማሸነፍ የጀመራችሁት በራስ የመተማመንና ተደጋግፎ መሄድ ያዋጣል እላለሁ፡፡ የፈለጋችሁትን የምታሳኩበት እንዲሆንላችሁ ምኞቴ ነው፡፡

ፀጋዬ ወ/ማሪያም (ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን)

35. ዙምራ ኑሩ ለሰው ልጆች ደህንነት ሲል እራሱን ፈትኖ የወጣ የሰው ልጆች ስጦታ ነው፡፡ በኔ በኩል የሱን ሀሳብ ለመተግበር ከቤተሰቦቼ በመጀመር ጥረት አደርጋለሁ፡፡

ተሾመ ሲሳይ መኮነን

36. በእውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት አርአያነት ያለው ተግባር የሚያከናውን ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር ብሎ ለመቀበል ያዳግታል፡፡ ይሁን እንጅ አይን አይቶ ይፈርዳል እንዲሉ በቦታው ተገኝቼ በተረዳሁት መሰረት ሀገራችን ከድህነት አረንቋ አውጥቶ ካደጉት አገሮች ጋር ሊያስተካክላት የሚችል አካሄድ ማለትም በመደጋገፍ፣ በመፈቃቀር፣ በመተሳሰብ በጋራ መስራት፣ አረጋዊያንንና ህፃናትን በመደገፍ፣ ያለፋታ በመስራት፣ ጎጂ ባህሎችን ወደጎን በመተው ለተሻለ ኑሮ መጣር የመሳሰሉ አካሄዶችን ተገንዝቢያለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ አርአያነት ያለው አካሄድ ለሌሎች የአገራችን አካባቢዎች መልካም ተምሳሌት ሆኖ በጥቅሉ ሀገራችን ስታድግ ማየትን ከልቤ እመኛለሁ፡፡

ተስፋዬ ይሁኔ (ኢ/ሀ/ማ/ል/ድ፣ አዲስ አበባ)

37. በእውነት ከድህነት መውጣት የሚያስችል የስራ ባህል የአውራ አምባ ማህበረሰብ ላይ ተመልክቻለሁ፡፡ በእውነት ኢትዮጵያን ሁላችንም እንዲህ መስለን ሳይሆን ሆነን ብንገኝ እንዴት ደስ ይል ነበር? ይቻላልም፡፡

ሙሉጌታ አዳነ (የደ/ታቦር ገ//አ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ኃላፊ፣ 1997)

38. የአውራ አምባ ማህበረሰብ ያለው አስተዳደርና አኗኗር ለሁሉም ጠቃሚና አርአያ ሆኖ አይቸዋለሁ፡፡ በኔ በኩል እንደህልም የሚታሰብና የሚደረስበት አይመስለኝም ነበር፡፡ በተግባራቸው በዓኖቼ አይቻለሁ፡፡

ሙሉእመቤት ፈለቀ (አዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት)

39. ይህ መልካም አርአያነት ያለው ማህበረሰብ ለሰው ልጆች መልካም ምኞትና ለህዝቦች በአንድነት፣ በመተባበር፣ በጋራ በመስራትና በመኖር የሚያደርጉት ተግባር ለሀገሪቱ አልፎም ለዓለም ሞዴል ሆኖ ሊታይ የሚገባ የሀገር ሀብት ነውና መንግስት ሊደግፈውና ሊያበረታታው ይገባል፡፡

ቢራራ አራጌ

40.ለመጀመሪያ ጊዜ መማር በሰው ልጅ ላይ ከሚያመጣው ለውጥ የበለጠ ማስተዋልና ችግር እንደሚያስተምር በግልፅ መመልከት ችያለሁ፡፡ በመሆኑም ለአውራ አምባ ማህበረሰብ ብልፅግናን መመኘት ሳይሆን እራሱ እንደሚመጣ ግልፅ ነው፡፡ ዙምራ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ የሚበቃ የፍልስፍና ሰው ስለመሆኑ ልመሰክር እወዳለሁ፡፡ እኔ ዛሬ የተማርኩትን ለማውቀው ግለሰብ ሁሉ እንደማስተምር እገልጻለሁኝ፡፡

ሰለሞን ደምሴ

41. በህይወቴ ውስጥ ካደረግኳቸው ጉብኝቶች የአውራ አምባ ማህበረሰብን መጎብኘቴ ከፍተኛ ቦታ ይይዛል፡፡ በዚህ ጊዜ ሌላውን ወንድሜንና እህቴን እንድወድ፣ ጥላቻንና ምቀኝነትን እንድጠላ አድርጎኛል፡፡ ለወደፊት መጥቼ እንደማያችሁ ተስፋ አለኝ፡፡

ንጋቱ በዳዳ (ዋሽንግተን ዲሲ)

42. በሄድኩበት ሁሉ ሌላ ማውራት የምችል አይመስለኝም፡፡ የሰማሁትን ባይኔ ማየቴ የበለጠ ሰውን ለማሳመን ይረዳኛል፡፡ አብረውኝ ከመጡት 8 ጋደኞቼ ጋር የናንተን ቀናነት፣ የአኗኗር፣ የመተጋገዝ፣ የመፈቃቀር፣ ዘይቤያችሁን ለምናገኘው ሁሉ እንነግራለን፡፡ የተቻለንን ሁሉ ለማድረግ በልባችን ቃል ገብተናል፡፡

ፈንዲሻ ፍስሃ ከነጓደኞቼ

43. በአውራ አምባ ማህበረሰብ በጣም በሚገርም ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን ለመተግበር ለማሰብ የሚያስቸግሩ ነገሮችን እየተገበሩ ያሉ በጣም ሊበረታቱ የሚገባቸውና አጋዥ የሚያስፈልጋቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ እንዴት የሚያኮራ ማህበረሰብ ነው? በጣም ያስደስታል፡፡ የሚያኮሩ ኢትዮጵያዊያን፡፡

አህመድ ሰይድ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

44.ከማዕከል የሚዲያ ተቋማት የተውጣጣ ቡድን የማህበረሰቡን እንቅስቃሴ ለመዘገብ በመጣበት ወቅት ያገኘነው መስተንግዶ በጣም አስደንቆናል፡፡ እንደጋዜጠኝነታችን ህዝብን ለማስተማር የሚያስችል ስራ ለመስራት መጥተን ከፍተኛ ትምህርት ቀስመን ተመልሰናል፡፡ የማህበረሰቡ የስራ ባህል፣ መተሳሰብና ጥቅል ወገናዊነት ሊጠናከር እንዲችል መንግስት፣ ህዝቡና ይመለከተኛል የሚል ማንኛውም ወገን አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት እናምናለን፡፡ ይህ አርአያነት ያለው የኑሮ ዘይቤ በሌላው ዜጋ ሁሉ ቢለመድና ቢስፋፋ ሁለንተናዊ እድገትና ለውጥ ለማምጣት ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት አለን፡፡

ጌታቸው ተስፋ (አዲስ ዘመን)
ሙላት ዓለማየሁ (ኢቴቪ) እና
ኃ/አምላክ ካሳዬ ኢ.ት.ሬዲዮ)

45. በአውራ አምባ ማህበረሰብ በዚች ትንሽ መንደር ሁሉም ቁልፍ አለ፡፡ የኛ የሚስጥሩ ቁልፍ እዚህ ይገኛል፡፡ እጅግ በጣም እረክቻለሁ፣ ኮርቻለሁም፡፡ በዚያው መጠንም ትልቅ ሽክም እንዳለብኝ ዓይኔን የከፈተልኝ ቦታ ነው፡፡ ይበቃኛል፡፡ በርቱ!!

ኤሊያስ ጌታቸው

46. ግሩም፣ ድንቅ ነው፡፡ የመንግስተ ሰማይ በር ይህች ትሆን ይሆን? እኔ እንጃ እኔ ምን አውቃለሁ፡፡ እኔ፣ እኔ ስል ዘመኔን ጨረስኩ፡፡ ከልቤ አስቀንታችሁኛል፡፡ ፈጣሪ ምድራችሁንና አእምሯችሁን ይባርክላችሁ፡፡ በኢትዮጵያነቴ አኮራችሁኝ፡፡

ጀማል መሀመድ

47. ያየሁት ከምጠብቀው በላይ እውነትም አውራ አምባ የኢትዮጵያ አውራ መሆናቸውን ተዘዋውሬ በማየት ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡ መስራች የሆነውን ዙምራንና ሌሎች የሰጡኝን ማብራሪያ በፊሎሶፊ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ በነሱ የተያዘ ሳይማሩ የተማሩ ማህበረሰቦች መሆናቸውን አረጋግጫለሁ፡፡

አለምሰገድ ወ/ገሪማ (ከትራንስፖርት ቢሮ)

48. በአውራ አምባ ስፍራ በዙምራ መንደር ተገኝቼ ይህን ጠንካራና መንፈሰ ጀግና ማህበረሰብ በማየቴ እጅግ በጣም ተደስቻለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ? ብዬ እራሴን እንድደፈትሽና በጣም ብዙ ነገሮችን በትንሽ ደቂቃ በመማሬ አደንቃችኋለሁ፡፡ በዚህ ጥንካሬያችሁ ወደፊት ሌላ ደረጃ እንደምትደርሱ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ከድር ይማም

49. አውራ አምባ የስራ ማዕከል፣ የባህል፣ የፆታ እኩልነትን የሚያሳይ መስታውት ነው፡፡ ለሌላው የአገራችን ህዝብ ተምሳሌት ነውና ማንም ኢትዮጵያዊ ከጎኑ የሚቆምለት ስለሆነ ወደፊት መጠንከር ብቻ አለበት፡፡ እኔም ሆንኩ መስሪያ ቤቴ ከጎኑ የቆምን ነን፡፡ አንድ ቀን ብርሃን ስለሚወጣለት ዛሬን በፅናት ማለፍን ያስተምረናል፡፡ እያስተማረም ይገኛል፡፡ በርቱ! ጠንክሩ! እላለሁ፡፡

መሰረት ቀለመወርቅ

50. ትልቅ ትምህርት ተፈጥሮ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ እንደኔ ሁሉም ዓለም ይህችን እንደሚከተል እርግጠኛ ነኝ፡፡ የሚገርመኝ ግን ይህ ትልቅ መንገድ ከዚች ትንሽዬ ምንም ኢንፎርሜሽን ከማይገኝባት ቦታ መሆኑ ነው፡፡

አሳዬ አየለ

51. ይህች መንደር ትልቅ አገር ሆና እንዳያት እግዚያብሄርን እድሜ እለምናለሁ፡፡

የለማሁ ሞላ ከአማራ ቴሌቪዥን

52. ሌብነት፣ ቅጥፈት፣ ውሸት የሌለበትና ስራ የሚወደድበት ባህል በመሆኑ ተደንቄያለሁ፡፡ ዓላማቸው መተባበር፣ መደጋገፍ፣ ፍቅርና፣ አንድነት ያለበት በመሆኑ ሁሉም ሰው ይህን ዓላማ እንዲከተል ምኞቴ ነው፡፡

ፍስሃ ጌታነህ (አዲስ አበባ)

53. ለዓለም ህበረተሰብ ፍቅርና ሰላምን የሚያስተምር ማህበረሰብ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በተለይ ስለ አረጋዊያን አያያዝ እኔ ካለኝ አመለካከት ጋር ሲዳመር ለቤተሰቤ ጥሩ አመለካከት እንዲኖረኝ እጅጉን ይረዳኛል፡፡ ይህ ባህል በፍጥነት ቢሰራጭ አገራችን ካለችበት ተነስታ ከማንም አገር በላይ እንደምትሆን እረግጠኛ ነኝ፡፡ በርቱ! አይዟችሁ በጣም ጥሩ ሞዴልነት ነው፡፡

ቢያድጌ ውቤ (አለማያ ዩኒቨርሲቲ)

54. በአውራ አምባ ተገኝቼ የሰማሁትና ያየሁት ነገር ለቀሪው ዘመኔ ሁሉ አስተማሪዬ ይሆናል፡፡ ምናልባትም የዘመናችን ሰው መሰረታዊ ችግር በአግባቡ ፈትቶ በወንድማማችነት እየኖረ ያለ ብቸኛ የአገራችን ቦታ ነው ብል ማጋነን አይሆንም፡፡ በመምህርነቴ ለማስተምራቸው ልጆች፣ ለቤተሰቦቼና ለጓደኞቼ የምሰብከውን ታሪክ ይዤለሁ፡፡

በላቸው መኩሪያ

55. ብዙ ጥሩ ታምራዊ ሁነቶችን ያየሁ ቢሆንም የአውራ አምባ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ እራሴን በውል እንድፈትሽ መነሻ ይሆነኛል የሚል ሙሉ ግንዛቤ ፈጥሮልኛል፡፡ እናም ከዛሬ ቀን ጀምሮ ማንነቴንና የወደፊት የህይወት ፍስፍናዬን ቅጥ ላበጅለት ወሰንኩ፡፡

ማሩ ቸኮለ (1998)

56. የዙምራ ራዕይ በጣም ትልቅና ለረጅም ጊዜ የሚወስድ በጣም ለአገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ኋላቀር የሆኑ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚዋጋ በአጠቃላይ እውን እየሆነ ያለ በመሆኑ በኔ በኩል ትምህር ያገኘሁበት ማህበረሰብ በመሆኑ እኔም የማህበረሰቡ አባል ለመሆን ወስኛለሁ፡፡

ፈንታው ከፍያለው (የወልዲያ ከተማ ከንቲባ)

57. የአውራ አምባ ማህበረሰብ እጅግ ታላቅ ከዘመናችን ኢትዮጵያዊያን አስተሳሰብ እጅግ አለፍ ያለና የላቀ፣ ዛሬ ያለንበት አስተሳሰብ ሳይሆን ከዚህ ያለፈ ዘመናዊ አስተሳሰብ ያለውና ለሀገራችንም ትልቅ ትምህርት መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ማህበረሰቡ ዛሬ ብቻ የሚኖር ሳይሆን ለነገ ራዕይ ያለው መሆኑንም ተገንዝቢያለሁ፡፡

መሰለ ካሳ (ከአዋሳ)

58. በአውራ አምባ ማህበረሰብ መኖሪያ ተገኝቸ እጅግ የላቀ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡ ደካማ ወገንን መርዳት የሚለው መሪ ቃል "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" ከሚለው የጌታ ትምህርት ጋር የተገናኘና የስብከተ-ወንጌል ተልእኮ ፍፁም ሆኖ በማግኘቴ እጅግ ደስ ብሎኛል፡፡ እርካታንም አግኝቻለሁ፡፡ መስራቹ ዙምራ ኑሩ ቀደም ሲል ስመጥር ከሆኑ ፈላስፎች የበለጠ እንጅ ያነሰ ባለመሆኑ የሚደነቅ ታላቅ ሰው ነው፡፡ ይበልጥም ሊረዱ የሚገባቸው መምህርና መሪ በመሆናቸው ሀሳባቸው ሁሉ በመጽሐፍ ቢሰፍር መልካም ይመስለኛል፡፡ እግዚያብሔር በዚህ መልካም ተግባር የተመሰገነ ይሁን፡፡

አባ ግርማ ፋሪስ (ከኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን)

59. በዚች ቀን ያየሁት ነገር ለህይወቴ የ10 ዓመት ትምህርት ያክል ጠቅሞኛል፡፡ የዙምራ ፍልስፍና ለማንኛውም የሰው ዘር በሙሉ ጠቃሚ ነውና ቀሪውን ህይወታቸውን የተመኙትን የሚያገኙበትና የጤና እንዲሆንላቸው እመኛለሁ፡፡

(በላይነህ ሽታዬ (ከአልማ))

60. የአውራ አምባ ማህበረሰብ የፍቅር፣ የስራና የጥበብ መሰረት የሚሆን ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም ህዝቦች በሙሉ አንድ አዳምና የሄዋን ዘር በመሆኑ በዓለማችን ላይ እስካሁን ተከስተው ከነበሩት ፈላስፎችና የአንዳንድ ሃይማኖት መስራቾች የበለጡ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ምናልባት የሰው ልጅ እንደነሱ ፍቅርን መሰረት ቢያደርግ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ፍቅር እራሱን አሳልፎ ሲሰጥ ጨክነው የገደሉት፡፡ የሰው ልጆች ጭካኔን በሰው ልጆች ላይ ማድረስ ከሰውነት ባህርይ ውጭ መሆኑን ምናለ ከዙምራ ተምረው ቢሆን ኖሮ!! እግዚያብሄር ሰውን ሲፈጥር እንደዙምራና እንደማህበረሰቡ እንዲሆን ነበር፡፡ ታዲያ ሌሎቻችንስ ምን እናስባለን?

መለሰ ልይህ

61. ህልም ሁጊዜም ህልም ሆኖ እንደይማቀር እዚህ ተምሬያለሁ፡፡ ነገ በጣም የተሻለ ነገር፣ የተሻለ ዓለም ተገንብቶ ለማየት አልማለሁ፡፡ ህልሜንም እውን ሆኖ አየዋለሁ፡፡

ሰለሞን ከበደ

62. ስለአውራ አምባ ማህበረሰብ ዝምብየ የተደላደሉትን ሀገራት የኑሮ ዘይቤ ከማሰብ ውጭ መናገር እጅግ ከብዶኛል፡፡ ፍፁም የሆነ የመፈቃቀር፣ የመተሳሰብና ለስራ ትልቅ አክብሮት ያላቸው ህዝቦች በመሆናቸው ለኖርኩባት ኢትዮጵያ ትልቅ ምሳሌና የመንግስቱም የስራ መዋቅር ማሻሻያ አድርጎ ሊቆጥራቸው የሚችላቸው ህዝቦች በመሆናቸው ያየሁትን ማመን እስኪያቅተኝ ድረስ ተገርሜያለሁ፡፡ በመሆኑም ያየሁትን ለሌላውም ህብረተሰብ ለማሳወቅና እኔም የሚጠበቅብኝን ለማድረግ የራሴን ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ከሁሉም እግዚያብሄር ይርዳችሁ፡፡

ዶ/ር ዘውዱ ሁሪሳ

63. እጅግ በጣም የሚገርም ነገር በማየቴ ደስተኛ ነኝ ይሆን? እኔ እንጃ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ አስተማሪዎች ሆነው ታይተውኛል፡፡ እኔም ትልቅ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡ እንደቻይናም ኢትዮጵያን ራሷን እንደሚያስችሉ ይታየኛል፡፡

ወንድሙ

64. አሸነፋችሁኝ፣ እራሴን ወቀስኩ፣ ባህላችሁ ባህሌ ሆኖ እንደሚቀጥል ለራሴ ቃል ሰጠሁ፡፡

ምስጋናው ታምራት (ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ)

65. ይህ ማህበረሰብ ለስራ ተነሳሽነቱና ለሰው ልጅ ክብር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ ስለሆነ የአገራችን ህዝቦች መማሪያ ማዕከል መሆኑ እጅግ አኩሪ ያደርገዋል፡፡

ፋንታዬ አበባው (ከሊቦ ከምከም ወረዳ ግ/ገ/ል/ጽ/ቤት)

66. የአውራ አምባ ማህበረሰብ በጣም ደጎች ጌታ የራሱን ጥበብ ያስተማራችሁ የታደላችሁ የጌታ አምሳል ናችሁ፡፡ እናመሰግናለን፡፡

ተናኘ እጅጉ (አዊ ዞን)

67. ወጣት መምህር ነኝና በማስተምረው እድሜዬ ምሳሌዎቼ ናችሁ፡፡

ሃፍቱ ህንዲያ (ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ)

68.የአውራ አምባ ማህበረሰብ ይዞት የተነሳው ላቅ ያለ አስተሳሰብ በሀገራችን በተለይም በክልላችን ውስጥ መገኘቱና የሰው ልጆች እኩልነትና የልማት ተሳታፊነት መታገሉ፣ ዓለም ላልደረሰበትን እድገት መብቃቱ፣ እኔም ይህን ማየቴ በእውነት እጅግ ላቅ ያለ ኩራት ተሰምቶኛል፡፡

የኔንድ እስቲበል (ከባህር ዳር)

69. የሰው ልጅን መልካም አስተሳሰብ ማስፈን የፈለገና ፍቅርና ሰላም የሞላበትን ዓለም የፈለገ- እንዲሁም በእውን ለማየት ጥሮ የተሳካለት ዙምራና እሱ የመሰረተው ማህበረሰብ ነው፡፡ ይህን ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሁም በአማራ ባህል በታጠረ ስፍራ መገኘቱ ደንቆኛል፡፡

ብስራት ዓለሙ የአክሽንኤድ ሰሜን ሪጅን አስተባባሪ

70. ሰዎች መምጫቸው፣ መፈጠሪያቸው፣ ሃይማኖታቸው አንድ መሆኑን የእምነትም ህንፃ ሰዎች እንጅ በየቦታው የሚሰሯቸው ጎጆዎች አለመሆናቸውን የተረዳሁበት፡፡ ሰው ሀብቱ አእምሮው፣ እምነቱ፣ ጥሩ ምግባሩ መሆኑን የተረዳሁበት በህይወቴ ትልቅ መሰረት ያገኘሁበት ቦታ ነው፡፡ ይህን የአመለካከት ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ማህበረሰብ መጎብኘት በሀገር ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ እኔም የነሱን ፈለግ በመከተል በምችለው ሁሉ ቃል የገባሁበትና የምለማመድበት ዕለት ነው፡፡

ተስፋየ የሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቴሌኮሚኒኬሽን ስራ አስኪያጅ

71. በኢትዮጵያዊነቴ ኮራሁ፡፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ ኩሩ፡፡ ያብዛችሁ፡፡ ኢትዮጵያንም አጥለቅልቋትና እኛንም ለውጡን፡፡ ፈጣሪ ይርዳችሁ፡፡ ፍቅራችሁን፣ መተባበራችሁን፣ መዋደዳችሁን ጌታ ያግዛችሁ፡፡ በጎንደሬነቴ ኮራሁ፡፡

ተስፋዬ ተሻገር

72. የአውራ አምባ ማህበረሰብ ማለት እንደኔ አገላለጽ በኢትዮጵያ የስራ መፈጠሪያና ትክክለኛ ኢትዮጵያን ለማሳደግ የሚታገል ታታሪ ማህበረሰብ ማለት ነው፡፡

ገ/መስቀል ሙሉ

73. በእውነት ዙምራ መፈጠር ባለበት በትክክለኛው ጊዜ የተፈጠረ ሰው እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ይህ የስራ ባህል በሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም ቢለመድ ኢትዮጵያችን ከተረጅነቷም በተላቀቀች ነበር፡፡

ስሙን ያልፃፈ አስያየት ሰጭ

74. በእድሜዬ እምመኘው አገሬ ኢትዮጵያ ራሷን ችላ ማየት ነው፡፡ ይህንን ህልም በአውራ አምባ መንደር አይቻለሁ፡፡ ይህንን ጅምር ራዕይ ከግብ የማድረስ የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ነው፡፡

ተስፋዬ ባንቲርጋ (1999)

75.ዙምራና መላው የአውራ አምባ ማህበረሰብ አኗኗር፣ እምነትና የስራ ፍቅር በኢትዮጵያችን አዲስ ተስፋን ፈጥሯል፡፡ ነገ የአውራ አምባ ማህበረሰብ እምነቶችና እሴቶች በሀገራችን በሙሉ ተሰራጭተውና ተተግብረው እንደምናይ አምናለሁ፡፡ በእውነት ዙምራ ታላቅ መምህር ነው፡፡

አብነት ሰለሞን ከኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ (ሰንዳፋ)

76. በእኔ እምነት የአውራ አምባ ማህበረሰብ የዓለም ማህበረሰብ ቁንጮ /አርአያ/ ናቸው፡፡ ስለዚህ የመኖሪያ ቦታቸው አውራ አምባ ቢባልም ተግባራቸው ደግሞ "የአለም አምባ" "የኢትዮጵያ ፋና" ብያቸዋለሁ፡፡

ስዩም በላይ (ላይ ጋይንት)

77. ሰው በተፈጥሮው ስግብግብ ነው ያልከው ፈላስፋ አውራ አምባን ሳታይ ስላልከው አበቃልህ፡፡

በጋይሉ ተ/ኃማኖት 4ኛ ዓመት የህግ ተማሪ

78. መቸም ዓለማችን በብዙ ድንቅ ነገር የተሞላች ናት፡፡ ነገር ግን ከእያንዳንዱ ድንቅ ስራ በስተጀርባ ገንዘብ፣ የተማረ ሰው ወይም ጉልበት አለበት፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ ድንቅ ስራ ግን ከበስተጀርባው ያለው ፍቅር ብቻ ነው፡፡ ዛሬ የውጬ ዓለም በስልጣኔና በሀብቱ ሊያገኝ ያልቻለው ፍቅር እዚህ በገፍ አለ፡፡ የስራ ፍቅር፣ የህፃናት ፍቅር፣ ያዛውንቶች ፍቅር እንዲሁም የእግዚያብሄር ፍቅር አለ፡፡ የእግዚያብሄር ፍቅር ባለበት ደግሞ ሁሉም ነገር አለ፡፡ እሰከዘላለሙ እግዚያብሄር ይርዳችሁ፡፡ እኛም ይህን ዓለም ያላዩ ሰዎችን ነግረን ዳግመኛ ለመምጣት ቃል እንገባለን፡፡

ዶ/ር እሸቱ ሙላትና ባልደረቦቹ

79. አውራ አምባ ልዩና ድንቅ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን የስራ ክቡርነትን ለማያውቁ ሁሉ ሞዴል ናት፡፡ የባህል ኋላቀርነት ለጎዳት ኢትዮጵያ አውራ አምባዎችን ስናይ ምን ያህል እንዳንቀላፋን የምታስረዳን ሞዴላችን ናት፡፡ ቃላቶች ያንሱኛል፡፡

ያሬድ ካሳ

80. አውራ አምባዎች በእውነቱ ለምወዳት ለሀገሬ ኢትዮጵያ የመፍትሄ ቁልፎች ናችሁ፡፡ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ሀሳባችሁን ለመቀበል በጣም ፈቃደኛ ነኝ፡፡ በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ በርቱልኝ!!

አሞኘ ድረስ

81. የአውራ አምባ ማህበረሰብ ለስራ ያለው አስተሳሰብና በእምነት ላይ ያለው አስተሳሰብ ወቅቱን የጠበቀና ለዓለማችን ወሳኝ አስተሳሰብ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ አስተሳሰባችሁ ለሌሎች አርአያ በመሆኑ በኢትዮጵ ተደርሶ የሚታይበትን ጊዜ እመኛለሁ፡፡ በጣም አክብራችኋለሁ፡፡

ናትናኤል አበጋዝ

82. ባለ አራት ነጥብ ይዞ የተነሳው ዙምራ ከህፃንነቱ ጀምሮ በመጣሩ ችግርና መከራ ሳይገታው ለዚህ ዓለም ለውጥ የሰውን ልጅ እኩልነትና መብት በማስቀደም የስራ ክቡርነትን ተግባራዊ ስላደረገ የሀገርና የወገን አለኝታ ስለሆ እግዚያብሄር ይባርከው!!

መሐር ተገኝ ከበደ

83. እኛ ከጎንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ የመጣን የልምድ ልውውጡ እጅግ በጣም ጥሩና መንግስትም የሚፈልገውን የእድገት ጎዳና የሚያሳካ በመሆኑ ጥሩ ልምድ ሰርቶ መለወጥ የሚቻል መሆኑን ተረድተን ዳግመኛ አውራ አምባ ለመሆን ጥረት እናደርጋለን፡፡

ባምላኩ ጀምበሬ

84. እኔ ልሰጥ የምፈልገው አስተያየት ቢኖር ከናንተ ያገኘናቸው ተሞክሮዎችና የተግባር እይታዎች ለሀገራችን አልፎም ለአለማችን ዕድገትና ለውጥ ትልቅ ግብዓት ሊሆን እንደሚችል በሚገባ ተገንዝቢያለሁ፡፡ ይህንም ተሞክሮ ከራሴ አልፌ ለሌሎች ዜጎች ላስተላልፍ ቃል እገባለሁ፡፡

ቢኒያም

85.ዙምራና እናንይ እንዲሁም ሁሉም የአውራ አምባ ማህበረሰብ ትልቅ ስራ፣ ትልቅ አስተሳሰብ፣ አመርቂ ስራ፣ ድንቅና ልዩ የሆነ በእኛ እድሜ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በማየቴ- በራሳችሁ ተደሰቱ፡፡ ትልቅ ስራ ሰርታችኋል፡፡

ማህሌት አብርሃም

86. የወደፊቷን ኢትዮጵ መገለጫ መሆን የሚችል ማህበረሰብ መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡

ቴዎድሮስ በጋሻው

87. የአውራ አምባ መንደር በጣም የሚገርምና በጣም አዋቂ ህዝብ የተሰባሰበበት መንደር ነው፡፡ በጣም የሚገርመው የገለፃ መንገዳቸው ከትልልቅ ዩኒቨርስቲ የወጡ ነው የሚመስለው፡፡ አቶ ዙምራ ኑሩ ያላቸው ጭንቅላት ማንም የተማረ ሰው አይወዳደራቸውም፡፡ ቤታቸው፣ ንፅህናቸው፣ ፍቅራቸው፣ የወደፊቷን ኢትዮጵያን ያሳያል፡፡

መላክነሽ ዋጃ

88. ያየሁትንና የሰማሁትን ነገር መቼም ቢሆን ልረሳውና ላጠፋው አልችልም፡፡ ከዚያ ይልቅ ሁልጊዜም ቢሆን የማህበረሰቡን ዓላማ ስተገብር እንደምኖር ለራሴ ቃል እገባለሁ፡፡ ዙምራ ለዘላለም ይኑሩ፡፡ ሀሳባቸውም ይስፋፋ!!

ፊቃዱ ታፈረ

89. ከሁሉም በላይ ደስ ያለኝ ነገር ቢኖር ሰው በመሆኑ የሚምን ህበረተሰብ ስለሆነ ደስ ብሎኛል፡፡ ሁሉም የሰው ልጅ በተለይም ኢትዮጵያ በዚህ ማህበረሰብ ስር ብትስተዳደር ደስተኛ እንደሆንኩ ማረጋገዋ እፈልጋለሁ፡፡ በጣም ኮራሁ!!

መ/ር ቴዎድሮስ ከጎንደር

90. በጣም ነው ያስደነቀኝ፡፡ ይህ ማህበረሰብ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ እንደሚያደርገው ጥርጥር የለኝም፡፡ እኔም ከዚህ ቀን ጀምሮ የማህበረሰቡ አስተሳሰብ ተጋሪ መሆኔን እገልፃለሁ፡፡

ዋለልኝ ደምለው

91. ከአቶ ዙምራ ጋር በነበረኝ ቆይታም ሆነ የማህበረሰቡን ኑሮ በማይበት ጊዜ ትምህርት ቤት ሆኘ የተማርኳቸው ዓለምን በአንድ ወቅት ያነቃነቁ እንደነ አርስቶትልና ሶቅራጥስ ያሉትን ፈላስፎች ሳስብ ነበር፡፡ አቶ ዙምራ ባለ ራዕይና ለራዕዩ ስኬት ዋጋ የከፈለ ሰው ነው፡፡ ከኢትዮጵያዊ የተለየ ወጣ ያለ አእምሮ ያለው ሰው ነው፡፡ ለአገራችንም ትልቅ ሀብት ነው፡፡ አቶ ዙምራ ኢንጂነር ነው፣ ሶሽኦሎጅስት ነው፣ ኬሚስት ነው፣ ፖለቲከኛም ነው፡፡ ከሰራቸውና ከሚናገራቸው ነገሮች እነዚህን ሙያዎች ማየት ይቻላል፡፡

እያሱ ሽሽጉ

92. ያልተበረዘና ትክለኛ የሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚገኝበት ስፍራ በመምጣቴ ደስተኛ ነኝ፡፡ ወንድማችንና አባታችን ዙምራ በዓለማችን ካሉ ታላላቅ ምሁራንና ፈላስፎች መካከል ስለመሆኑ አልጠራጠርም፡፡

ጌትነት ብሩ

93. በስደት ላይ ስኖር ነጮች ሰለአገራችን ድህነት፣ ድርቅና ኋላቀርነት በየጊዜው በማንሳት አቆሰሉኝ፣ አደከሙኝ፡፡ ምነው የአገሬ ገበሬ ተለውጦ ባየሁ ብዬ ተመኘሁ፡፡ ምኞቴ የተሳካ መሰለኝ፡፡ ይኸው ዛሬ ለአገሬ ህዝብ ከፍተኛ አርአያ የሚሆን ስራ በተግባር አየሁ፡፡ እየሰራችሁት ያለው ስራ ሁሉ ከአገራችን አልፎ ለአፍሪካ ህዝብ ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ በርቱ!! ስራችሁን ሁሉ ፈጣሪያችን ይባርክ እላለሁ፡፡

ተፈራ ዘርፉ ከሆላንድ

94. እጅግ ድንቅ የሆነ ማህበረሰብና በጣም ልዩ የሆነ የስራና የመከባበር መንፈስ የነገሰበት ህዝብ በማየቴ እጅግ ተደስቻለሁ፡፡ ታሪካችሁና አኗኗራችሁ ለዓለም ህዝብ አርአያ የሚሆን ነውና በርቱ እላለሁ፡፡ ከምንም በላይ ግን እናንተን በማየቴና እንደናንተ ለመኖር እንድፈልግ ስላረጋችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

ስንታየሁ ይልማ

95. ስለአውራ አምባ ማህበረሰብ የሰማሁትን በተግባር አይቼ በጣም ተደንቄአለሁ፡፡ ይህ መልካም የስራ ባህልና አኗኗር ለሌሎች ማህበረሰቦች በአርአያነት /በመልካም ምሳሌነት/ እንዲስፋፋ የበኩሌን አስተዋፅኦ ለማድረግ ቃል እገባለሁ፡፡

መ/ር ደምስ መንግስት ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ

96. በእርግጠኝነት አውራ አምባ ከ5 ዓመት በኋላ 3 ፎቅ ህንፃዎች እንደሚሰሩ፣ ታላቅ ከተማ እንደምትሆንና ለወደፊት ዙምራ ብዙ ተከታይ እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡

አየለ አንዷለም ከደጋ ዳሞት

97.አውራ አምባ እንዲህ አልጠበኩም ነበር፡፡ ከጠበቅሁትና ካሰብኩት በላይ ሆኖ ነው የታየኝ፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ያለ እምቅ ችሎታና የመስማማት አዝማሚያ እዚህ መቅረት ያለበት ሳይሆን ለዓለም ህዝብ ገሀድ መውጣት እንዳለበት አምናለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

ጋዲሳ ከጎንደር

98.መኖር ከተባለ እንዲህ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "እኔ እንደወድኳችሁ እናንተም ተዋደዱ" የሚለው ተግባር በአውራ አምባ ማህበረሰብ ውስጥ አየሁ፡፡ "ያልሰራ አይብላ" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ እሱም በዙምራ ስራ ወዳድነት ሲተገበር አየሁ፡፡ ከቴዎድሮስ በኋላ የመጡ ዲሞክራት የሆኑ የኢትዮጵያ ልጅ ዙምራ ብቻ ናቸው፡፡ ታዲያ የሳቸውን ድምፅ የሚያስተጋባ ማነው? እኔ አንተ አንቺ ሁላችንም ነን፡፡ ኑ በአንድ ላይ አገራችንን እናልማ፡፡

በሪሁን ሰጡ

99.ቃላቶች ያጥሩኛል፤ ስለ አውራ አምባ ለመግለፅ፡፡ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ታሪክ ከልጅ ልጅ ተላልፎ ማየት ህልሜ ነው፡፡ በእውነት አይደለም ኢትዮጵያ ዓለም ላይ ስለሌለው አንድነታችሁ እጅግ አደንቃችኋለሁ፡፡ ፈጣሪ በፈቀደ ጊዜ ዳግም መጥቼ ለማየት ለራሴ ቃል እገባለሁ፡፡ ዳግም እወዳችኋለሁ፡፡ ለእድገታችሁም የበኩሌን አስተዋፅኦ አደርጋለሁ፡፡

ሰላም ደሳለኝ የ2ኛ አመት የስነ ህዝብ የጎንደር ዩኒቨርስቲ ተማሪ

100. በእርግጥ የዛሬ 4 ዓመት ይህችን ቦታ ጎብኝቼ ነበር፡፡ የነበረኝ ደስታ ወደር አልነበረውም፡፡ ዛሬ ደግሞ ከተማ ሆኖ ሳገኘው እጅግ ደስ አለኝ፡፡ ሰላምና ፍቅርን በእውነት ከናፈቅናት ማግኘትና ማድረግ እንደምንችል ይህ ማህበረሰብ አስተምሮኛል፡፡ በሀሳብም የአስተሳሰቡ ተካፋይ አባል መሆኔን እመሰክራለሁ፡፡ አንድ ቀን ይህች ቦታ ዓለምን የምታስተምር እንደምትሆን አልጠራጠርም፡፡ ረጅም ዕድሜን ለክቡር ዶክተር ዙምራ እመኛለሁ፡፡

ፍቅር ለሁላችን ይሁን!! ዘውዱ ሁሪሳ

101. ዙምራ የጀመርከው ውጥን ወደፊት ትልቅ ደረጃ እንደሚደርስ አትጠራጠር፡፡ በእንዲህ ዓይነት ትንሽና ገና ታዳጊ አገር ውስጥ እንዳንተ ዓይነት ህልምና ታላቅ ዓለማ ይዞ የተነሳ በህይወቴ አላጋጠመኝም፡፡ በመንገድህ ላይ ብዙ እንቅፋቶች እንደሚያጋጥሙህ አንተም ታውቀዋለህና ይህን አልነግርህም፡፡ ግን በርታ!! ተስፋ አትቁረጥ! ዛሬ በትንሹ የጀመርከው ነገ ትልቅ ብርሃን ይዞ ለዓለም ህዝብ ብቅ ስለሚል፡፡ (ስሙ ያልተገለፀ አስተያየት ሰጭ)

102. ዛሬ እዚህ በመምጣቴ በወሬ የሰማሁትን፣ በቴሌቪዥን ያየሁትን አረጋገጥኩ፡፡ በጣም የሚደንቅ ማህበረሰብ ነው፡፡ ምነው ሰው ሁሉ /ፍጡር ሁሉ/ እንደነሱ ባሰበ ብዬ ተመኘሁ፡፡ አንድ ቀን እግዚያብሔር ሁላችንንም አንድ ያደርገናል ብዬ አምናለሁ፡፡

ስምረት በየነ

103. በአውራ አምባ ማህበረሰብ ያየሁትን በጣም በመማረክ ነው ያሳለፍኩት፡፡ በዚህ አስተሳሰባችሁና አኗኗራችሁ በጣም ተማርኬአለሁ፡፡ እናም እኔም የእናንተው ሀሳብና ተግባር ባልችለውም እንኳን በመታገል እስከመጨሻው ድረስ እታገላለሁ፤ እሰራለሁ፡፡ ከአሁን በኋላ የማህበረሰባችሁ አባል ነኝ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ገዛኸኝ ገ/ፃዲቅ ከአዲስ አበባ

104. ለዓለም ሰላም፣ አንድነትና ልማት የሚሰራ ታላቅ ማህበረሰብ አውራ አምባ ልምዱ ለዓለም ሁሉ ይሰራጭ እላለሁ፡፡

ጥላሁን ታደሰ ከወላይታ ሶዶ

105. በህይወቴ ማየት ከምፈልጋቸው ነገሮች አንዱ የሆነው የአውራ አምባ ማህበረሰብ ነው፡፡ ለማህበረሰቡ ያለኝ አድናቆት በጣም የላቀ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች /ማህበረሰብ/ ስለብዙ ነገር ሊያወሩ ይችላሉ፡፡ የሚፈጽሙት ግን ጥቂቶቹን ብቻ ነው፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ ግን የሚኖረውን ይናገራል፡፡ ለጂማ ዩኒቨርሲቲ ትልቅ አክብሮት አለኝ፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ታላቅ ስራ ባለቤት ለሆነው ለዙምራ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በመስጠቱ፡፡

ተስፋዬ ያደታ

106. የአውራ አምባን ማህበረሰብ ስመለከተው የሃማኖት /ትክክለኛ/ አምባ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ የሰው ልጆች በፍቅር፣ በመተሳሰብ፣ የሚኖሩበት መንደር ሆኖ አይቸዋለሁ፡፡ ከአውራ አምባ ማህበረሰብ የህይወት መመሪያ ሁላችንም ልንማር ይገባናል፡፡ አውራ አምባ ማለት የኢትዮጵያ የአፍሪካ ብሎም የዓለም ብርቅዬ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ ልንንከባከበው ይገባል፡፡ ፍቅራችንን ከልብ ልንለግሳቸው ይገባል፡፡ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ ምሳሌያቸውን ተከትለን መንፈሳቸውን ማራመድ አለብን፡፡

ባህሩ አስፋው

107. እኔ በእውነት ያየሁት ቅንነታችሁን ሲሆን መንግስት ብሆን ኖሮ የእናንተን ልምድና አስተሳሰብ አንዱና ዋነኛው ስራዬ አድርጌ እይዝ ነበር፡፡ አሁንም ለመንግስታችን እምመክረው ይህንን ዓይነት ማህበረሰብ ጠንክሮ መፍጠር ላይ ቢያተኩር ጥሩ ነው፡፡ እንደ-ልምድ ልውውጥ ይሆን ዘንድ ከዚህ ማህበረሰብ አንድ- አንድ ሰው በመመደብ አልያም ከሌሎች ማህበረሰቦች ወይም ክልሎች ለተወሰነ ጊዜ እዚህ በማምጣት ልምዱን እንዲወስዱ፣ አስተሳሰቡን እንዲተገብሩና እንዲጋሩ ቢያደርግ ሀገራችን በአጭር ጊዜ በፍጥነት ቢያንስ አስተሳሰባችንን መለወጥ ይቻላል፡፡ በርቱ ፈጣሪ ይርዳችሁ!! የዶክተር ዙምራን ህይወት ያርዝምልን!! ሌላ ታሪክ የሚፈጥር እንዲሆን እመኝላቸዋለሁ፡፡

ደረጀ አያሌውና ህይወት ተሾመ ከአዲስ አበባ

108. አውራ አምባዎች!! እናንተ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ብሎም የዓለም ምሳሌዎች ስለሆናችሁ አርአያነታችሁ የሁሉም ዓለም ነውና ዓለም ሊያደንቃችሁና ሊያከብራችሁ ይገባል፡፡ በርቱ! በጣም እወዳችኋለሁ፡፡

አምባቸው ዳምጤ ተፈራ ከአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ

109. በየዘመኑ የተለያዩ ሰዎች ይነሳሉ፡፡ በመሆኑም ክቡር ዶ/ር ዙምራ በዚህ ዘመን የተነሱ ልዩ ሰው ናቸው፡፡ ናፍቆቴ ህልማቸው እውን ሆኖ ማየት ነው፡፡ ደግሞም ይሳካል፡፡

ዓለምወርቅ ጌታው

110. በመከራ፣ በስቃይ፣ በስግብግብነት ከተሞላው የጨለማ ዓለም ለትንሽ ጊዜ ቢሆንም ወጥቼ አውራ አምባ በመቆየቴ እራሴን እንደ እድለኛ እቆጥራለሁ፡፡ በእውነት ያየሁት ነገር እጅግ አስገራሚ የፍቅር ዓለም ነው፡፡ በተለይ ሌላው ዓለም አረጋዊያንን ሲያሰቃይ እናንተ ግን በፍቅር ትንከባከባላችሁ፡፡ ፈጣሪ ይርዳችሁ!! ማንም በእውነትና በፅናት ላይ የተመሰረተ ህይወትን እንዲሁም ለራሱ ደህንነት አስተማማኝ የሆነ ቦታን ማየት ከፈለገ መታየትና በህይወቱም ውስጥ ሊኖርበት የሚገባው ህብረተሰብና አካባቢ ነው፡፡

ብሩህ ውብት

111. አውራ አምባ እጅግ በጣም የተደነቅሁበትና የተደሰትኩበት ቦታ ነው፡፡ በኢትዮጵያውያን የተለመዱና አሳሪ ከሆኑ ባህሎች መካከል እንዲህ ዓይነት ስር ነቀል የሆነ የባህል ጥሰት አድርጎ ወደ እውነተኛውና አስደሳቹ የባህል መስመር በመግባት በእርግጥም ይህ ማህበረሰብ ቆም ብሎ ማሰብ የቻለና ወደፍፁምነት /perfection/ መንገዱን የያዘ ማህበረሰብ ነው፡፡ እወዳችኋለሁ፡፡ እኔም ባለሁበት የማህበረሰባችሁ አባል ነኝ፡፡ በርቱ!

ሳምሶን መኮንን

112. የሚደንቅ ባህል ነው፡፡ ሀሳቡ የሰው ብቻ አይደለም፡፡ የእግዚያብሔር እንጅ፡፡ የዓላማ ቁርጠኝነት ካለ የማይቻል ነገር እንደሌለ ያስተምራል፡፡

ብርሀኑ ገ/ሰንበት

113. ይህን ማህበረሰብ በማየቴ ሰፊ የስራና የአስተሳሰብ ለውጥ አግኝቻለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ያለኝን አስተሳሰብ በስራና በሰው ዘር ቀይሬ ባለኝ ዕድሜ ቅንና ስራ አክባሪ በመሆን ለመኖር ወስኛለሁ፡፡ ይህንን ላሳየኝ እግዚአብሔር ምስጋና ይገባው!!

ኢሳያስ ደምለው

114. እኔ ያየሁት በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው፡፡ ዙምራ እጅግ በጣም ትልቅ ዓለምን የሚቀይር አስተሳሰብ ያለው ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ እግዚያብሔር ትልቅ ዕድሜ ይስጠው!! ወደዋናው ነገር ስንገባ ከመንግስት ጋር በመተባበር የእናንተ ፕሮግራም በሳምንት ሁለቴ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዲተላለፍ ቢደረግ እናንተ የያዛችሁት ራዕይ ይህች በድህነት ውስጥ የምትገኝ ሀገርን የሚለውጥ ራዕይ ነው፡፡ በርቱ! ጥረታችሁ ዋጋ እያገኘ ይገኛል፡፡ መልካሙን እመንላችኋለሁ፡፡

ጌታሁን በሻህ የሶዶ ቡኢ ህፃናትና ቤተሰብ ልማት ማህበር

115. ዙምራ የአንተ ዓይነት ሰው ኢትዮጵያ በማግኘቷ እኔን እንደዜጋ ያኮራኛል፡፡

ይነበብ ደርሰህ

116. እኔን እስከዛሬ ድረስ ምንም ነገር አለመስራቴን ፍንትው አድርጎ ያሳየኝ የአውራ አምባዎች ጣምራ ጥበብ ነው፡፡

ደሴ ገ/ህይወት

117. ለነዚህ ዘላቂና ድንበር ለማይገድባቸው የአውራ አምባ ማህበረሰብ እሴቶች በጋራ መስራት አለብን፡፡

(ከአቶ መርሀ-ፅድቅ የአማራ ክልል ር/መስተዳድር አማካሪ)

7. ክክብር ዶ/ር ዙምራ ኑሩ አባባሎች ጥቂቶቹ

1. ሰዎች በሶስት ይከፈላሉ፡፡ ትልቅ ፣ መካከለኛ፣ ትንሽ
   - ትልቁ ሰው ማን ነው? ያውቃል ይጠይቃል፡፡
   - መካከለኛ ሰው ማን ነው? ያውቃል አይጠይቅም፡፡
   - ትንሹ ሰው ማን ነው? አያውቅም አይጠይቅም፡፡
2. ጉድና ድንቅ አንድ ቀን ነው፤ ጥሩ ነገርን ለማግኘት ይሉኝታ አይገድብህ!!
3. ለሰው ትልቁ ገንዘብ ሰው ነው፤ ሌላው ሁለተኛ ደረጃ ገንዘብ ነው፡፡
4. ስለ ራሱ ብቻ የሚያውቅ ሰው ስለሌላው አያውቅም፡፡
5. ብስል ሰው ማለት የዛሬን ተጎድቶ የነገን የሚያስብ ሲሆን ብልጥ ሰው ማለት ደግሞ የዛሬን እንጅ የነገን የማያስብ ማለት ነው፡፡
6. የሴት ስራ በመስራቴ የተቀየረው መህይምነቴ እንጅ ወንድነቴ አልተቀየረም፡፡
7. ጠብን የሚያመጡ ነገሮች መጥፎ አሰራርና መጥፎ አነጋገር ናቸው፡፡
8. ጠብ እንደሸረሪት ድር ያደራል እንጅ ስር የለውም፡፡ ምክንያቱም ጠብን የሚያጋንኑ ነገር ስራዎች ናቸው፡፡
9. ቅጣት በቀልን እንጅ ሰውን አያስተምርም፡፡ ሰውን የሚያስተምረው ስህተትህን አንቀበልም ብለን ስናስገልለው ነው፡፡ ሰው ከስተቱ እንዲማር ስህተቱን አናስተናግደው፡፡
10. አንድ ሰው ከሰው ከተገለለ ከባህር የወጣ አሳ ነው፡፡ ሰውን ከስተቱ ለማስተማር መገለልን እናሳየው፡፡
11. ሀዘን ማለት አንድ ሰው በህይወት እያለ ለደረሰበት ችግር ስንደርስለት ነው፡፡
12. በህይወቴ ከምንም ነገር በላይ የሚያስከፋኝ የተቸገረ ሰው አይቸ የምስጠው ሳጣ ነው፡፡
13. ደካማ ወገንን መርዳት የእድገት መሰላል እንጅ ውድቀትን አያመጣም፡፡
14. መረዳዳት ባህላችን ይሁን፡፡ አቅም እያለው ልመና መግባት አስፈላጊ አይደለም፡፡
15. መስጠትን ያላወቀ መለመንን ማን ነገረው?
16. ከሰራን ለምነን ያጣነውን ሳንለምን እናገኘዋለን፡፡
17. ዛሬ ማለቅ የነበረባቸው ስራዎች ሳይሰሩ ከቀሩ የነገን ስራ ይጋፋሉ፡፡
18. በአንድ ዳቦ ላይ የተንጠለጠለ ህይወት የትም አያደርስም፤ በመመራመን የዳቦ መስመሮቻችንን እናስፋ፡፡
19. ገበሬ መህይም አይደለም፡፡ የቆየ ሳይንስም ቢሆን ገበሬ ምሁር ነው፡፡
20. ሰላምን ከፈለግን ሁላችንም ራሳችንን ለሰው ልጆች ሰላም ማድረግ አለብን፡፡
21. እርስዎታ የአክብሮት መግለጫ ሳይሆን በሰው ልጆች መካከል ባዕድነትን የፈጠረ ነው፡፡ ለክብር ከሆነ ዘመድ ለምን ክብር አጣ?